ጅማ ዩኒቨርሲቲ

የሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ /አማርኛ/ ትምህርት ክፍል

ድህረ ምረቃ መርሃግብር

# በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ከ1922-1983 ዓ.ም. ድረስ የተፃፉ የስራ ደብዳቤዎች ቋንቋ አጠቃቀም ይዘት ትንተና፡፡

በቅድስት ጫንያለው

በተግባራዊ ስነልሳን የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ባህሎች ጥናት ድህረ ምረቃ

መርሀግብር ማሟያ ተሰርቶ የቀረበ፡፡

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሀምሌ 2010 ዓ.ም.

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

የሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ /አማርኛ/ ትምህርት ክፍል

ድህረ ምረቃ መርሃርግብር

**በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ከ1922-1983 ዓ.ም.**

**ድረስ የተፃፉ የስራ ደብዳቤዎች ቋንቋ አጠቃቀም ይዘትትንተና፡፡**

በቅድስት ጫንያለው

አማካሪ ጌታቸው አንተነህ (ፒ.ኤች.ዲ)

ረዳት አማካሪ ለማ ንጋቱ (ፒ.ኤች.ዲ)

በተግባራዊ ስነልሳን የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ባህሎች ጥናት ድህረ ምረቃ

መርሀግብር ማሟያ ተሰርቶ የቀረበ፡፡

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሀምሌ 2010 ዓ.ም.

የፈተና ቦርድ አባላት

የፈታኞች ስም________________________________ ፊርማ________________

________________________________ ፊርማ________________

የአማካሪ ስም ________________________________ ፊርማ______________

የትምህርት ክፍሉ ሃላፊ ስም__________________________ ፊርማ______________

## ምስጋና

ሁሌምለምትረዳኝ እግዚአብሔር ምስጋናዬ ልዩ ነው፡፡

የተለያዩ ተቋማት እና ግለሰቦች ቀና ትብብር እና እገዛ ባይታከልበት ኖሮ ይህ የምርምር ስራ አሁን የያዘውን መልክ እንዲይዝ ማድረግ እጅግ አስቸጋሪ ይሆን ነበር፡፡ በዚሁ መሠረት በዚህ ምርምር ላይ በከፍተኛ ደረጃ አሻራቸውን ካስቀመጡት ሰዎች መካከል የጥናት አማካሪዬ ዶ/ር ጌታቸው አንተነህ ቀዳሚውን ስፍራ ይይዛሉ፡፡ ዶ/ር ጌታቸው በጥናቱ ሂደት ወቅት የጥናቱን ረቂቅ ደጋግመው በማንበብ፣ አቅጣጫ በማሳየት እና ገንቢ ምክሮችን በመለገስ ለጥናቱ መሳካት ላበረከቱት አስተዋፅኦ ከፍተኛ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

በተመሳሳይ ይህንን ጥናት በማደርግበት ወቅት ገንቢ ሀሳቦችን፣ አቅጣጫዎችንና አካሄዶችን በመጠቆም ካላቸው እምቅ የእውቀት በረከት ላካፈሉኝ ዶ/ር ለማንጋቱ እጅግ የከበረ ምስጋናዬ ይድረሳቸው፡፡ከዚህ በተጨማሪም በጥናቱ ሂደት ወቅት ለሚያጋጥሙኝ ጥያቄዎችና ሙያዊ ክፍተቶች ካለምንም መሰልቸት ቀና ምላሻቸውን ለለገሱኝለ ትምህርት ክፍሉ መምህራን በሙሉ ምስጋናዬ ከልብ ነው፡፡

## አጠቃሎ

የዚህ ጥናት አላማ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ከ1922-1983 ዓ.ም. ድረስ የተፃፉ መደበኛ ደብዳቤዎችን በጥልቅ ዲስኩር ትንተና መርህ መሰረት የቋንቋ አጠቃቀም በመተንተን በተፃፉበት ዘመን የነበረውን ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ምን እንደሚመስሉ ማሳየት ነው፡፡ በዚህ መሠረት ጥናቱ አይነታዊ የምርምር አይነት በመሆኑ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ እና በደርግ ዘመን የተፃፉ የስራ ደብዳቤዎችን ለመተንተን ተሞክሯል፡፡ በጥናቱ ወቅት ደብዳቤዎቹ ከተፃፉበት ዘመን አኳያ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችን መሠረት አድርገው ከመተንተናቸው ባለፈ ደብዳቤዎቹ ከዘመን ዘመን አኳያ ያሳዩዋቸው ልዩነቶችም ተጠቅሰዋል፡፡ ጥናቱን ለማድረግ በመሠረታዊነት ጥናቱ በተመሰረተበት ጊዜ እና ቦታ ወሰን ያሉ ሰነዶችን በመረጃ ምንጭነት ለመጠቀም ተችሏል፡፡ በዚህ መሠረት የትንተናው ውጤት እንደሚያሳየው በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የተፃፉ የስ ራደብዳቤዎች ከተፃፉበት ዘመን መንፈስ፣ የፖለቲካና የማህበራዊ ሁኔታ አንፃር ሲተነተኑ ፖለቲካውና ሀይማኖቱ የነበራቸውን ቁርኝት፣ ፖለቲካውና የፖለቲካ አመራሩ በማህበረሰቡ ላይ ያደርስ የነበረውን አወንታዊና አሉታዊ ጫና ያሳያል፡፡ በተጨማሪ በአብዛኛው በጃንሆይ ዘመን፣ በአንፃራዊነት በደርግ ዘመን የተፃፉ ደብዳቤዎች ከቃላትአጠቃቀም አንፃር አሁን ካለንበት ዘመን ለየት ያሉ ቃላት ይጠቀሙ እንደነበር ለመረዳት ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል ደብዳቤዎቹ ከተፃፉበት የዘመን መንፈስ አንፃር ሲተነተኑ የፖለቲካ አመራሩ ግብርንና መሰል ጉዳዮችን መሠረት በማድረግ በዝቅተኛው የማህበረሰብ ክፍል ላይ ኢኮኖሚያዊ ጫና ያደርሱ እንደነበ መረዳት ተችሏል፡፡

በጃንሆይ ዘመን የተፃፉ ደብዳቤዎች ለንጉሰ ነገስቱ፣ ለንጉሰ ነገስቱ ሹማምንት እና ለላይኛው ለፖለቲካና የኢኮኖሚ መደብ የአዋቂነት፣ የልበ ብርሃንነት፣ የጌትነት፣ የጀግንነት፣ የአስተዋይነት፣ የችግር ፈችነት፣የደግነት ወዘተ ውክልና እና ሙገሳ ሲሰጡ በአንፃሩ ለታችኛው መደብ ደግሞ የምፅዋት ጠባቂነት፣ የአጥፊነት፣ ያላዋቂነት፣ የስልጣን ውስንነት እና የመሳሰሉት ውክልና ተሰጥቶት እናያለን፡፡ በደርጉ ዘመን የተፃፉ ደብዳቤዎች በአንፃሩ ከግለሰብ ይልቅ አብዮታዊት ኢትዮጵያን፣ ህብረተሰባዊት ኢትዮጵያን፣ ዘመቻን እና ወዘተ ሲያወድሱ ይስተዋላል፡፡ በተጨማሪም የፊውዳሉን ስርዓት ኮናኝ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ በአጠቃላይ በቀድሞ ስርዓት ይደረጉ የነበሩ ሁኔታዎችን ሁሉ በመኮነን ከዚህ በኃላ ፍፁም ለውጥ የመጣ መሆኑን የሚገልፁ ናቸው፡፡

**ማውጫ**

| አርዕስት | ገፅ |
|---|---|


ምስጋና ........ i
አጠቃሎ ........ ii
ማውጫ ........ iii
ምዕራፍ አንድ ........ 1
1. መግቢያ ........ 1
1.1 የጥናቱ ዳራ ........ 1
1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 3
1.3 የጥናቱ ዓላማ ........ 3
1.3.1 የጥናቱ ዋና ዓላማ ........ 3
1.3. 2 የጥናቱ ንዑሳን /ዝርዝር/ ዓላማዎች ........ 3
1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ ........ 3
1.5 የጥናቱ ወሰን ........ 3
ምዕራፍ ሁለት ........ 5
2. ክለሳ ድርሳናት ........ 5
2.1 ፅንሰ ሃሳባዊ መሰረቶች ........ 5
2.1.1 የፅህፈት አገልግሎት ........ 7
2.1.2 ድብዳቤ ........ 9
2.1.3 በኢትዮጵያ የደብዳቤ አፃፃፍ አጀማመር ........ 9
2.1.4 የስራ ደብዳቤ ........ 9
2.1.5 የስራ ደብዳቤ አፃፃፍ ስልት ........ 10
2.1.6 የደብዳቤ አይነቶች ........ 13
2.2 የጥልቅ ዲስኩር ትንተና ዘዴ (CDA) ........ 15
2.3ቀደምት የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ........ 19
2.4 ጥናቱ የተካሄደበት አካባቢ ዳራዊ መግለጫ ........ 23
2.5 የብሔር እና ቋንቋ ብዝሀንነት በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ........ 24
ምዕራፍ ሶስት ........ 25
3. የጥናቱ ዘዴና አካሄድ ........ 25
3.1 የጥናቱ ዘዴ ........ 25
3.2. የናሙና አመራረጥ ........ 27
3.3. የመረጃ ምንጮች ........ 28

3.4. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ........ 29
3.4.1. ሰነድ ፍተሻ (document analysisi) ........ 29
3.5. የመረጃ መተንተኛ ዜዴ ........ 30
3.6. የጥናቱ አካሄድ ........ 31
3.6.1. ቅድመ መረጃ ስብሰባ ........ 31
3.6.2. የመስክ መረጃ ስብሰባ ሂደት ........ 32
3.6.3. ድህረ መረጃ ስብሰባ ........ 32
3.7. የጥናቱ ተአማኒነት መለኪያ (Validity) ........ 32
3.8. የምርምር አከናወን ስነ ምግባራዊ ጉዳዮች (Ethicla concideration) ........ 33
ምዕራፍ አራት ........ 34
4. በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ከ1922-1983 ዓ.ም ድረስ የተፃፉ ደብዳቤዎች ቋንቋ አጠቃቀም ይዘት ትንተና ........ 34
4.1. በጃንሆይ ዘመን በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የተፃፉ ደብዳቤዎች ቋንቋ አጠቃቀም ይዘት ትንተና ........ 34
4.1.1. ፖለቲካዊ ጉዳዮች ትንተና ........ 34
4.1.2. ማህበራዊ ጉዳዮች ትንተና ........ 39
4.1.3. ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ትንተና ........ 40
4.2. በደርግ ዘመን በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የተፃፉ ደብዳቤዎች ቋንቋ አጠቃቀም ይዘት ትንተና ........ 42
4.2.1. ፖለቲካዊ ጉዳዮች ትንተና ........ 42
4.2.2. ማህበራዊ ጉዳዮች ትንተና ........ 46
4.2.3. ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ትንተና ........ 47
4.3. በኃይለሥላሴ እና በደርግ ዘመን በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የተፃፉ ደብዳቤዎች ........ 48
መዋቅራዊ ሁኔታ እና ከዘመን ዘመን ያሳዩዋቸው ለውጦች ........ 48
ምዕራፍ አምስት ........ 50
5. ማጠቃለያ መደምደሚያ እና አስተያየት ........ 50
5.1 ማጠቃለያ ........ 50
5.2 መደምደሚያ ........ 52
5.3 አስተያየት ........ 53
ዋቢ መፅሀፍት ........ 55

# ምዕራፍ አንድ

## 1. መግቢያ

### 1.1 የጥናቱ ዳራ

በዚህ ጥናት ውስጥ የስራ ደብዳቤዎችና ማመልከቻዎች ላይ ትንተና የሚደረግ ሲሆን ወደ ዋናው ጥናት ትንተና ከመግባቱ በፊት ስለ ኢትዮጵያ የስነ ፅሁፍ ባህልና ታሪክ መግለፅ መነሻ ይሆናል፡፡ ኢትዮጵያ ከሰሀራ በታች ካሉ የአፍሪካ ሀገራት መካከል ልዩ በሆነ መልኩ የራሷ የሆነ ፊደል እና የስነ ፅሁፍ ባህል ያላት ሀገር ናት፡፡ የጥንታዊት ኢትዮጵያ ስነ-ፅሁፍ እስከ መካከለኛው ክፍለ ዘመን ድረስ በግዕዝ ይፃፍ ነበር፡፡ ግዕዝ በአለም ላይ በጣት ከሚቆጠሩ እንደ እብራይስጥ እና ግሪክ ጥንታዊ የፅሁፍ ቋንቋዎች መካከል አንዱ ነው፡፡ በዚህ መሰረት በተለይ በኢትዮጵያ የክርስትና ስነ ፅሁፍ ውስጥ ግዕዝ በብዛትና ልዩ በሆነ ጥራት ከፍተኛ ስራዎች ሲሰሩበት የነበረና እየተሰራበት ያለ ቋንቋ ነው፡፡ ከክርስቶስ ልደት በኃላ በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የታላቁ ጥንታዊት አክሱም ግዛት ንጉስ በሆኑት ካሌብ አማካይነት የኦርቶዶክስ ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ መግባቱንና መስፋፋቱን ተከትሎ የግዕዝ ስነ-ፅሁፍ በከፍተኛ ደረጃ መስፋፋቱና ማደጉይነገራል፡፡ ለምሳሌ እንደብራና እና የመሳሰሉት አዳዲስ የመፃፊያ ግብዓቶች ከዚህ ዘመን በኃላ በከፍተኛ ደረጃ መስፋፋታቸው ይታመናል፡፡ በዚህመሰረትከጥንት ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ የኢትዮጵያ የስነ ፅሁፍ ባህል ሳይቋረጥ እንደቀጠለ ይገኛል (D Nosnitsin 2012) (Sertse Abebe 2011)::

የሰው ልጅን ማህበራዊ ግንኙነት ለማቀላጠፍ እገዛ የሚያደርገው ፅህፈት እንዳለፈበት የዕድገት ደረጃና ዘመናት አኳያ የተለያዩ መሻሻሎችን እያደረገ የመጣ የማህበረሰብ እሴት መሆኑ ይታወቃል፡፡

በአማርኛ ቋንቋ ውስጥ እየተጠቀምንባቸው የምንገኘው ፊደላት አመጣጥ ከግዕዝ ሲሆን የግዕዝ መሰረት ሳባ የሚባለው ሲሆን ከደቡብ አረቢያ ወደ ኢትዮጵያ በመጡ ህዝቦች አማካይነት ወደ ሀገራችን መግባቱንና ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ700 ዓመተ ዓለም ጀምሮ አገልግሎት ይሰጥ እንደነበር ይገለፃል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚነሱ ሌሎች መላምቶችም አሉ፡፡ ከነዚህ ውስጥ አንዱ ለአማርኛ ፊደል አመጣጥ እንደ ምክንያትነት የሚጠቀሰው በአክሱም ዘመነ መንግስት በንጉስ ካሌብ አገዛዝ ዘመን የኢትዮጵያዊያን ፈላስፎች የፈጠሩት ነው ተብሎ የሚሰነዘረው መላምት እንደሆነ ይኸው (D Nosnitsin 2012) በሰፊው ይገልፀዋል፡፡

በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ በብራና ላይ የሚፃፉ የዕጅ ፅሁፎች (Manuscript) በሀይማኖት ተቋማት ማለት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ውስጥ አገልግሎት

ከመስጠታቸው ባለፈ በሀገሪቱ የፖለቲካና ማህበራዊ መዋቅር ውስጥ ከፍተኛ ሚና ነበራቸው፡፡ ይህ ማለት በጥንታዊት ኢትዮጵያ በመካከለኛው ክፍለ ዘመን ከዚያም ሲያልፍ እስከ ቅርብ ዘመን ድረስ ነገስታት እና ግለሰቦች ብራናን ለደብዳቤ መፃፊያነት ለአስተዳደራቸው መዋቅር፣ አዋጅ ማወዳጃነት ፣ በቅርብ እና በሩቅካሉ ነገስታት ጋር መልዕክት መለዋወጫነት ይጠቀሙበት እንደ ነበር በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት የተገኙ የአማርኛ የብራና የዕጅ ፅሁፎች ይጠቁማሉ (Sertse Abebe 2011)::

በኢትዮጵያ እስከ 19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ ማመልከቻዎችና ደብዳቤዎች ፣ የነገስታት መዋዕለ ድርሳናት ፣ የነገስታት ገድል ፣ አዋጆች ወዘተ በብራና ላይ ብቻ ይፃፍ ነበር፡፡ ብራና ማለት የእንስሳትን ቆዳ በተለይም የፍየል እና የበግን ቆዳ በልዩ

ሁኔታ በማለስለስ በወረቀት መልክ የምንጠቀምበት ለመፃፊያነት የሚጠቅም ነው፡፡ ከ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ ግን በኢትዮጵያ ታሪክ ዘመናዊ ወረቀት መግባቱ ይነገራል፡፡ ሆኖም በጊዜው ዘመናዊ ወረቀት በወቅቱ የነበሩ የኢትዮጵያ ነገስታት ከውጪ ነገስታት ጋር ለሚያደርጓቸው የደብዳቤ ልውውጦች ካልሆነ በስተቀር ለሀገር ውስጥ ፍጆታ መቀጠም ያልተለመደ ነበር (Bausi 2006)፡፡

በአጠቃላይ የኢትዮጵያ የስነ ፅሁፍ ባህል እንዳለፈበት የዕድገት ደረጃ የተለያዩ ለውጦችንና መሻሻሎችን እያሳየ አሁን ያለበት ደረጃ መድረሱ በተለያዩ ፀሀፊያን የሚገለፅ ነው፡፡ ስለ ኢትዮጵያ ስነ-ፅሁፍ ሲነሳ ግዕዝ ቀዳሚውን ስፍራ የሚይዝ ይሆናል፡፡ የግዕዝ ቋንቋ ፅሁፍ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ክርስትና መግባቱና መስፋፋቱን ተከትሎ የመጣ እንደሆነም ተጠቅሷል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የግዕዝ ስነ-ፅሁፍ በከፍተኛ ሁኔታ በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን አካባቢ መስፋፋቱና ማደጉ የሚገለፅ ነው፡፡ በዚህ ወቅት ለኢትዮጵያስነ ፅሁፍ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረከተው “ብራና” ነው፡፡ ብራና እንደ አሁኑ ወረቀት የሌለበት ወቅት ከእንስሳት ቆዳ በተለይም የበግና የፍየል ቆዳ በማለስለስ ለመፃፊያነት የሚጠቀም ነው፡፡ ይህም የብራና ላይ ፅሁፍ እስከ 19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ድረስ የነበረና በኃላ ግን ከ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀመሮ ዘመናዊ ወረቀት ወደ ኢትዮጵያ መግባቱን በመከተል የብራና አገልግሎትም እየቀዘቀዘ የመጣበት ወቅት እንደሆነ ከላይ ለመረዳት ችለናል፡፡

እንግዲህ የኢትዮጵያ የስነ ፅሁፍ ባህል ከጥንት ጀምሮ አሁን እስከሚገኝበት ደረጃ ድረስ በተለያዩ የእድገት ዝግመተ ለውጥ ያለፈ ቢሆንም ፅሁፎቹ በየተፃፉባቸው ዘመንና ወቅት በሀይማኖት ተቋማት እና በፖለቲካ መዋቅር ውስጥ ከፍተኛ ሚና ነበራቸው፡፡ ይህ ማለት በጥንታዊት ኢትዮጵያ ፣ በመካከለኛው ክፍለ ዘመን ከዚያም ሲያልፍ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ያሉትን ፅሁፎች ብንመረመራቸው በተፃፉበት ወቅት የነበረውን የዘመን መንፈስ አመልካች መሆናቸውን እንረዳለን፡፡ በመሆኑም ይህንን እሳቤ ከግምት ውስጥ በማስገባት ለቀጣዩ ጥናት ውስጥ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ከ1922 -1923 ዓ.ም ድረስ የተጻፉ የስራ ደብዳቤዎችን ቋንቋ አጠቃቀም ይዘት ትንተና በማድረግ በየወቅቱ የነበሩትን የዘመን መንፈሶች ለማሳየት የታሰበ ሲሆን ለሚከተሉት መሪ ጥያቄዎችም ምላሽ ይሰጣል ተብሎ ይገመታል፡-

- ከ1922– 1983 ዓ.ም ድረስ የተፃፉ የስራ ደብዳቤዎች የቋንቋ አጠቃቀም ሲመረመር በወቅቱ የነበረው ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሁኔታ እንዴት ተገልጿል?
- በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ከ1922 -1983 ዓ.ም ድረስ የተፃፉ የስራ ደብዳቤዎች አጠቃላይ የአፃፃፍ ስልት ምን ይመስላል?
- ከ1922 – 1983 ዓ.ም ድረስ የተፃፉ የስራ ደብዳቤዎች መዋቅር (መግቢያ፣ ሀተታና መደምደሚያ) ከዘመን ዘመን ያሳዩªቸው ልዩነቶች ምን ይመስላሉ?

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

የዚህ ጥናት አነሳሽ ምክንያት በአጋጣሚ ላይ የተመሰረት ነው፡፡ አጥኚዋ በ2008 ዓ.ም በታሪክ ትምህርት ክፍል የተፃፉ የተለያዩ ጥናታዊ ፅሁፎችን የማየት እድሉ ገጥሟታል፡፡ በዚያን ጊዜ በጥናታዊ ፅሁፎቹ ላይ እንደ “Apendex” ተያይዘው የተቀመጡ በተለያዩ ዘመናት የተፃፉ ደብዳቤዎችን ተመልክታለች፡፡ በመሆኑም አጥኚዋ አሁን እየተማረች ባለችው ትምህርት በዲስኩር ትንተና መርህ ተጠቅማ የደብዳቤዎችን የቋንቋ አጠቃቀም በመተንተን የተማረችውን ትምህርት የመተግበር ሀሳብ በውስጧ ያድራል፡፡ እነዚህ ደብዳቤዎች በተፃፉበት ጊዜ እና ወቅት ስለነበረው ማህበራዊ ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ለማወቅ ቀጥተኛ ምንጭ ሆነው የሚያገለግሉ በመሆናቸው  የስራ ደብዳቤዎችን በመምረጥ፣ በመመርመርና በመተንተን በወቅቱ የነበረውን የዘመን መንፈስ ለማሳየት ተነሳስታለች፡፡

## 1.3 የጥናቱ ዓላማ

### 1.3.1 የጥናቱ ዋና ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ከ1922 – 1983 ዓ.ም ድረስ የተፃፉ የስራ ደብዳቤዎችን የቋንቋ አጠቃቀም መተንተን ነው፡፡ ይህ ዋና ዓላማም የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች ይኖሩታል፡፡

### 1.3. 2 የጥናቱ ንውሳን /ዝርዝር/ ዓላማዎች

- ከ1922 -1983 ዓ.ም ድረስ የተፃፉ የስራ ደብዳቤዎች የቋንቋ አጠቃቀም በመመርመር በወቅቱ የነበረውን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሁኔታ ይተነትናል፤
- በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ከ1922 – 1983 ዓ.ም ድረስ የተፃፉ የስራ ደብዳቤዎችን  አጠቃላይ የአፃፃፍ ስልት ይመረምራል፤
- ከ1922 – 1983 ዓ.ም ድረስ የተፃፉ የስራ ደብዳቤዎችን መዋቅር (መግቢያ፣ ሀተታ እና መደምደሚያ) ከዘመን ዘመን ያሳዩዋቸውን ለውጦች ይተነትናል፡፡

## 1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት ቀጥሎ የቀረቡትን ጠቀሜታዎች ከማስገኘት አንፃር አስፈላጊነቱ ተገቢ ይሆናል ተብሎ ይታመናል፡፡

- ደብዳቤዎቹና ማመልከቻዎቹ በተፃፉባቸው ዘመናት የነበረው የስራ ደብዳቤ አፃፃፍ ይዘት ምን ይመስል እንደነበር ለአሁኑ ትውልድ እና ለመጭው ትውልድ እንደ ማሳያነት ሊያገልግል ይችላል፤
- ደብዳቤዎቹና ማመልከቻዎቹ ከዘመን ዘመን የነበራቸውን የአፃፃፍ ስልት ልዩነቶች ለመጪው ትውልድና ለአሁኑ ትውለድ ግንዛቤ ሊሰጥ ይችላል፤
- ወደፊት በተመሳሳይ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ጥናት ማድረግ ለሚፈልጉ ተመራማሪዎች እንደ መነሻ ሃሳብ ሆኖ ሊያገለግላቸው ይችላል፡፡

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

ሀገራችን ኢትዮጵያ ቀደምት የስነፅሁፍ ባህል ያላት ሀገር ከመሆንዋ አንፃር በተለያዩ አካባቢዎች ወይም ሀገራት በተለያዩ ጊዜያት የተፃፉ በርካታ ፅሁፎች ይገኛሉ፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥ በየስራ ደብዳቤዎች ላይ ጥልቅ ትንታኔ የሚሰጥ ቢሆንም

ሁሉንም የሀገራችንን የስራ ደብዳቤዎች ማግኘት አስቸጋሪ ስለሚሆን የይዘትና የቦታ እንዲሁም የዘመን ወሰኖች እንደሚከተለው ለይቶ ማስቀመጥ አስፈላጊ ሆኗል፡፡

የይዘት ወሰን፡- እንደሚታወቀው በሀገራችን ኢትዮጵያ በተለያዩ ዘመናትና በተለያዩ ሀገራት የተፃፉ ፅሁፎች ይገኛሉ፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥ ትኩረት ተደርጎባቸው የተመረጡት ፅሁፎች የስራ ደብዳቤዎች ብቻ ናቸው፡፡

የቦታ ወሰን፡- በዚህ ጥናት ውስጥ ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው የስራ ደብዳቤዎች ትንተና የሚደረግ ሲሆን፣ በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች ተፅፈው ከሚገኙት የስራ ደብዳቤዎች ውስጥ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ በተለይም በጅማ ዞን፣ በከፋ፣ በቤንች ማጂ በየም ልዩ ወረዳና በዳውሮ ዞን የተፃፉ የሥራ ደብዳቤዎ ላይ ተተኩሯል፡፡

የጊዜ /የዘመን/ ወሰን፡- በኢትዮጵያ በተለያዩ ዘመናት ከተፃፉ የስራ ደብዳቤዎች ውስጥ ለዚህ ጥናት የተመረጡት ከ1922 – 1983 ዓ.ም ድረስ የተፃፉት የሥራ ደብዳቤዎች ብቻ ናቸው፡፡ በዚህ የጊዜ ክልል ውስጥ ያሉት ላይ ብቻ የተተኮረው ከኃይለሥላሴ ዘመነ መንግስት በፊት የነበሩ ደብዳቤዎችን በቀላሉ ማግኘት ባለመቻሉ፤ ከ1983 ዓ.ም ወዲህ ያሉት የስራ ደብዳቤዎች ደግሞ በተለያዩ የስራ ቋንቋዎች የተፃፉ በመሆናቸው ይህንን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የቋንቋ ችግር እንዳይከሰት በማሰብ ከ1922-1983 ዓ.ም ድረስ ያሉት ላይ ብቻ ተተኩሯል፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## 2. ክለሳ ድርሳናት

ይህ ክፍል በዋናነት የሚዳስሳቸው ጉዳዮች በተለያዩ ጊዜያት በልዩ ልዩ ጥናትና ምርምር ስራዎች ከፅህፈትና ደብዳቤዎች ጋር ተያያዥነት ባላቸው ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የተፃፉ ፁሁፎችንና ለቅድመ ምረቃ እንዲሁም ድህረ ምረቃ የተሰሩ ስራዎችን ነው፡፡

### 2.1 ፅንሰ ሃሳባዊ መሰረቶች

"ፅሁፍን የፈጠሩት እና የሰነዱት ሰዎች የመጀመሪያዎቹ ታላላቅ የስነ ልሳን ጠበብቶች ናቸው፡፡ ምክንያቱም የሥነ ልሳን ጥናትን ጀመሩት እነሱ ናቸውና" ("The men who invented and perfected writing were great linguists and it was they who created linguistics) በማለት የገለፀው በ20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ አካባቢ ታዋቂ የሥነ ልሳን ተመራማሪ የነበረው ፈረንሳያዊው የስነ ልሳን አጥኚ Antoine Millet ነበር፡፡

የተለያዩ ምሁራን ስለፅህፈት ምንነት ፣ አጀማመር እና ታሪካዊ ዕድገት እንደየ ጊዜው የተለያዩ መረጃዎችን ይሰነዝራሉ፡፡ ምሁራኑ የሚሰጧቸው መረጃዎች እንደ ጊዜው ርቀትና ቅርበት እንዲሁም ከደረሱበት የዕውቀት ደረጃ መለያየት የተነሳ የሚቀራረቡና መጠነኛ ልዩነት የሚያሳዩ ቢሆኑም አንድ የጋራ መነሻና የሚያግባባቸው ሃሳብ መኖሩ ይታመናል፡፡ በሸክላዎች ላይ በተለያየዩ ቅርፆች ከመፅሐፍ እስከ ኮምፒውተር «ቺፕሶች» ላይ እስከመፃፍ ድረስ ላለፉት በርካታ ሺ አመታት ከሰው ልጆች ጋር አብሮ የኖረው ፁሁፍ ከጊዜ ወደ ጊዜ አሥፈላጊነቱ እየጨመረ መጥቷል፡፡ በምድር ላይ ምንም እንኳን በርካታ መቶ ሚሊየኖች ማንበብ እና መፃፍ የማይችሉ ቢሆኑም እንኳን በዘመናችን ወሳኝ የሰው ልጆች እንቅስቃሴዎች ከሚገመተው በላይ ከፁሑፍ ጋር የተያያዘ ሆኗል፡፡

በዚህ የተነሳ ዛሬ ዛሬ ብዙዎቹ የሰው ልጆች ህጋዊ የግንኙነት መፍጠሪያ መንገዶች ከንግግር ይልቅ ፁሁፎች እየሆኑ በመምጣት ላይመሆናቸውን ጥናቶች ያመላክታሉ (Flarian Coulmas 2017)፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ፅህፈትየሰው ልጅ በሥልጣኔ ሂደት ውስጥ ከፈጠራቸው የፈጠራ ውጤቶች መካከል ጠቃሚው እና ተፅኖ ፈጣሪው ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም ለዚህ ማሳያነት ይውል ዘንድ በየአብያተ መፀሀፍቱ ፣ በየሰነድ መሰናጃ መአከላት ፣ በየመረጃ መረብ ማዳረሻ ማዕከላት እጅግ በዓይነት የብዙ የፁሁፍ ውጤቶች በውስጣቸው የብዙ መቶ አመታት ከዛምሲያልፍ የሺ አመታት እውቀቶች ተጭቅባቸው ለሰው ልጆች እና ለአለም መሻሻል የሚኖራቸውን ሚና በአይነ ህሊና መታዘብ በቂ ነው፡፡ በዚህ አጋጣሚ ፁሁፍ ሥላለፈው ክስተት ብቻ የምናትትበት እና የምንዘግብበት ሳይሆን የወደፊቱንም የምንተልምበት አቅጣጫየምናሳይበት ድንቅ የፈጠራ ውጤት ነው፡፡ ፁሁፍ ምንድን ነው? ለሚለው ጥያቄ በተለያዩ ፈላስፎች ፀሐፍት እና ተመራማሪዎች የተለያዩ መግለጫዎች ይሰጣሉ፡፡ አንዳንዶች ፁሁፍ ቋንቋን ሥልታዊ በሆነ የውክልና ምልክቶች የምንቀርፅበት የፈጠራ ውጤት ነው ሲሉ፤ ሌሎች ደግሞ ፁሁፍ ብልሀታዊ (systematic) በሆነ መንገድ ከአንድበት የሚወጣን ቃል የምልክት ውክልና በመስጠት ትርጉም ወዳለው ነገር የምንለውጥበት የጥበብ ውጤት ሲሆን የጥበቡ ባለቤቶችም በጥበቡ ዙሪያ የሰለጠነ ባለሞያዎች ናቸው (Fiorian Coulmas 2017)፡፡

ፅሁፍን በተመለከተ ፅሁፍ እንዴት እንደሚሰራ ወይም እንዴት እና በምን መልኩአገልግሎት ላይ እንደሚውል ፣ ምን አይነት አገልግሎት እንዳለው እና ይሄንንለመረዳት ምን አይነት ዘዴ ተግባር ላይ መዋል አለበት የሚሉ እና መሰል ጥያቄዎችን ለመመለስ የስነ ልሳን ተመራማሪዎች ፣ የታሪክ ተመራማሪዎች የባህላዊ አንትሮፖሎጂ ተመራማሪዎች ፣ የኮምፒውተር ፕሮግራም ተመራማሪዎች የሥነልቦና ተመራማሪዎች እና ፊሎሊጂሥቶች (philologists) ወይም ያለፉ የፅሁፍ ሰነዶችን አጥኚዎች በየዘርፋቸው ሥለ ፁሑፍ የሚፈለጉትን ነገር ለማግኘት ምርምሮችን እና ጥናቶችን ያደርጋሉ፡፡ በዚሁ መሰረት ፅሁፉ ምንድን ነው የሚለውን ፅንሰ ሐሳብ በከፊል ተመሳሳይነት ያለው ትርጓሜ ቢሰጡትም ወጥነት እና ተመሳሳይነት ያለው ሁሉም ተመራማሪዎች ፣ ፈላስፎች እና በዘርፉ ጥናት ያደረጉ አካላት የተሥማሙበት ትርጓሜ ለመስጠት ግን እስከዛሬ ሥምምነት ላይ አልተደረሰም፡፡ ለዚህ ማሳያ ይሆነን ዘንድ ሥለ ፅሁፍ  ምንነት በተለያዩ ፋላስፎች የተነሱሀሳቦችን እንደሚከተለው እንመለከት፡-

አርሥጣጣሊሥ **(Aristotle):** ይህ ግሪካዊ ፈላስፋ እና ሳይንቲስት ፅሁፍን በተመለከተ የሰጠውን ገለፃ በተመለከተ የሰጠው ገለፃ በተለያዩ ፅሁፎች ላይ ሥለ ፅሁፍ በሚሰጡ ማብራሪያዎች ላይ በተደጋጋሚ ይታያል፡፡ እንደ አርጣጣሊስ(Aristotle) አገላለፅ ፅሁፍ የንግግር  ጥገኛ እና ተከታይ ነው፡፡ በዚህ የተነሳ የፅሁፍ ሥራ ንግግሮችን በምልክታዊ ገለፃ መወከል ብቻ ነው ይላል፡፡ በሌላ በኩል ይህንን የአርጣጣሊሥን የፅሁፍ ምልከታ የፅሁፍ ቅድመ ጥናትን በምናይበት ጊዜ በሥዕል መልክ ይቀርቡ የነበሩ ፅሑፎች የነገሮችን ወይም ሀሳቦችን ንግግራዊ ውክልና ያልያዙ እንደነበሩ በማንሳት ይሞግታሉ፡፡ ነገር ግን በአርሥጣጣሊስ እይታ በፁሑፍ ውስጥ ያሉ ፊደላት ከንግግር ድምፅት ጋር አብረው የሚሄዱ እና በንግግር ድምፀት ላይ ተመርኩዘው የተፈበረኩ መሆናቸውን ይገልፃል፡፡ ከዙህ በተጨማሪ አርሥጣጣሊስ በነገሮች፣ በሀሳብ፣በቃላት እና ፅሁፍ መካከል ምክንያታዊ የሆነ ግንኙነት መኖሩን ያስረዳል፡፡ በዚሁ መሰረት እንደ ግለሰብ የሚያውን ነገር በዓይነት ህሊናው ውስጥ በመሳል ሀሳብ ያደርገዋል ከዛም ቡሀላ በንግግር መልክ ያሰበውን ነገር ቃል ያደርገዋል ያ ቃል ደግሞ በሁለት መንገድ ይገለፃል፡፡ አንደኛ በድምፅ መልክ ሲሆን ሁለተኛው በድምፅ ላይ በመመርኮዝ በፅሁፍ መልክ ነው በማለት ያብራራል (Florian Colmas 2017)፡፡

ሊ ሲኽ (Liu Hsiph): ከክርስቶስ ልደት በኃላ ከ 465 -522 የኖረ ቻይናዊ የቡደሀ እምነት ቄስ እናፈላስፋ (thinker) ሲሆን በቻይና ሥነ-ፅሁፍ ታሪክ ውስጥ ከሚጠቀሱት ፀሀፍት መካከል አንዱ ነው፡፡ ፅሁፍን በተመለከተ ሊሲኽ (Liu Hsiph)ከአርሥጣጣሊስ ጋር በብዙ መልኩ ተቀራራቢነት ያለው ገለፃ ቢሰጥም በተወሰኑ ነጥቦችእንደሚለይ ለማየት ይቻላል፡፡ ሊ ሲኽ Liu Hsiph “Coving of the literary Dragon” በሚባለው ፅሁፍ ላይ እንዳለው ጭንቅላት ስራውን በሚሰራብት ጊዜ ንግግሮች (ቃላቶች) ይወለዳሉ (ይወጣሉ) ቃላቶች በሚወጡበት ጊዜ ፅሁፍ ይፈበረካል” በማለት ከ አርስጣጣሊስ ጋር በሚመሳሰል መልኩ ፅሁፍ በንግግር ላይ ጥገኛ እንደሆነ የሚመሥል ገለፃ ሰጥቷል፡፡ ነገር ግን ይህ ቻይናዊ ፈላስፋ ከንግግር ቋንቋ ጋር የተያዘ እና የንግግር ቋንቋን የሚወክል ነው የሚለውን ይቃወማል (Florian Colmsa 2017)፡፡

ፕላቶ (Plato): ይህ የሶቅራጦስ ተማሪ የአርስጣጣሊስ መምህር የሆነው ፕላቶ ሥለፅሁፍ በሚገልፅበት ፅሁፍ ያለፈ ክስተትን ቀርፀን የምናስቀርበት እረዳት እንጂ በምንም መልኩ ንግግርን ሊተካ አይችልም በማለት የተለየ ምልከታውን ይሰነዝራል፡፡ በፕላቶ ገለፃ መሰረት በፅሁፍ ውስጥ የተፃፈውን ነገር በማንበብ ግልፅ ያልሆነ ነገር ቢኖር የምንጠይቀው አካል የለም በንግግር

ጊዜ ግን ያልገባንን ነጥብ ንግግር ከሚያደርገው አካል መጠየቅ እንችላለን፡፤ ከዚህ ባለፈ በንግግር ጊዜ ከንግግር አድራጊው የአካል እንቅስቃሴ በርከት ያለ መልዕክት እና ማብራሪያ ማግኘት እንችላለን በማለት ያብራራል፡፡በተቃራኒው የተፃፉ ቃላት ዝም ያሉ የአሁን ያልሁኑ ወይም በፐላቶ አገላለፅ (dead) ናቸው በማለት ያብራራል (Florian Colmas 2017)፡፡

በሌላ በኩል ፅሁፍ ለአንድ የንግግር ቋንቋና ሃሳብ ውክልና የተሰጣቸውን ፊደሎች እና ምልክቶች በመጠቀም ማህበራዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ እንዲሁም ፖለቲካዊ ሃሳቦችንና ግንኙነቶችን ለማሳለጥ የሚረዳ ዘዴ መሆኑን (Peter Damerow 2006)ይገልፃል፡፡ (Isabel 2009) ስለ ፅሁፍ ምንነት ስትገልፅ ደግሞ ፅሁፍ በአንድ ቋንቋ ውስጥ የሚነገሩ ድምፆችን ውክልና በመውሰድና ቀጥታዊ ያልሆነ ግንኙነት በመፍጠር ተግባቦት የምናካሂድበት ስልት መሆኑን ታብራራለች፡፡ እንግዲህ ከላይ የተገለፁት ፀሐፊዎች እና ፈላስፎች ስለፁሁፍ ምንነት ሲገለፁ ምንም እንኳን ልዩነቶች ቢኖሯቸውም የጋራ የሆነ ሃሳብ እንዳላቸው ማስተዋል እንችላለን፡፡ ይህም ፅሁፍ በአንድ ቋንቋ ውስጥ ያሉ ድምፆች ውክልና በመሆን የሚያገለግል መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም ንግግር (ቋንቋ) በአንድ አይነት ዘዴ ወክሎ መልዕክትን በማስተላለፍ የሰው ልጅ መግባቢያ የሆነውን ቋንቋን በማገዝ ተግባቦትን የሚያቀላጥፍ እንደሆነ መረዳት እንችላለን፡፡ ይሁን እንጂ ፅህፈት ሙሉ በሙሉ በአንድ ማህበረሰብ ቋንቋ ውስጥ ያሉትን ድምፆች ሁሉ መወከል ሥለማይችል እና ሁሉም የቋንቋው ተናጋሪ ማህበረሰቦች ፅፈትን የማይችሉ ከሆነ ተግባቦቱ በተወሰኑ እና ዕውቀቱ ባላቸው ሰዎች ብቻ የተገደበ እንዲሆን ግድ ይለዋል፡፡ ፅህፈት ብቻውን ሙሉ በሙሉ የአንድ ማህበረሰብን ንግግር ሙሉ በሙሉ መወከል አለመቻል ብቁ የመግባቢያ ዘዴ ነው ለማለት አያስደፍርም፡፡ ምክንያቱም ንግግር ከድምፅ በተጨማሪ በአካል እንቅስቃሴና በተለያ ቅላፄዎችና ቃናዎች የሚሞላቸው በርካታ የመልዕክት አካላትአሉት፡፡ ሥለዚህ በፅህፈት የተገለፀው መልዕክት ትክክለኛሃሳቡን ሳይለቅ በትክክለኛው መንገድ መልዕክቱን ለማስተላለፍ ከተፈለገ የስርዓተ ነጥቦች ጠቀሜታ ጉልህ መሆኑን ያስረዳል፡፡ David R.olson (2009)::

በአጠቃላይ ስለፅህፈት የተሰጡ የምሁራኑ የጋራሃሳብ የሆነውን "ፅህፈት የንግግር /የቋንቋ/ድምፆች ወካይ ነው" የሚለውን መነሻ ሃሳብ መሠረት በማድረግ ፅህፈት የአንድ ቋንቋ ተናጋሪ ህብረተሰብ የሚነጋገርባቸውን የንግግር ድምፆች ይወክላሉ ተብለው በባለሙያ በተመረጡ የሚታዩ ምልክቶችን በመጠቀም የቋንቋውን ስርዓት ሳናፋልስ መልዕክትን በመፃፍና በመቅረፅ የምናስተላልፍበት ክሂል መሆኑን መግለፅ ይቻላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ፅህፈት የቋንቋን /ንግግር/ ክፍተትን የደፈነ ሁነኛ የመግባቢያ ዘዴ መሆኑም ተጠቁሟል፡፡ ይህ ማለት ቋንቋ /ንግግር/ በጊዜና በቦታ የተገደበ ሲሆን ፅህፈት ግን ይህን ገደብ ተሻጋሪ ሆኖ መገኘቱ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ፅህፈት ምልክታዊና የሚታይ በመሆኑና ሙሉ በሙሉ የንግግር ድምፆችን መወከል ባለመቻሉና አንዳንድ ቋንቋዎች ውስጥ ደግሞ የሚፃፉ ነገር ግን የማይነበቡ ፊደሎች በመኖራቸው እንዲሁም በአካል እንቅስቃሴና በተለያዩ የድምፅ ቃናዎች የሚሞሉ በርካታ የሃሳብ መግለጫ ሁኔታዎች በመኖራቸው ፅህፈት ሙሉ በሙሉ ለብቻው በቂ የተግባቦት አገልግሎት ይሰጣል ማለት አያስችለንም፡፡

#### 2.1.1 የፅህፈት አገልግሎት

ፅህፈት የሰው ልጅ በቋንቋ መጠቀም ከጀመረ እጅግ በጣም ዘግይቶ እንደተጀመረ በብዙ ምሁራን ዘንድ የተገለፀ ነው፡፡ ነገር ግን ከተጀመረ ጀምሮ በልዩ ልዩ ዝግመተ ለውጦች ውስጥ በማለፍ የሰው ልጅ በጊዜና በቦታ ልዩነት ሳቢያ በቋንቋው /ንግግር/ መግለፅ ያልቻለው ሃሳቡን እንዲገልፅና የቋንቋ /የንግግርን/ ክፍተት በመድፈን ግንኙነትን ማጠናከሪያ ሆኖ ሲያገለግል የኖረ እና አሁንም እያገለገለ ያለ ዘዴ ነው፡፡

ፅህፈት ለሰው ልጆች ያበረከታቸው ጥቅሞችን (Peter Damerow 2006) እንደሚከተለው ይገለፀዋል፡፡

ፅሁፍ የአንድን የንግግር ቋንቋና ሃሳቦች ውክልና በተሰጣቸው ፊደሎች በመጠቀም የማህበረሰቡን ማህበራዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ፓለቲካዊ ግንኙነቶችን ቀርፆ በማስቀረት ለመጪው ትውልድ ለማስተላለፍ የሚያገለግለን መሳሪያ መሆኑን ያብራራል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ዕውቀቶችን ከግለሰብ ወደ ግለሰብ ፣ ከአንድ ማህበረሰብ ወደ ሌላ ማህበረሰብ እና ከአንድ ትውልድ ወደ አንድ ትውልድ የምናስተላልፍበት ሁነኛ ዘዴ ነው በማለት ይገልፃል፡፡

ይህ ማለት እንግዲህ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ያሉና በቋንቋ በጊዜና በቦታ ልዩነት ሳቢያ ሊያስተላልፈው ያልተቻላቸውን መልዕክቶች በዘመን ሳይገደብ ተደራሽ በማድረግ መቻሉን አመላካች ነው፡፡ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ያለን ማንኛውንም ማህበራዊ ዕውቀት ሳይሸራረፍ ለቀጣዩ ትውልድ ለማቆየት ፣ እንዲሁም ለሌላው ማህበረሰብ ለማስተላለፍ የፅሁፍ ሚና ከፍተኛ መሆኑን መረዳት እንችላለን፡፡

ፅሁፍ የተፈጠረበት ቃላዊ ግንኙነቶችን ለመተካት ወይም ቋንቋ በጊዜና በቦታ መግለፅ የሚያቅተውን ክፍተት ለመተካት እንደሆነና ዕውቀትን ከትውልድ ወደ ትውልድ ለማስተላለፍ ፣ ባህልንና ዕምነትን ቀርፆ ለማቆየትና ለቀጣዩ ትውልድ ለማውረስ ፣ የማህበረሰቡን ታሪክ ወይም የታሪክ ቅርሶችን በትክክለኛው መንገድ ለማቆየትና ለትውልድ ለማስተላለፍና በአስተዳዳሪውና በተዳዳሪው መሀከል ወይም በማህበረሰቦች መሀከል የተቀላጠፈ ግንኙነት ለመፍጠር በመሆኑ እና ጉልህ ድርሻ እንዳለው Isabel Panosa (2006) ትገልፃለች፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ፅሁፍ የሰው ልጆች የአኗኗር ዘይቤ ለውጥ ውጤት ወይም የስልጣኔ ትሩፋት ሲሆን ጥቅሙም መረጃዎችን ለመሰብሰብ መረጃዎችን ለማደራጀት ፣ መረጃዎችን ለማከማቸትና ለመጠቀም እንዲሁም ለማሰራጨትና የመረጃ ልውውጥን ለማፋጠን እንደሚጠቅመን (David R. Olson 2009)ይገልፃል፡፡

እንግዲህ ከላይ በተለያዩ ፀሀፊዎች እንደተገለፀው ፅህፈት ከቋንቋ /ከንግግር/ መፈጠር በኋላ የተጀመረ ቢሆንም ለሰው ልጆች ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው ዘርዝረዋል፡፡ የፅህፈት አገልግሎት የሰው ልጅ ግንኙነት በጊዜና በቦታ የተገደበ እንዳይሆን ወሳኝ ሚና ያለው ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ዕውቀትን ለማስተላለፍም ትልቁን አስተዋፅኦ ያበረከተ ነው፡፡ ይህም ሲባል ከባህላዊ ዕውቀት ጀምሮ እስከ ዘመናዊ ት/ት መስጫነት የሚያገለግል ነው፡፡ የታሪክ ቅርስን ማስተላለፊያ በመሆኑም ያገለግላል፡፡ መጪው ትውልድ ያልነበረበትን ዘመን ታሪክ ያለ አንዳች መበራረዝ በትክክል ተፅፎ እንዲያገኘው ይረዳዋል፡፡ ሰዎችን በቦታና በጊዜ ርቀት መለያየትምክንያት የሚያጋጥማቸውን አሉታዊ ተፅዕኖም ይቀርፋል፡፡ ፅህፈት ካለ በቀላሉ መገናኘት እንዲችሉ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡ በአሁኑ ወቅትም የመረጃ መረቦች ይህንን ችግር በእጅጉ ቀርፈውት በብዙ ርቀት ልዩነት ያሉ ሰዎች በቀላሉ የፅህፈቱ ዘዴን በመጠቀም መልዕክት ማስተላለፍ እንዲችሉ ሆነዋል፡፡

ሰዎች የተለያዩ የፅህፈት ዘዴዎችን በመጠቀም መረጃዎችን ይለዋወጣሉ፡፡ ለምሳሌ የተለያዩ የደብዳቤ አይነቶችን መጥቀስ እንችላለን፡፡ ደብዳቤዎች እንደየዘመኑ ስልጣኔ የኢንተርኔት አገልግሎቶችንና .... የመሳሰሉትን ሁኔታዎች መሠረት በማድረግ እየተሸሻሉ መጥተዋል፡፡

### 2.1.2 ድብዳቤ

ደብዳቤ ከጥንት ዘመን ጀምሮ አሁን እስካለንበት ዘመን ድረስ በርቀትና በቅርበት ያሉ ተቋማትን ፣ ሀገራትን እና ግለሰቦችን በአቀራራቢነት እና መልዕክት በማስተላለፊያት ሲያገለግል የነበረና እያገለገለ ያለ የግንኙነት መሳሪያ ነው፡፡ የሰው ልጆች ትስስርና ግንኙነት በከፍተኛ ደረጃ እየጨመረና ቀልጣፋ እየሆነከመምጣቱ ባሻገር በተቋማትና በግለሰቦች መሃከል የሚደረጉ ግንኙነቶች በህግ የታሰሩና እየተወሳሰቡ የመጡ መሆናቸውን ጥናቶች ይጠቁማሉ፡፡ በእነዚህ ተቋማትና ግለሰቦች መሀከል የሚደረጉ ግንኙነት በህግ የታሰሩና እየተወሳሰቡ የመጡ መሆናቸውን ጥናቶች ይጠቁማሉ፡፡ በእነዚህ ተቋማትና ግለሰቦች መሀከል ያለን ግንኙነት ህጋዊ መሠረት እንዲኖረውና ዘለቄታዊ መተማመን እንዲሰርፁ ከሚረዱ ነገሮች መሀከል አንዱ ደብዳቤ ነው፡፡ በዚህም የተነሳ በተቋማት መሃከልና በግለሰቦች መሀከል ከጥንት ጀምሮ አሁን ሰለጠነ እስከምንለው ዘመን ድረስ ደብዳቤ ዘመን ያልሻረውና ዓይነቱም እንደ ዘመኑ እየተሻሻለ የመጣ የመገናኛ ዘዴ ነው (Melika Hadavia and Mostafa Morday 2015)፡፡

### 2.1.3 በኢትዮጵያ የደብዳቤ አፃፃፍ አጀማመር

በኢትዮጵያ የደብዳቤ አፃፃፍ አጀማመር ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያው ደብዳቤና ማመልከቻ መቼ እና በማን እንደተፃፈ ትክክለኛውን ጊዜ መግለፅ አስቸጋሪ ነው፡፡ ነገር ግን የተለያዩ ፅሁፎች እንደሚገምቱት በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ደብዳቤም ይሁን ማመልከቻ በ4ተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የኦርቶዶክስ ክርስትና መስፋፋቱን በኋላ መፃፉን ይጠቁማሉ፡፡ በ4ተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የኦርቶዶክስ ክርስትና ከተስፋፋ ተከትሎ የብራና ላይ የዕጅ ፅሁፎች እያደጉ የታዩበት ጊዜ ነበር፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በ4ተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የኦርቶዶክስ ክርስትና ከመስፋፋቱን ፅሁፍ የተጀመረ ቢሆንም ይፃፍ የነበረው ድንጋዮች ላይ ነበር፡፡ ወይም “epigraphic monuments’ writing” ነበር፡፡ ስለዚህ የብራና ላይ የዕጅ ፅሁፎች ማደግና መስፋፋትን ተከትሎ የኢትዮጵያ የደብዳቤ አፃፃፍ አጀማመር ታሪክም አብሮ ተጀመረ (D. Nosnitsin 2012)::

በኢትዮጵያ በተለያየ ዘመናት የተፃፉ ደብዳቤዎች /በጥንት ፣ በመካከለኛውና በአሁኑ ዘመን/ እንደጊዜው ርቀትና ቅርበት፣ እንደተፃፉበት ቀለምና ብራና ወይም ወረቀት ጥራት ከአካባቢ አካባቢ ፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ በማንበብ በጣምአስቸጋሪ ከነበሩና እጅግ ጥቃቅን የአፃፃፍ ስልቶች ካሏቸው እስከ 10mm ፊደላቸው ረጅም ሆነው የተፃፍ ፅሁፎች መኖራቸው ይገለፃል፡፡ ከዚህ ባለፈ እስከ 15ተኛው ክፍለ ዘመን ድረስ ይፃፍ የነበሩት ደብዳቤዎች ፣ ማመልከቻዎችና ሌሎች የዕጅ ፅሁፎች የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀማቸው አሁን ባለንበት ዘመን ያክል ያላደገ ወይም ያልዳበረ ነበር፡፡ በጥንታዊና በመካከለኛው ዘመን የተፃፉ የኢትዮጵያ የብራና ላይ ፅሁፎችና ደብዳቤዎች ከፅሁፉ ውጫዊ ቅርፅ ይልቅ ለመልዕክት ከፍተኛ ትኩረት ያደረጉ ነበር፡፡ በዚህ የተነሳ በሚፅፉበት ጊዜ ከላይ እስከ ታች ጥቅጥቅ የተደረገው የሚፃፉና በደብዳቤው ላይ ከሚገለፀው ሃሳብ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ቅኔዎችንና ምሳሌያዊ አነጋገሮችን መጠቀም የተለመደ ነበር፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በወቅቱ የሚፃፉት ደብዳቤዎችና ማመልከቻዎች ለአምላክ ምስጋና በማቅረብ የሚጀምሩ ነበሩ (Viviane Delpech 2012)፡፡

### 2.1.4 የስራ ደብዳቤ

የስራ ደብዳቤ /መደበኛ ደብዳቤ/ የስራ ደብዳቤ በአብዛኛው ጊዜ ከአንድ ድርጅት ወደ ሌላ ድርጅት ወይም ለድርጅቱ ተገልጋይ ደንበኞች ወይም ከግለሰቦች ለተቋማት የሚፃፍ የደብዳቤ አይነት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የስራ ደብዳቤ

በተቋማትተገልጋዮች እና ደንበኞች ፣ በተቋማቱ አጋሮች እና የተለያዩ ድርሻ ባላቸው አካላት መሀከል የሚደረግ የራሱ የአፃፃፍ ቅርፅ ያለው የደብዳቤአይነት ነው፡፡

የስራ ደብዳቤ በውስጡ ከሚያካትታቸው የደብዳቤ አይነቶች ውስጥ የማሳሰቢያ ደብዳቤ የመጠየቂያ ደብዳቤ የትዕዛዝ ደብዳቤ ፣ የትዕዛዝ መሻሪያ ደብዳቤ ፣ የፍርድ ቤት ደብዳቤ ወዘተ እያልን እጅግ ብዙ የስራ ደብዳቤዎችን መጥቀስ እንችላለን፡፡

የስራ ደብዳቤዎች ዋነኛ ጥቅማቸውን ሲገልፅ መረጃዎችን በተቋማትና ተቋማት መሀከል እንዲሁም በተቋማትና ግለሰቦች መሀከል ህጋዊ በሆነ መልኩ ማድረስ ነው ይላል፡፡

ይህ ማለት እንግዲህ መረጃዎችን በተቋማት መሀከል ተደራሽ ማድረግ ሲባል ለምሳሌ፡- መረጃ ለመጠየቅ ፣ ዕውቅና ለመስጠት ፣ ምስጋና ለማቅረብ የስራ ግንኙነቶችንና ስምምነቶችን ለማድረግ ፣ ትዕዛዝ ለመስጠት.... የመሳሰሉትን መጥቀስ እንችላለን፡፡

**2.1.5 የስራ ደብዳቤ አፃፃፍ ስልት**

የቢሮ ደብዳቤዎችንና ማመልከቻዎችን መፃፍ እራሱን የቻለ ሙያ መሆኑን H.Ding (2007) ይገልፃል፡፡ አንድ ደብዳቤ ችሎታውና ዕውቀቱ በሌለው ሰው ቢፃፍ ጥቃቅን የሚመስሉ ነገር ግን ከፍተኛ ጠቀሜታ ያላቸው ነጥቦች ሊዘነጉ ይችላሉ፡፡ በዚህም የተነሳ ማመልከቻው ወይም ደብዳቤው ፍሬ ነገሩን አቅሙ ዝቅተኛ ይሆናል፡፡ H.Ding (2007)

ማመልከቻም ይሁን የቢሮ ደብዳቤ ወይም ሌላ ፅሁፍ በምንፅፍበት ጊዜ መልዕክቱ ለሚደርሰው አካል ከፍተኛ ትኩረት መስጠት አለብን፡፡ ምክንያቱም በጥንቃቄ የተተየበ ደብዳቤ ፈጣንና ውጤታማ ምላሽ ለማግኘት ቅርብ በመሆኑ ነው፡፡Rigg (1991)::

የደብዳቤ አፃፃፍ ጥበብን በቅጡ መረዳት አሁን ባለንበት ዘመን የሚፃፍ ትምህርታዊ (academic)እና ንግድ የሆኑ ፅሁፎችን ተቀባይነት እንዲያገኙ ማድረግ ያስችለናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የደብዳቤ አፃፃፍ ጥበብ ያለው ሰው የድርሰት ፅሁፎችን በተዋጣለት መንገድ ለመተየብ አስፈላጊው ችሎታ እንዳለው Ashley Crew (2000) ይገልፃል፡፡

አንድ ደብዳቤ ሲፃፍ በውስጡ የሚገለፁት ሀሳቦች በጥንቃቄ መፃፍ ይኖርባቸዋል፡፡ ደብዳቤው ቅርፁን ጠብቆ በመግቢያ ወይም ርዕሰ አሰጣጥ የሀሳብ ትንተና ወይም ሀተታ እና የመዝጊያ ሁኔታ ወይም መደምደሚያ ክፍሎች ሊኖሩት ይገባል፡፡ይህም በደብዳቤው ውስጥ የተገለፀው መልዕክት ለተፈለገው አካል በግልፅ እንዲደርስ ወይም እንዲታይ የሚያደርገው መሆኑን Bergamo (2010) ያብራራል፡፡

Boxu (2012) ደግሞ የቢሮ ደብዳቤ ሲፃፍ በግዴለሽነት የሚታለፍ ጥቃቅን የሚመስሉ ነገሮች ነገር ግን ከፍተኛ ጠቀሜታያላቸው ብሎ የሚዘረዝራቸው ነገሮች አሉ፡፡ ለምሳሌ ደብዳቤው የሚፃፍለትን አካል ስም /ሙሉ ስም/ ወይም የማዕረግ ስም አለመጥቀስ ነው፡፡ ይህም የሚያመጣው አሉታዊ ተፅዕኖ መኖሩን በማራራት ትኩረት ሊሰጥበት የሚገባ ጉዳይ መሆኑን ይገልፃል (Boxu 2012)፡፡

የፍርድ ቤት ደብዳቤዎችን ወይም ማመልከቻዎችን ስንፅፍ የህግ ስርዓቶችን ደንቦችንና አንቀፆችን ክብር በተላበሰ መልኩ መግለፅ መቻል እንዳለብንና ይህ ሳይሆን

ቀርቶ በቸልተኝነት (leniency) የተፃፉ ማመልከቻዎች ትኩረት እንደማይሰጣቸው ያብራራል፡፡ (Marian Mason 2010)::

አንድ የቢሮ ደብዳቤ ሲፃፍ መግቢያ ከሚለው ሃሳብ በፊት ለደብዳቤው ተደራሽ እንዳለው የስልጣን ፣ የትምህርት ወይም የማህበራዊ ውክልና ተዋረድን በሚመጥን መልኩ ርዕብ በመስጠት በመቀጠል ገለፃ እና ትንታኔው ደረጃውን በጠበቀ መልኩ እንዲቀርብና መዝጊያውም ክብር በተሞላበትመልኩ በማሰናበት ፊርማና ማህተም ....መረሳት እንደልለባቸው Aliya Aimoldina and Shopan Zharkyn Bekova (2014)ይገልፃሉ፡፡

ከላይ በተለያዩ ፀሀፊያን እንደተገለፀው ደብደዳቤ የሚፃፍበት ጊዜ በጥንቃቄና ዕውቀቱ ሰዎች ባላቸው መጻፍ እንደሚኖርበት ተብራርቷል፡፡አንድ የስራ ደብዳቤ ሲጻፍ በውስጡ ሊያካትታቸው የሚገባ መሰረታዊ ነጥቦች Sundrive (2006) እንደሚከተለው ገልፆታል፡፡

- ደብዳቤ ሲፃፍ የላኪና የተቀባይ አድራሻ ተገቢ ቦታቸውን ይዘው መፃፍ ይገባቸዋል፡፡ ይህ ማለት የላኪ አድራሻ በስተቀኝ በኩል ከፍ ብሎ የሚፃፍ ሲሆን የተቀባይ አድራሻ ደግሞ ከላኪው አድራሻ ትንሽ ዝቅ ብሎ በስተግራ ጠርዝ በኩል መፃፍ ይኖርበታል፡፡
- ቀን በምንፅፍበት ወቅት በአድራሻዎቹ እና በቀን መካከል በቂ ክፍተት መተዋችንን ማረጋገጥ ይኖርብናል፡፡ ይህም በአድራሻውና በቀኑ መሀከል በቂ ክፍተት አለመኖሩ የደብዳቤውን ቅርፅ ከመበላሸት አልፎ በአንባቢያን ዘንድ መደናገር ሊፈጠር ይችላል፡፡
- ደብዳቤ ስንፅፍ ወሮችን በፊደል መፃፍ ተመራጭ ይሆናል፡፡ ለምሳሌ ሃምሌ 19 ቀን 20011 ዓመተ ምህረት ብለን መፃፍ ያስፈልጋል፡፡ ይህንን የጊዜ ሰሌዳ በቁጥር ብቻ ፅፈን ብናስቀምጠው መደናገርን ሊፈጥር ይችላል፡፡ ምክንያቱም በአንዳንድ ሀገሮች የቀን መቁጣሪያ ቀን መጀመሪያ ላይ ይመጣል፡፡በመጨረሻም ዓመተ ምህረት ሊመጣ ይችላል፡፡ በሌሎች አገራት ደግሞ መጀመሪያ ወር ይመጣል ቀጥሎ ቀን ይመጣልበመጨረሻ አመተ ምህረት ይመጣል፡፡ ስለዚህ ይህንን አይነት መደናገር እንዳይፈጠር ወሮችን ፊደል መፃፍ ተመረጭነት እንዲኖረው ያስችለዋል፡፡
- ደብዳቤ በምንፅፍበት ወቅት እንደ ደብዳቤው አይነት በሚከተሉት ቃላት መጀመር ግድ ይላል፡፡ ለምሳሌ:- ውድ ክቡርነትዎ . ለክቡር ፣ ለአቶ ፣ ለወዘሮ ፣ ለግርማዊነትዎ ፣ ለክቡር ዶክተር፣ ለክቡር ጀነራል ወዘተ ....... መጀመር ይኖሮበታል፡፡ ወይም ደግሞ ደብዳቤው የሚፃፍለት ሰው የመጀመሪያው አንቀፅ በአክብሮት ስያሜ እና ስም መጀምር ይኖርበታል፡፡ በሌላ በኩል የምንፅፈው ለተቋም ወይም ድርጅት ከሆነ የተቋሙን ወይም የድርጅቱን ሙሉ ስም በመጻፍ መጀመር ይኖርብናል፡፡
- ደብዳቤውን ስንፅፍ ከወረቀቱ ከላይ ፣ ከታች ከጎንና ከጎን በቂ ክፍተት መተው መቻል ይኖርብናል፡፡ከዚህም በተጨማሪ ደብዳቤውን በአንቀፅ መክፈልም ያስፈላጋል፡፡ የመጀመሪያው አንቀፅ የሰላምታና ስለ ጉዳዩ መግለጫ ሊሆን ይችላል፡፡ ቀጣዩ አንቀፅ ደግሞ የደብዳቤው ዋና አካል ይሆናል፡፡ ይህ የደብዳቤው ዋና መልዕክት ወይም ፍሬ ሃሳብ በዝርዝር የሚቀርብበት ክፍል ነው፡፡ የመጨረሻው አንቀፅ ማጠቃለያ ወይም መደምደሚያ ሲሆን ይህም የደብዳቤውን የመዝጊ ሃሳብ የምናቀርብበት ክፍል ነው፡፡

- ደብዳቤውን ፅፈን ከጨረስን በኃላ ተገቢውን የመዝጊያ ቃል መጠቀም ይኖርብናል፡፡ በመጨረሻም ፊርማችንን ፈርመን መጨረስ እንችላለን፡፡

አንድ የስራ ደብዳቤ ሲፃፍ የሚከተሉትን ነጥቦች ማሟላት ይኖርበታል፡፡ Aberdeen (2011) እንደሚከተለው ገልፆታል፡-

አድራሻ፡- የስራ ደብዳቤው ከየት ቦታ ለማን እንደተላከ የሚያሳይ መረጃ ነው፡፡ የስራ ደብዳቤ ህጋዊ ቅርፅን በተከተለ መልኩ መፃፍ አለበት፡፡ ለምሳሌ፡- አብዛኛውን ጊዜ የስራ ደብዳቤ ሲፃፍ የላኪው አድራሻ በደብዳቤው በቀኝ ራስጌ በኩል መፃፍ ይኖርበታል፡፡ የተቀባዩ አድራሻደግሞ ዝቅ ብሎ በስተግራ ጠርዝ በኩል ይፃፋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአድራሻው ስር የቦታ ስም ፣ የስልክ ቁጥር ፣ የፖስታ ሳጥን ቁጥር የኢ-ሜል አድራሻ ወዘተ ነጥቦች መካተት ይኖርባቸዋል፡፡

ቀን - ቀን በምንፅፍበት ጊዜ ወሩን በፊደል መፃፍ ተመራጭ ይሆናል፡፡ ለምሳሌ ሀምሌ 19 2001 ዓ.ም በማለት መግለፅ ይኖርብናል፡፡ ይህም በአንዳንድ ሀገራት ካሉ የቀን አፃፃፎች ጋር መደናገር እንዳይፈጠርብን ይረዳናል፡፡

ለምሳሌ በአሜሪካ መጀመሪያ ላይ የሚፃፈው ወር ነው ቀጥሎ ቀን ከዛም ዓመተ ምህረት ይጠቀሳል፡፡በሌላ ሀገራት ደግሞ መጀመሪያ ቀን ከዚያ ወር መጨረሻ አመት መህረት ይፃፋል፡፡ ይህ እንግዲህ ሙሉ በሙሉ በቁጥር የሚገለፅ ከሆነ ሲነበብ እንደየ አካባቢው የተለያየ ጊዜን ጠቃሽ ሊሆን ይችላል፡፡ ስለዚህ ይህንን ችግር ለመቅረፍ መጀመሪያ ወሩን በፊደል ማፃፍ ተመራጭነት ይኖረዋል፡፡

የደብዳቤ ቁጥር የስራ ደብዳቤ በምንፅፍበት ወቅት ሌላኛውን ወሳኝ ነጥብ የደብዳቤው ቁጥር ነው፡፡ የደብዳቤ ቁጥር ለአንድ ምላሽ ለሚያስፈልገው የስራ ደብዳቤ ቁጥሩን ጠቅሰን ምላሽ ለመስጠት ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በስራ ምክንያት የወጡ /የተፃፉ/ እናየገቡ /የተላኩልንን/ ደብዳቤዎች በቅድመ ተከተል ለማስቀመጥና በፈለግናቸው ሰዓት ለመጠቀም የደብዳቤ ቁጥር ጠቃሜታ የጉላ ነው፡፡

ሰላምታ፡- በስራ ደብዳቤ አፃፃፍ ላይ ሌላኛው ጠቃሚ ነጥብ ሰላምታ ነው፡፡ በስራ ደብዳቤ ላይ ፅሀፊው ለሚፃፍበት አካል በሚመጥን መልኩ ከተገቢው ማዕረግ ጋር ሰላምታ ማቅረብ አለበት፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ደብዳቤ ተፅፎ ካበቃ በኋላ “ከሰላምታ ጋር” “ከአክብሮት ጋር” ወዘተ ቃላትን በመጠቀም መቋጨት ያስፈልጋል፡፡

ጉዳይ /ርዕስ/፡- ይህ ነጥብ በስራ ደብዳቤ ላይ መዘንጋት የሌለበት ሌላኛው ጉዳይ ነው፡፡ የስራ ደብዳቤ ጉዳይ /ርዕስ/ ከስሩ ተሰምሮበትና ጎላ ተደርጎ መፃፍ ይኖርበታል ይህም ደብዳቤው የተፃፈው ለምን አላማ እንደሆነ የሚያመለክተንነው

ግልባጭ፡- አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለባለድርሻ አካላት ግልባጭ ይኖረዋል፡፡ ይህም በደብዳቤው መጨረሻ ላይ የሚፃፍ ነው፡፡

የደብዳቤው ዋና አካል፡ -ይህ የስራ ደብዳቤ ዋና አካል ብለን የምንጠራው የደብዳቤ አካል እንደምንፅፈው የስራ ደብዳቤ አይነት እና ይዘት ሊለያይ ይችላል፡፡ ለምሳሌ፡- ከአንድ ተቋ ወይም ደንበኛ ለተፃፈ ደብዳቤ መልስ የምንሰጥ ከሆነ በቅድሚያ መልስ የምንሰጥበት ያሰብነውን ደብዳቤ ቁጥር ፣ የደብዳቤ አይነት የደብዳቤ ርዕስ ወዘተ ቀድመን መጥቀስ ይኖርብናል፡፡ በዚህ መሰረት እንደ ምንፅፈው የደብዳቤ አይነት ፣ ሁኔታና ሀሳብ የደብዳቤው ዋና አካል ይዘት የተለያየ ሊሆን ይችላል፡፡

ማጠቃለያ፡- ይህ በደብዳቤው ዋና አካል ላይ የተጠቀሱትን በተመጠኑ ቃላት በዐጭሩ የምንገልፅበትና መልካም ምኞታችንን የምንገልጥበት የደብዳቤ አካል ነው፡፡

ፊርማና መሀተም፡- በአንድ የስራ ደብዳቤ ላይ ከፍተኛ ቦታ ላይ ካላቸውና መዘንጋት ከሌለባቸው ነጥቦች መሀከል ፊርማ እና መሀተም ተጠቃሾች ናቸው፡፡ ፊርማና ማህተም የደብዳቤውንህጋዊነት ለማረጋገጥና መተማመን ለመጨመር ጠቀሜታቸው የጎላ ነው፡፡

የመስሪያ ቤት አርማ (logo)፡- ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የሚፃፍ የመስሪያ ቤት ደብዳቤዎች የራስጌ ማህተምም ከመጠቀም ይልቅ የመስሪያ ቤቱ አርማ (logo) መጠቀም ይመረጣሉ፡፡ ነገር ግን አርማ ከሌላቸው የራስጌ ማህተም መጠቀም ይገደዳሉ ቀደም ባሉ ዘመናት የተፃፉ ደብዳቤዎችን በምንመረምርበት ጊዜ ግን ሙሉ በሙሉ የራሴጌ ማህተም ተጠቃሚዎች ነበሩ፡፡

### 2.1.6 የደብዳቤ አይነቶች

የደብዳቤ አይነቶችን መደበኛና ኢ-መደበኛ የደብዳቤ አይነቶች ለማለት በሁለት ከፍለን እንመለከታቸዋለን፡፡

#### *2.1.6.1 መደበኛ የደብዳቤ አይነቶች*

መደበኛ ደብዳቤዎች ከኢ-መደበኛ ደብዳቤዎች ይለያሉ ምክንያቱም በቢሮ ውስጥ የሚደርጉ ህጋዊ የስራ እንቅስቃሴዎችን ለማስኬድ ስለሚያገለግሉ እና ህጋዊ የሆነ የራሳቸው የአፃፃፍ መስፈርት ሥላላቸው ነው፡፡

ማንኛውም ሰው አንድ ደብዳቤ በሚፅፍበት ጊዜ መጀመሪያ ልብ ሊላቸው እና ሊያጤናቸው ከሚገቡ ነገሮች መካከል ደብዳቤው የሚፃፍበት ዘዴ /style/ እና በደብዳቤው ውስጣዊ እና ውጫዊ ይዘት ናቸው፡፡ በዚሁ መሰረት የተለያዩ መደበኛ የስራ ደብዳቤ አይነቶች እንዳሉ ይታመናል፡፡ ከነዚህም መካከል በከፊል፡-የማሳሰቢያ ደብዳቤ ፣ የምስጋና ደብዳቤ የመጠየቂያ ደብዳቤ ፣ የትዕዛዝ ደብዳቤ ከስራ የማባረሪያ ደብዳቤ ፣ ከስራ የመልቀቂያ ደብዳቤ ፣ የፍርድ ቤት ክስ ደብዳቤ ፣ የትዕዛዝ መሻሪያ ደብዳቤ ወዘተ ይገኙበታል፡፡ እነዚህን ደብዳቤዎች ሥንፅፍ በመደበኛነት ልንከተላቸው የሚገቡ ነጥቦች አሉ በዚሁ መሰረት ከውጫዊ ይዘት አኳያ እንዲነበቡ ማድረግ ፣ ቀን እና አድራሻ ማስቀመጥ ፣ መሀተም እና ፊርማ አለመርሳት ወዘተ የሚሉት ይገኙበታል፡፡ ከውስጣዊ ይዘት አኳያ የደብዳቤዎች መግቢያ ፣ ሀተታ እና መደምደሚያ በምክንያት ላይ የተመረኮዘ ሊሆን ይገባል፡፡ ከዚህ ባለፈ ደብዳቤዎቹ ለተደራሹ አካል በማይገቡ ሞያዊ ቃላት የተጨናነቁ መሆን የለባቸውም፡፡ በዚሁ መሰረት የተወሰኑ የመደበኛ ደብዳቤ አፃፃፎችን በምሳሌነት እንደሚከተለው እንመልከት፡-

**2.1.6.1.1. ከስራ የማሰናበቻ ደብዳቤ** (Employment termination letter)

አንድን ሰራተኛ ከሚሰራበት ተቋም ህጋዊ በሆነ መልኩ ከማሰናበቻ ዘዴዎች አንዱ ህጋዊ ደብዳቤ መፃፍ ነው፡፡ በዚሁ መሰረት አንድ የድርጅት መሪ አንድን ሰራተኛ በሚያባርርበት (በሚያሰናብትበት) ወቅት ለደብዳቤው ቀን ፣ ቁጥር ፣ ርዕሰ ጉዳይ ፊርማ ፣ ማህተም ወዘተ የሚባሉት የመደበኛ ደብዳቤ መሰረታዊ ነጥቦች መሟላት አለባቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ፀሀፊው ለተሰናባቹ ሰራተኛ የተሰናበተበትን ምክንያት ግልፅ እና በማያሻማቋንቋ እና አገላለፅ ማብራራት ይኖርበታል፡፡ በደብዳቤው ላይ ከስራ እንዲባረር

የተወሰነበት ሰራተኛ በተወሰነ የጊዜ ርዝመት ለተፃፈበት ደብዳቤ በፅሁፍ መልስእንዲያቀርብ መፍቀድ አለበት፡፡ ፀሀፊው በሚፅፍበት ወቅት በተቻለ መጠን የተሰናባቹንሰራተኛ ሞራል በማይጎዳ እና በዲፕሎማሲያዊ አገላለፅ መልዕክቱን ማሥተላለፍ ይኖርበታል፡፡ ይህም በተሳናባቹ ሥነ ልቦና ሰውስጥ በተወሰነ መልክም ቢሆን ቀና(posive)ምልክታን ለማዳበር እና ተሰናባቹን ጥፋቱ የኔ ነው ወደፊት እንደዚህ አላደርግም በማለት ከጥፋቱ እንዲመከር ስለሚረዳ ነው፡፡

### 1.1.6.1.2. የቅጣት ማስጠንቀቂያ ደብዳቤ (warnig letter)

ይህ የደብዳቤ አይነት በውስጣዊ ይዘቱ ከስራ ማሰናበቻ ደብዳቤ ጋር በተወሰነ መልኩ ይቀራረባል፡፡ በአንድ ተቋም ውስጥ አንድ ሰራተኛ ጥፋት አጥፎቶ ሲገኝ ቅደም ተከተሉን ጠብቆ የፅሁፍ ማሥጠንቀቂያ የሚሰጠው ከሆነ ማስጠንቀቂያውን የሚፅፈው ሰው ለምን የማስጠንቀቂያ ደብዳቤው እንደተፃፉ ማስጠንቀቂው የተፃፈበትን ግለሰብ በሚያሳምን መልኩ ከምክንያት በመነጨ እና በማስረጃ በተደገፈ አገላላፁ ሊገለፅለት ይገባል፡፡በገለፃው ወቅትጸሀፊው የቃላት አጠቃቀሙን ከአሽናፊነት ይልቅ ዲሎማሲያዊ የሆኑ ቃላትን በመጠቀም ከ "እኔ" አገላለፅ ይልቅ ተቋማዊ ይዘት ያላቸውን አገላለፆች በመጠቀም አጥፊው በስራው ጥፋት እንዲፀፀት በሚያደርገው መልኩ የሰራው ጥፋት በተቋሙ ላይ ያደረሰውን ችግር በመግለፅ ሊፅፍለት ይገባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አጥፊው ጠንካራ ጎን ካለው በተወሰነ መልኩ ለደብዳቤው መንደርደሪያነት ወይም ደብዳቤው ውስጥ ለተነሱት ሀሳቦች ማጣቀሻነት ቢውሉ የተቀጣውን ሞራል በመጠበቅ በቅጣቱ እንዲፀፀት ሊያደርገው ይችላል፡፡ በዚህ የተነሳ የቅጣት ደብዳቤ በሚፃፍበት ጊዜ ከቀን ፣ የደብዳቤ ቁጥር ማህተም ፣ ፊርማ ዕርዕሰ ጉዳይ ባለፈ ከላይ የቀረቡት ነጥቦች ከግምት መግባት ይኖርባቸዋል፡፡

### 2.1.6.1.3 የምስጋና ደብዳቤ (Thank you letter)

በተለያዩ ተቋማት እና ግለሰቦች በስፋት ከሚሥተዋሉበት መደበኛ ደብዳቤ አይነቶች አንዱ የምስጋና ደብዳቤ ነው፡፡

የምስጋና ደብዳቤ ልክ እንደማንኛውም ደብዳቤ ቀን ፣ የደብዳቤ ቁጥር፣ ፊርማ ፣ ርዕስ መሀተም ወዘተ በላይ ላይ ሊኖሩት ይገባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ግልጽ በሆነ ቋንቋ ለምን ምስጋናው እንደተሰጠ ምክንያታዊ በሆነ መልኩ ሊገለፅ ይገባዋል፡፡ ይህ ደብዳቤ ከአንድ ተቋም ለሌላ ተቋም ወይም ከተቋም ለግለሰብ ወይም ለግለሰብ ለተቋም ሊፃፍ ይችላል፡፡ ይህ የደብዳቤ አይነት በአንድ አካል ወይም ተቋም ለተሰራ ሥራ ህጋዊ እውቅና እና ምስጋና ለማቅረብ የሚረዳ መደበኛ ደብዳቤ አይነት ነው፡፡

### 2.1.6.1.4 መሥማማትን የመግለጫ ደብዳቤ(acceptact letter)

ይህ የደብዳቤ አይነት ልክ ሌሎች የስራ ደብዳቤዎችመያዝ ያለባቸውን እንደ ፊርማ ቀን ቁጥር አድራሻ ወዘተ የደብዳቤዉንውጫዊ ይዘት ማሟላታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ አሁንም በምክንያት ላይ የተመሰረተ እና ግልፅ የሆነ ቋንቋ በመጠቀም ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ እነዚህ የደብዳቤ አይነቶች ለአንድ ቀድሞ ለተነሳ ሀሳብ እውቅና የመስጠት እና ተቀባይነቱን ለማረጋገጥ የሚፃፉ አይነት ደብደቤዎች ናቸው፡፡ በሚፃፉበት ወቅትም ከመጠን ያለፈ እና አገላለፁ ድምቀቱ ገደቡን እንዳይለቅ መመጠን ያስፈልጋል፡፡

### 2.1.6.1.5 ከስራ የመልቀቂያ ደብዳቤ(withdrawal letter)

ይህ የደብዳቤ አይነት አንድ ግለሰብ በአንድ ተቋም ወይም ማህበራት አገልግሎት የወሰደውን ሀላፊነት ህጋዊ በሆነ መንገድ ለመልቀቅ የሚፃፉ የደብዳቤ አይነት ነው፡፡ አንድ የማህበረሰብን ወይም የተቋምን ሀላፊነት ወስዶ በማገልገል ላይ ያለ ግለሰብ ሀላፊነቱን በሚለቅበት ጊዜ ዝም ብሎ እሱ ሥለፈለገ ብቻ መልቀቅ አይችልም፡፡ በአንጻሩ በተሰየመበት ቦታ እያገለገለ ሥራውን

መልቀቅ መፈለጉን ከምክንያታ ጋር አስደግፎ በዛ ቦታ ለሾመው ወይም ለቀጥረው አካል ህጋዊ በሆነ መልቀቂያ ደብዳቤ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡ በገለጸው ወቅትም በቦታው እና በተቋሙ ውስጥ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ ግልፅ እና ዲፕሎማሲያዊ በሆነ አገላለፅ መገለፅ ይኖርበታል፡፡ ደብዳቤውንም በምስጋና እና በሰላምታ መደምደም ይኖርበታል፡፡ (R. Adam 2006)

2.1.6.1.6 **የትዕዛዝ መስጫ ደብዳቤ**

ይህ ደብዳቤ አይነት ከአንድ ግለሰብ ለድርጅት ወይ ከድርጅት ለግለሰብ ወይም ከድርጅት ለድርጅት ሊፃፍ የሚችል የደብዳቤ አይነት ሲሆን ፀሀፊው ወይም ትዕዛዝ ሰጭው ሥለ ትዕዛዙ በቂ የሆነ እና የማያሻማ መግለጫ ግልፅ በሆነ ቋንቋ ማስተላለፍ መቻል አለበት፡፡ ለምሳሌ ትዕዛዙ በቁጥር ወይም በመጠን ከሆነ መጠኑን እና ቁጥሩን መግለፅመቻል አለበት፡፡ ምክንያቱም እንደዛ የማያደርግ ከሆነ ለትዕዛዙ በቂ ምላሽ ወይም የተሳሳተ ምላሽ ሊያገኝ ሥለሚችል ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ትዕዛዙን የያዘው ደብዳቤ በመጠን እና በቁጥር የማይገለፀ ከሆነ ስለ ጉዳዩ አካሄድ በቂ የሆነ ማብራሪያ መስጠት ይኖርበታል፡፡ ከዚህ ባለፈ ቀን ፣ ቁጥር ፣ የላኪ እና የተቀባይ አድራሻ ፣ ማህተም ፣ ፊርማ ፣ ተገቢውን ሰላምታ ወዘተ ማካተት ይኖርበታል (R. Adam 2006)

***2.1.6.2 በወዳጅ ዘመድ መሀከል የሚጻፉ ደብዳቤዎች***

እንደነዚህ ደብዳቤዎች በወዳጅ ዘመድ መሀከል የሚጻፉ ደብዳቤዎች ሲሆኑ የራሳቸው ውስጣዊ ቅርፅ ያላቸው ናቸው፡፡ ይህም በመግቢያ (ሰላምታ) ፣ ሀተታ እና መደምደሚያ ተከፍለው የሚጻፉ ሲሆኑ እንደመደበኛ ደብዳቤዎች ቁጥር ፣ ጉዳይ (ርዕስ) ፣ ማህተም እና ወዘተ የመሳሰሉት ነጥቦችን የሚያካትቱ ናቸው፡፡

## 2.2 የጥልቅ ዲስኩር ትንተና ዘዴ (CDA)

በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ባህላዊ ግንኙነቶችን እና ቁርኝቶችን ለማሳለጥ ቃላዊ እና ፅሁፋዊ የግንኙነት ዘውጐችን መከተል ግድ ይላል፡፡ እርግጥ ነው በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የሚደረጉትን ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ወዘተ ግንኙነቶች ከቃላት ይልቅ በፅሁፍ ላይ ተመርኩዞ መከወን የጉዳዩ ህጋዊ ተቀባይነት እና ተአማኒነቱን ከፍ ስለሚያደርገው መሰል ግንኙነቶችን በአብዛኛው ጊዜ ሰዎች በፅሁፍ መከወንን ይመርጣሉ፡፡ ከነዚህ በፅሁፍ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ እና ባህላዊ ግንኑነትከምንፈፀምባቸው ዘዴዎች አንዱ የስራ ደብዳቤ ነው፡፡ የስራ ደብዳቤ በተለያዩ ቦታዎች እና ሀገራትወይም በተለያዩ ተቋማት ከዛም ሲያልፍ በተቋማት እና በግለሰቦች መካከል ያለን የግንኙነት ቀለበት ህጋዊ መሰረትን በተላበሰ አኳሁዋን የምናስኬድበት የግንኙነት አይነትነው፡፡ በዚህ የተነሳ ከጊዜ ወደ ጊዜ ተቋማት፣ ሀገራት፣ ግለሰቦች ወዘተ የተለያየ ይዘት ያላቸውን ደብዳቤዎች በመጠቀም ልዩ ልዩ ግንኙነቶችን መመስረት ችለዋል፡፡ Bo xu, (2012)፡፡

የስራ ደብዳቤ ማለት ከአንድ ግለሰብ ወደ ሌላ ግለሰብ፣ ከአንድ ተቋም ወደ ሌላ ተቋም ወይም ከተቋም ወደ ግለሰብ ወይም ከግለሰብ ወደ ተቋም የሚፃፉ የራሱ የሆነ የአፃፃፍ ስልት ያለው፣ የራሱ የሆነቅርፅ ያለው፣ የራሱንየዲስኩርስ ዘዴ የሚከተል ለተፈለገው አካል /ለተደራሹ/ በተፈለገው መልኩ መረጃ ለማስተላለፍ ወይም መተማመን ለመፍጠር ወይም መነቃቃት እና መነሳሳት ለመፍጠር የምንገለገልበት የግንኙነት ማስኬጃ መንገድ ነው፡፡ (Ashley Cerku, 2005)፡፡

የሰው ልጆች የእርስ በእርስ የትስስር አለም እየሰፋ እና እየጨመረ በሄደ ጊዜ በመካከላቸው የተፈጠረው ግንኙነት የበለጠ እየተወሳሰበ እና ጥብቅ እየሆነ መጥቷል፡፡ የስራ ደብዳቤዎች እንደ አንድ የግንኙነት መፍጠሪያ ወይም መመስረቻ መንገድ መፃፍ እና ማንበብ መስፋፋት ከጀመረበት ዘመን ጀምሮ ፊደል በቆጠረው የማህበረሰብ ክፍል ጠቃሚ እና ተአማኒነት ያለው ወሳኝ የግንኙነት መመስረቻ ዘዴ ሆኖ በማገልገል ላይ ይገኛል፡፡ ዛሬ ከቴክኖሎጂ እድገት ጋር ተያይዞ የሉላዊነት (globalization) መስፋፋት የስራ ደብዳቤ በተለያዩ የማህበራዊ ሚዲያዎች እና በኢ-ሜይል ተፅዕኖ ስር የወደቀ ቢመስልም ቅሉ አሁንም ቢሆን ግለሰቦች፣ ድርጅቶች እና ሀገራት ወሳኝ የሚሏቸውን ግንኙነቶች የስራ ደብዳቤ በመፃፍ እንደሚገናኙ በተለያዩ ጊዜያት የተሰሩ ምርምሮች ያሳያሉ፡፡ እንደ ምርምሮቹ ገለፃ የስራ ደብዳቤን በኢ-ሜይል ወይም በሌላ የማህበራዊ ድረ-ገፆች መጠቀም ተመራጭ እንዳይሆን ካደረጉት ምክንያቶች አንድ በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ በሚደረጉት የደብዳቤ ልውውጦች መሀተም፣ ፊርማ፣ ግልባጭ ወዘተ ነጥቦችን ማካተት አስቸጋሪ መሆኑን በመግለፅ ያብራራሉ፡፡ የነዚህ ነጥቦች አለመኖር ደግሞ የተፃፈውንየስራ ደብዳቤ ህጋዊ ተቀባይነት ይቀንሰዋል፡፡ በዚህ የተነሳ ዛሬም ድረስ ግለሰቦች፣ተቋማት፣ ሀገራት ወዘተ የስራ ደብዳቤ ልውውጦችን በሶሻል ሚዲያ እና በኢ-ሚል ከማድረግ ይልቅ በወረቀት ማድረግን ይመርጣሉ፡፡ (Melika Hadari 2015)::

ከዚህ ባለፈ በአንድ ድርጀት ውስት ወጪ እና ገቢ የሚደረጉ የስራ ደብዳቤዎችን የአስተዳደር መዋቅሩን ሚና ተዋረድን በጠበቀ መልኩ ገቢ እና ወጭ ለማድረግ በኢ-ሜል ወይም በሌላ የማህበራዊ የትስስር መፍጠሪያ ሚዲያዎች አስቸጋሪ ስለሚሆን በወረቀት ላይ የተተየበ የስራ ደብዳቤ ልውውጥ ተመራጭነቱ የጐላ ነው (Melika Hadavi 2015)::

በሌላ በኩል Ding የተባለ ፀሀፊ እንደሚተነትነው የስራ ደብዳቤን መፃፍ እራሱን የቻለ ስራ ነው፡፡ በመሆኑም አንድን የስራ ደብዳቤ ለመፃፍ ዝም ብሎ ማንበብ እና መፃፍ መቻል በቂ አይደለም፡፡ ምክንያቱም የስራ ደብዳቤ ለመፃፍ ከማንበብ እና መፃፍ ባሻገር ዲስከርስ ስለሚደረገው ጉዳይ ወይም ማህበረሰብ በቂ እውቀት ሊኖር ይገባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ስለሚፃፈው የስራ ደብዳቤ አይነት እና ለምንፅፈው የስራ ደብዳቤበቂ ግንዛቤ ሊኖረን ይገባል፡፡ ከዚህ አለፍ ሲልም ፀሀፊው የአንባቢዉን ወይም የኦዲየንሱን የግንዛቤ፣ የትምህርት፣ የሞያ ወዘተ ሁኔታ ከግምት ማስገባት ይኖርበታል፡፡ ለምሳሌ አንድ የሂሳብ ባለሞያ ለአንድ መሀንዲስ የስራ ደብዳቤ በሚፅፍበት ወቅት ለመሀንዲሱ አዲስ የሆኑ እና ለመረዳት አስቸጋሪ የሆኑ ሞያዊ ቃላቶችን እየተጠቀመ የሚፅፍ ከሆነ ለመግባባት እና ግንኙነት ለመፍጠር አስቸጋሪ ስለሚሆን የስራ ደብዳቤው የተፈለገለትን ግብ ሳይመታ የቀራል (H. Ding, 2007)::

Rigg የተባለ ፀሀፊ እንደዚሁ አንድ ፀሀፊ ወይም ተናጋሪ በሚፅፍበት ወይም በሚናገርበት ጊዜ የኦዲየንሱን ወይም መልዕክቱ እንዲደርሳቸው የታሰበውን አካል ነባራዊ ሁኔታ ከግምት ማስገባት ይኖርበታል ይላል፡፡ ምክንያቱም የስራ ደብዳቤ ዲስኩር ዋና አላማ ለመልዕክት ተቀባዩ አካል መልዕክትን በአግባቡ ማስተላለፍ ስለሆነ ነው፡፡ P.Rigg, (1991)::በዚህ መሠረት አንድ የስራ ደብዳቤ በሚፃፍበት ወቅት የሚፃፍበት ግብ (purpose) የደብዳቤውን ውስጣዊ የይዘት ቅኝት ለግቡ በሚመጥን መልኩ እንድንቃኝ ያደርገናል፡፡ በዚህ የተነሳ አንድ የስራ ደብዳቤ ፀሀፊ በሚፅፍበት ወቅት ደጋግሞ የደብዳቤውን ግብ ማስታወስ እና የደብዳቤውን ውስጣዊ የይዘት ቅኝት በዚህ መልኩ እንዲቃኝ መደራጀት አለበት፡፡

በሌላ በኩል በዚህ ጥናት ውስጥ በግብአትነት የሚያገለግሉትን የስራ ደብዳቤዎች ውስጣዊ ይዘት እና ከፊደላቱ ጀርባ የመሸጉትን ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ሀይማኖታዊ አና ባህላዊ መልዕክቶች እና ሚስጥራት ለማግኘት ከምንጠቀመባቸው ዘዴዎች

መካከል አንድ የጥልቅ ዲስኩር ትንተና ዘዴ አንዱ ይሆናል፡፡ የጥልቅ ዲስኩር ትንተና ዘዴ (CDA) በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የተከሰቱ ክስተቶችን የሚመረምር፣ የሚተነትን ከመሆን ባለፈ በትንተናው ወቅት የርዕዮተ አለም፣ የባህል፣ የፖለቲካ፣ ኢኮኖሚ፣ የስልጣን ወዘተ ቅርፆች፣ ግንኙነቶች እና ሂደቶች (Processess) በምን፣ ለምን እና እንዴት ተፅኖ እንዳላቸው የሚያመላክተን የትንተና አይነት ነው (FairClough 1992)::

የጥልቅ ዲስኩር ትንተና ዘዴን (CDA) ከሌላ የትንተና ዘዴዎች የሚለየው «ጥልቅ» በመሆኑ ነው፡፡ በዚሁ መሠረት ጥልቅ (critical) የሚለው የሚያሳየወ በትንተናው ወቅት ድብቅ የሆኑ ምክንያቶችን እና ቁርኝቶችን የሚመረምር በመሆኑ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የጥልቅ ዲስኩር የትንተና ዘዴ (CDA) በአንድ ፅሁፍ ውስጥ የሰፈሩ፣ ሀረጋት እና አረፍተ ነገሮች በምን መልኩ እንደተደራጁ ለምን እና እንዴት በዛ መልኩ እንደተደራጁ እና እንድምታቸው ምን እንደሆነ የምንመረምርበት መንገድ ነው (Andrew Atkins, 2002):: Fairclough የተባለ ፀሀፊን በመጥቀስ Andrew የተባለ ፀሀፊ እንደገለፀው የትንተና ዘዴ ሶስት ደረጃዎች እንዳሉት ያትታል፡፡ የመጀመሪያው ደረጃ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ያሉ ነባራዊ ሁኔታዎች በምንፅፈው ፅሁፍ ላይ ምን አይነት ተፅዕኖ እንደለው ያትታል፡፡ ሁለተኛው ደረጃ አንደ ፅሁፉ የተፃፈበት መንገድ በፅሁፉ ትንተና እና ትርጉም ላይ ተፅዕኖ አለው፡፡ ሶስተኛው ደረጃ ከላይ የተጠቀሱት የሁለቱ ደረጃዎች ውጤት የሆነው እራሱ ፅሁፉ ነው፡፡ (Andrew, 2002):: ከዚህ በተጨማሪ አንድ ተንታኝ ትንተና በሚያደርግበት ወቅት የሚከተሉትን መሰረታዊ ጥያቄዎች መጠየቅ ይጠበቅበታል፡-

1. በሚተነተነው ፅሁፍ ውስጥ የሰፈሩት ቃላት ከተፃፉበት ክስተት እና ሁኔታ አኳያ ምን አይነት እንድምታ እንዳላቸው መጠየቅ፡፡ ይህ ማለት በፅሁፉ ውስጥ የሰፈሩት ቃላትን በጥልቀት በመመርመር የቃላቱን «ቶን» (tone) በመመርመር ከጀርባቸው ያለውን መልዕክት መረዳት ማለት ነው፡፡
2. በሚተነተነው ፅሁፍ ውስጥ ያሉት ቃላት እርስ በእርስ ያላቸው ግንኙነት ምንድነው? ብለን መመርመር ለትንተናው ስኬታማነት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው፡፡ ይህ ማለት ለምሳሌ በፅሁፉ ውስጥ የመደበኛ «ፎርማል» እና የኢ-መደበኛ «ኢንፎርማል» ቃላት አጠቃቀም ምን እንደሚመስል መመርመር እና በተዘዋዋሪ መልኩ ወይም ከጀርባቸው ሚስጢር ያዘሉ ቃላት ወይም አገላለፆች ካሉ መመርመርን ያካትታለ፡፡
3. በሚተነተነው ፅሁፍ ውስጥ ያሉት ቃላት፣ ሀረጋት እና አረፍተ ነገሮች በሚያብራሩት ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ምን ያህል የገላጭነት እና መልዕክት ተሸካሚነት ሚና ተጫውተዋል? የሚለውን ጥያቄ በመጠየቅ የቃላቱን፣ የሀረጉቹን እና አ/ነገሮቹን የገላጭነት እና መልዕክት አስተላላፊነት ሚና መገምገም፡፡
4. በሚተነትነው ፅሁፍ ውስጥ የተፃፉ ምሳሌያዊ አነጋገሮች (metraphors) ካሉ የተገለፁት ምሳሌያዊ አነጋገሮች ከተገለፁበት ሁኔታ አኳያ ምን አይነት መልዕክት እንደያዙ መጠየቅ፡፡ ምሳሌያዊ ንግግሮቹ ከጀርባቸው ያለውን ሚስጢር መመርመር ፅሁፍን በምንመረምርበት ወቅት ወሳኝ ሚና አለው፡፡
5. አንድን ፅሁፍ በምንተነትንበት ጊዜ ሌላኛው መጠየቅ ያለብን ወሳኝ ነጥብ በፅሁፉ ውስጥ ያለውን የሰዋሰው አጠቃቀም ሁኔታ ነው፡፡ ይህ ማለት በፅሁፉ ውስጥ የሰዋሰው አጠቃቀሙ የፁሁፉን መልዕክት ለማደባበስ ወይም መጉላት ያለበትን ነጥብ ለማደብዘዝ እና መደብዘዝ ያለበትን ነጥብ እንዲጐላ በማድረግ የተሳሳተ መልዕክት እና ግንዛቤ እንዲኖር ለማድረግ መሞከሩንእና አለመሞከሩን መመርመር ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ የ "passive" እና

"active" አ/ነገሮች በፅሁፉ ውስጥ በምን መልኩ እንደተደራጁ መመርመር፡፡ ከዚህ ባለፈ በፅሁፉ ውስጥ አወንታዊ እና አሉታዊ አረፍተ ነገሮች በምን መልኩ እንደተዋቀሩ መመርመር፡፡

6. በትንተና ወቅት ሌላኛው ትኩረት ለንሰጠው የሚገባው ነጥብ በሰዋሰው አጠቃቀም ወቅት እኛ፣ አንተ ወዘተ ተውላጠ ስሞች በፅሁፉ ውስጥ ያሉ ቀላል እና ውስብስብ (Complpx sentences) አ/ነገሮች በምን መልኩ እንደተዋቀሩ መጠየቅ ይገባል፡፡ ከዚህ ባለፈ በእነዚህ አረፍተነገሮች መካከል ያለውን ስልታዊ ቁርኝት መመርመር ይገባል፡፡
7. በትንተና ወቅት በፅሁፉ ውስጥ ያሉ ቀላል እና ውስብስብ (Complex Sentences) አ/ነገሮች በምን መልኩ እንደተዋቀሩ መጠቅ ይገባል፡፡ ከዚህ ባለፈ በእነዚህ አረፍተ ነገሮች መካከል ያለውን ስልታዊ ቁርኝት መመርመር ይገባል፡፡
8. በፅሁፍ ትንተና ወቅት ትኩረት ልንሰጣቸው ከሚገቡ ነገሮች መካከል ሌላኛው በፅሁፍ ውስጥ ሚና ያላቸው አካላት በፅሁፉ ውስጥ የተሰጣቸው ቦታ፣ ተፅኖ ፈጣሪነት፣ እና ወዘተ ነጥቦች ናቸው (N. Fairclough, 1989)::

በሌላ በኩል አንድን ደብዳቤ በምንተነትንበት ጊዜ የደብዳቤውን ግብ (Purpase) መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ምክንያቱም የደብዳቤው ግብ በደብዳቤው ውስጣዊ ይዘት ላይ የራሱ የሆነ ተፅዕኖ ስላለው ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአንድ ደብዳቤ ውስጥ የደብዳቤውን ግብ (purpose) መረዳት በትንተና ወቅት የደብዳቤውን ሂደት (Process) የሚለውን እና ከሂደቱ (Process) ጀርባ የተመሰጠረ ነገር መኖሩን ለመረዳት ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የአንዳንድ ደብዳቤ ሂደት (process) በምንመረምርበት እና በምንተነትንበት ወቅት የተደጋገሙ ቃላት እና አገላለፆችን በአትኩሮት መመልከት ያስፈልጋል፡፡ ምክንያቱም ፀሀፊው እነዚያን ቃላት የተጠቀመው ወይ ተፈላጊውን ጉዳይ ለመመስጠር በማሰብ ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህ የተነሳ አንድ ደብዳቤ ተንታኝ በትንተና ወቅት የደብዳቤውንግብእና ሂደት በደብዳቤው ውስጥ ካለው ፅሁፍ፣ ከደብዳቤው አይነት፣ ሀሳብ አወቃቀር፣ ከደብዳቤው ቶን ወዘተ አኳያ ምልከታውን ሰፋ በማድረግ መመልከት ይኖርበታል፡፡ በሌላ በኩል አንድን ደብዳቤ በምንተነትንበት ጊዜ እንደ ደብዳቤው ሁኔታ እና አቀራረብ የመተጣጠፍ (fletabiliy) ባህሪ ማዳበር ይኖርብናል፡፡ ምክንያቱም አንድ ደብዳቤ እንደ ፀሀፊው የመፃፍ ችሎታ፣ እንደሚፃፍለት አካል የስልጣን ደረጃ፣ እንደሚፃፍለት አካል ቀረቤታ እና ርቀት፣ የደብዳቤው መደበኛነት እና ኢ-መደበኛነት፣ የአፃፃፍ ስልት፣ እንደፀሀፊው አትኩሮት እና ፍላጐት ሊለያይ ስለሚችል ነው (Melika Hadavi, 2015)::

ከዚህ በተጨማሪ በታሪካችን ውስጥ የነበሩ የተለያዩ ደብዳቤዎችን ውስጣዊ እና ውጫዊ ይዘት በጥልቅ ዲስኩር ትንተና በምንተነትንበት ጊዜ ደብዳቤዎቹ በተፃፉበት ዘመን የነበረውን የፖለቲካ ሁኔታ፣ የአስተዳደር ስርአት፣ የማህበራዊ ግንኙነት እንቅስቃሴ እና የኢኮኖሚያዊ ግንኙነት ሁኔታ ለመረዳት ያስችለናል፡፡ በሌላ በኩል በአንድ ዘመን የተፃፈን መዝገብ በጥልቅ የዲስኩር የትንተና ዘዴ በምንተነትንበት ወቅት በነበረው የፖለቲካዊ ስርአት ውስጥ የነበረውን የርዕዮተ አለም ግጭት፣ የርዕዮተ አለም የበላይነት፣ የሀይማኖት እና የመንግስት ግንኙነት ለይተን እንድንረዳ ያግዘናል፡፡ እነዚህን የተዘረዘሩ ነጥቦች ለመረዳት ግን መዛግብቱን በወፍ በረር ማንበብ በቂ ላይሆን ይችላል፡፡ ምክንያቱም ስለ አንድ ሰነድ ለመረዳት እና ተገቢውን ትንታኔ /ዲስኩር/ ለመስጠት ሰነዱ ውስጥ የሰፈሩትን ቃላት መረዳት፣ በመዝገቡ ውስጥ የሰፈሩትን አገላለፅ መረዳት፣ በሰነድ ውስጥ የሰፈሩ ሞያዊ እና ፖለቲካዊ ቃላት ወይም አገላለፆች ካሉ መረዳት እና በአጠቃላይ ገለፃዎቹ ወይም ቃላቶቹ በጊዜው ከነበረው የፖለቲካ፣ የሀይማኖት፣ የባህል፣ የአመለካከት፣ የእምነት፣ የኢኮኖሚ ወዘተ ሁኔታ ጋር በማገናኘት ለመረዳት መሞከር ውጤታማ ትንተና ለማድረግ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡

Norman Fairclough የተባለው ፀሀፊ በማከል ስለ ዲስኩር አሰጣጥ ዙሪያ በሰጠው ማብራሪያ ላይ የሚከተለውን ይላል፡፡ አንድን ሰነድ /ደብዳቤ/ በምንተነትንበት ወይም በምንደሰኩርበት ወቅት በሰነድ ውስጥ የሰፈሩ ሞያዊ እና ፖለቲካዊ ቃላት ወይም አገላለፆች ካሉ መረዳት እና በአጠቃላይ ገለፃዎቹ ወይም ቃላቱ በጊዜው ከነበረው የፖለቲካ፣ የሀይማኖት፣ የባህል፣ የአመለካከት፣ የእምነት፣ የኢኮኖሚ ወዘተ ሁኔታ ጋር በማገናኘት ለመረዳት መሞከር ውጤታማ ትንተና ለማድረግ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ ከዚሁ ጋር አያይዞ ፀሀፊው በዲስኩር አሰጣጥ ዙሪያ በሰጠው ማብራሪያ ላይ የሚከተለውን ይላል፡- - አንድን ሰነድ /ደብዳቤ/ በምንተነትንበት ወይም በምንደሰኩርበት ወቅት በሰነድ ውስጥ የሰፈሩትን ቃላት ወይም ሀረጋት ወይም አጠቃላይ ገለፃ ፍቺ በምንሰጥበት ወቅት ፍቻቸው በተንታኙ ወይም በደስኳሪው እይታ፣ እምነት፣ የቀደመ ልምድ እና ችሎታ ላይ የተመረኮዙ ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህም የተነሳ አንድ ሰነድ በተለያዩ ደስኳሪዎች የተለያየ የድስኮራ ውጤት ሊኖረው እንደሚችል ያሳየናል (Norman Fair clough, 2003,)::

ከላይ ከተጠቀሱት ነጥቦች ባሻገር አንድ ሰነድ በሚተነተንበት ጊዜ ስለ አንድ ማህበረሰብ የስልጣኔ ደረጃ፣ የትምህርት መስፋፋት እና እድገት ምን አይነት እንደነበር ለመረዳት ሊያስችለን ይችላል፡፡ ለምሳሌ በአንድ የአስተዳደር ዘመን በተፃፉ ማመልከቻዎች ወይም ደብዳቤዎች ላይ በአብዛኛው ተገልጋይ በጣቱ የፈረመበት ማመልከቻ ወይም ደብዳቤ በብዛት ከተገኙ በዘመኑ የነበረውን የት/ት እድገት ማሳያ ተደርጐ ሊቆጠር ይችላል፡፡ ከዚህ ባለፈ በተለያዩ ጊዜ የተፃፉ ሰነዶችን ወይም የስራ ደብዳቤዎችን በምንመረምርበት ጊዜ ከቋንቋ አጠቃቀም እና ከስርአተ ነጥብ አጠቃቀም አኳያ በጊዜ ሂደት የመጡ ለውጦችን ለመረዳት ያስችለናል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በትንተና ወይም ዲስኮራ ወቅት አንድ ማህበረሰብ ወይም ጐሳ ከሌላ የማህበረሰብ አባላት ጋር የነበረውን ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ወዘተ ግንኙነቶች ምን ይመስሉ እንደነበር ልንረዳበት እንችላለን፡፡

## 2.3ቀደምት የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ከ1922 – 1983 ዓ.ም ድረስ የተፃፉ የስራ ደብዳቤዎች ትንተና በሚል ርዕስ በተደረገው ጥናት በተመሳሳይ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ የተሰሩ ጥናቶችን በቀላሉ ማግኘት ተችሏል፡፡ ማለት አያስደፍርም፡፡ ነገር ግን በቀጥታ ግንኙነት ያላቸው ባይሆኑም በተወሰነ መልኩ ተያያዥ ሃሳብ ያላቸው ቀደምት ተዛማጅ ጥናቶችን ለማየት ተሞክሯል፡፡

(Edward Ullendorff 1972) "some early Amharic letters" በሚል ርዕስ ፅፏል፤ ይህ ፅሁፍ በኢትዮጵያ ውስጥ የተፃፉ ማመልከቻዎችንና የስራ ደብዳቤዎችን በመሰብሰብ የሰዋሰውና የቃላት አጠቃቀም ትንተና በማድረግ የተዘጋጀ ነው፡፡ በአጠቃላይ በዚህ ፅሁፍ ውስጥ ወደ 12 ደብዳቤዎች ቃል በቃል ተፅፈው ከሰዋሰው አገባብ አንፃርትንትና የተሰጣቸው ናቸው፡፡ ለምሳሌ በኢትዮጵያውያን አቆጣጠር ነሀሴ 6 ቀን 1916 ዓ.ም በወቅቱ የኢትዮጵያ መንግስት አልጋ ወራሽና እንደራሴ ከነበሩት ከራስ ተፈሪ መኮንን /ከንግስትና በኋላ ሀይለስላሴ/ ለምስራቅ ቋንቋዎች አስተማሪ ለሆኑትለፕሮፌሰር ሚትዎችየተፃፈ ደብዳቤና ማብራሪያው ይገኝበታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ነሀሴ 2 ቀን 1903 ዓ.ም /በኢትዮጵያ አቆጣጠር/ ከአለቃ ታዬ ለሚትዎች የተፀፈውን ደብዳቤና ሌሎች ደብዳቤዎችን በመፃፍ ከሰዋሰው አጠቃቀም አንፃር /እነዛን ቃላት ለምን እንደተጠቀሙ/ ሰፊ ትንተና የሚያደረግ ነው፡፡

ይህ ፅሁፍ ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ሁለቱም ስራዎች መሠረት አድርገው የሚነሱት የስራ ደብዳቤዎችንና ማመልከቻዎችን በመሆኑ ነው፡፡ የጥናቶቹ ልዩነት ደግሞ የዚህ ጥናት ዓላማ በደብዳቤዎቹና ማመልከቻዎቹ ውስጥ የተጠቀሱት ቃላት ካላቸው ቀጥተኛ መልዕክት በስተጀርባ በወቅቱ የነበረውን ፖለቲካዊ ፣ ሀይማኖታዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ማሳየት ሲሆን ይህ ጥናት ግን ትኩረት ያደረገው የሰዋሰው አጠቃቀም ላይ ብቻ ነው፡፡

በመሆኑም በዚህ ጥናት ውስጥ የስራ ደብዳቤዎችና ማመልከቻዎችን ከሰዋሰው አጠቃቀም ባለፈ መልኩ ሰፋ ያለ ትንተና ማድረግና በEdward Ullendorffጥናት ውስጥ ያልተነሱ ሃሳቦችን ሰፋ ባለ መልኩ የሚተነትን በመሆኑ በጥናቶቹ መሀከል ያለውን ክፍተት አመልካች ሆኗል፡፡

(Viviane Delpech 2012) "Two Amharic letters of debtera Tewelde Medhin of welqayt" በሚል ርዕስ የፃፈው ፅሁፍ ደግሞ ቀደምት የሆኑትን የኢትዮጵያ የስራ ደብዳቤዎችና ማመልከቻዎች ይዘትን የሚገመግም ነው፡፡ በእነዚህ የስራ ደብዳቤዎችና ማመልከቻዎች ውስጥ ቅኔዎችና ምሳሌያዊ አነጋገሮች መኖራቸውን ለምን እንደ ሆነ ያብራራል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በቀደመው ዘመን የሚፃፉ ማመልከቻዎችና የስ ደብዳቤዎች ይዘትንም ይገመግማል፤ አጀማመራቸው ለአምላክ ምስጋና የሚያቀርቡ መሆናቸውንም ይዘረዝራል፡፡

ከዚህ ጥናት ጋር ይህ ጥናት የሚያመሳስለው ሁለቱም በደብዳቤና ማመልከቻዎች ላይ ትንተና የሚያደርጉ በመሆናቸው ሲሆን የሚለያዩበት ምክንያ ደግሞ የቪቪን ዴልፒች ፅሁፍ ትኩረት የሚያደርገው ምሳሌያዊ አነጋገሮችና ቅኔዎች በደብዳቤው ውስጥ መገኘታቸው ለምን እንደሆነ የሚያብራራ ነው፡፡ ይህም በእነዚህምሳሌያዊ አነጋገሮችና ቅኔዎች አማካይነት መልዕክቱ ትኩረት እንዲያገኝ ያደርገዋል የሚል አጠቃላይ የሆነ እሳቤ ወይም መደምደሚያ ያለው ነው፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥ ግን ምሳሌያዊ አነጋሮችና ቅኔዎች ቀጥተኛ መልዕክት ከማስተላለፋቸው ባሻገር ምን እንድምታ እንዳላቸው እና ከዚህ ጋር ተያይዞምለአምላክ ምስጋና በማቅረብ የሚጀምሩትስ ለምን ይሆን?" በማለት በጥልቀት ትንተና የሚሰጥበት በመሆኑ የጥናቶቹ ልዩነት ሆኖ ይጠቀሣል፡፡

(Edward Ullendorff 1986) "Two Amharic letters by the Falasha leader Tamrat Emanuel." በሚለው ፅሁፍ ላይ ሁለት የአማርኛ ደብዳቤዎችን የሰዋሰውና የቃላት አጠቃቀም ትንተና አቅርቧል፡፡ በዚህ ፅሁፍ ውስጥ በቀዳማዊ ሀይለ ስላሴ ዘመን የተፃፉ ሁለት ደብዳቤዎችን የሰዋሰው አጠቃቀምና በእነዚህ ደብዳቤዎች ውስጥ የተጠቀሟቸው ቃላት አስፈላጊነትን የሚገልፅበት ነው፡፡

ቀጣዩ ጥናትና ይህ የኤድዋርድ ኡለንዶርፍ ፅሁፍ የሚያመሳስላቸው ጉዳይ ሁለቱም በደብዳቤዎች ላይ ትንተና የሚያደርጉ በመሆናቸው ነው፡፡ ነገር ግን የኤድዋርድ ስራ በሰዋሰውና በቃላት አጠቃቀማቸው ላይ ብቻ ትኩረት አድር ትንተናን የሚያደርግ መሆኑና በዚህ ጥናት የሚሰራው ጥናት ደግሞ ጥልቅ የሆነ የዲስኩር ትንተና ዘዴን በመጠቀም ቃላቱና ሀረጋቱ ቀጥተኛ ከሆነ ፍቺያቸው በስተጀርባ ያለውን ሁኔታ በጥልቀት ለመተንተን የታቀደ በመሆኑ የልዩነታቸው ምክንያት መሆን ችሏል፡፡

R.A Caulk የተባለ ፀሐፊ the Abyssinian difficulty by arrell sates the Amharic letters of emperor theodros of Ethiopia to Queen Victoria በሚል ርዕስ ላይ ተመርኩዞ ከንጉስ ነገስት ዳግማዊ ቴዎድሮስ ለእንግሊዝ

ንግስት ቪክቶሪያ ከመጀመርያው የ1949 ዓ.ም ደብዳቤ እስከመጨረሻው 1960 ዓ.ም ድረሥ የተፃፉ ሰላስ ሁለት ደብዳቤዎችን ከታርክ እና ከዲፕሎማሲያዊ አንደምታ አኳያ በጸሀፊው ተተንትኖ እናገኛዋለን፡፡

በጹሁፍ መሰረትንጉሰ ነገስት ቴዎድሮስ ለንግስት ቪክቶርያ የፃፉት ደብዳቤዎች በቃላት አወቃቀር ፣ በሥነ ቋንቋ አጠቃቀሙ እና ሀሳብ ፍሰት በጣም የበሰሉናቸው፡፡ ንጉሰ ነገሥቱ ይሄንን ደብዳቤ በወቅቱ ለነበሩት ንግስት በተመረጡ ቃላት እና በሁለት ነገስታ መካከል መደረግ ያለበትን የፖለቲካ ዲፕሎማሲ በሚመጥን መልኩ መፃፋቸውን ይሄ ፁሁፍ ያስረዳል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ይህ ፁሁፍ ንጉሰ ነገስት ቴዎድሮስ ለንግስት ቪክቶሪያ የፃፉትን ደብዳቤ ከታሪካዊ ጠቀሜታው አንፃር እና በደብዳቤው ውስጥ የነበሩትን የስነ ቋንቋ አጠቃቀም፣ የሥነ ቃል አጠቃቀም እንዲሁም ከመልዕክት ማስተላለፍ በስለት እና አቀራረብ አኳያ ደብዳቤዎች ለመተንተን ሞከሯል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በዚህ ፁሁፍ ውስጥ በኢትዮጵያ ቤተ መንግስት ውስጥ ደብዳቤዎች በምን መልኩ ይፃፍ እንደነበር የተለያዩ ደብዳቤዎችንበምሳሌነት በማቅረብ ለማብራራት ይሞከራል፡፡ በሌላ በኩል በዚህ ፁሁፍ ውስጥ በደብዳቤዎች ላይ ሥላሉ መሀተም እና ፊርማ በማብራራት አንድ መደበኛ ደብዳቤ ምን ማካተት እንዳለበት ለማብራራት ይሞከራል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ደብዳቤዎቹን በወቅቱ ከነበረው የዘመን መንፈስ ጋር በማያያዝ ከዲፕሎማሲ ስታርክ እና ከፖለቲካ አኳያ የነበራቸውን አንድምታ ለማብራራት ይሞከራል፡፡ በአጠቃላይ በዚህ ፁፍ ውስጥ ፀሀፊው ከንጉሰ ነገስት ዳግማዊ ቴዎድሮስ ለንግስት ቪክቶሪያ የተፃፉ እና በእንግሊዝ ቤተመዘከር ውስጥ የተሰነዱ ሰላሳ ሁለት የአማርኛ ደብዳቤዎችን እና የእንግሊዝኛ ትርጉማቸውን በዋቢነት በማንሳት እና የተፃፉበትን አላማ ከታሪክ እና ከዲፕሎማሲአንፃር በመተንተን ለማብራራት የሚሞከር ነው፡፡

ይህ ፁሁፍ ከቀዳማዊ ሀይለ ስላሴ ዘመን እስከ ደርግ ዘመን በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የተጻፉ መደበኛ ደብዳቤዎች ይዘት ትንተና ከሚለው ጥናት ጋር የሚመሳሰለው ሁለቱም ጥናቶች መሰረት አድርገው ተነሱት መደበኛ ደብዳቤዎችን በመሆኑ ነው፡፡ በሌላ በኩል በሁለቱ ጥናቶች መካከል ያለውን ልዩነት በምንመለከትበት ወቅት የ R.A.caulk ጥናት በዋናነት ደብዳቤዎቹን በወቅቱ ወይም ደብዳቤዎቹ ከተፃፉበት የጊዜ መንፈስ አኳያ የነበረውን የታሪክ እና የዲፕሎማሲ ሁኔታ ለመተንተን ከማሰብ አኳያ ነው፡፡ ይህ ጥናት ግን መደበኛ ደብዳቤዎችን ከተፃፉበት የዘመን መንፈስአንፃር የያዙትን የሰዋሰው አጠቃቀም ፣ የቃላት አጠቃቀም ከቃላት አጠቃቀማቸው ጀርባ ያለን ትርጓሜ በአጠቃላይ የደብዳቤዎቹን ፖለቲካዊ . ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ አንድምታ ከግምት በማስገባት የሚተነትን ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በሁለቱ ጥናቶች መካከል የዘመንእና የቦታ ልዩነት መኖሩን እንረዳለን፡፡ በመሆኑም የሱ ጥናት ከቀዳማዊ ይሀለ ስላሴ ዘመን እስከ ደርግ ዘመን በደቡብ ምዕራብ ኢትጵያ የተፃፉ መደበኛ ደብዳቤዎች ይዘት ትንተና በሚል ዕርስ ለተሰራው ጥናት ደብዳቤዎች ከፖለቲካ እና ከዲፕሎማሲ አኳያ በምን መልኩ መተንተን እንዳለባቸው ለመረዳት በግባአትነት ውላል (Ricard Pankhurst 1979)፡፡

(Ricard Pankhurst 1920) The Amharic letters of empior Theodor of Ethiopia to queen victoria and her special envory በሚል ርዕስ ስር ዳግማዊ ንጉሰ ነገሰትቴዎድሮስ ለንግስት ቪክቶሪያ እና የቪክቶሪያ መልዕክተኛ ለነበረው ለራስማ የፃፉትን ደብዳቤዎች በወቅቱ የነበረውን የታሪክ እና የግንኙነት መንፈስ በሚያብራራ መልኩ አብራርተዋል፡፡ አንደ ፓንከረስ ገለፃ ዳግማዊ ቴዎድሮስ በወቅቱ ደብዳቤዎችን በአማርኛ ብቻ ሳይሆን በአረበኛም ይጽፉ እንደነበር እና ይህም የሚያሳየው በወቅቱ አረበኛ በኢትዮጵያ ውስጥ የዲፕሎማሲ ቋንቋ ነው በማለት ያስረዳሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ፀሀፊው በፁሁፋቸው ላይ እንደሚገልፁት በዘመኑ የተፃፉት ደብዳቤዎች ከታሪክ አኳያ ብቻ ሳይሆን ከስነ ልሳን (lingustic) ጥናት አኳያ ጥቅም እንዳላቸው ካብራሩ በኋላ ደብዳቤዎቹ horthography ከአረፍተ ነገር አወቃቀር (sentence structure) እና

የዘዬ ሁኔታ (dialect features)አኳያም ለየት ያሉ በመሆናቸው ጥናት ቢደረግባቸው ጠቀሜታቸው የጎላ መሆኑን ያብራራሉ፡፡

በዚሁ መሰረት የፓንክረስት ፅሁፍከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ሁለቱም ከዚህ በፊት የተፃፉ መደበኛ ደብዳቤዎች ላይ ትኩረት አድርገው ትንታኔ መስጠታቸው ሲሆን፤ ልዩነታቸው ደግሞ የፓንክረስት ፁሁፍ በዋናነት ደብዳቤዎቹን በወቅቱ ወይም ደብዳቤዎቹ በተፃፉበት የዘመን መንፈስ የነበረውን የታሪክ፣የፖለቲካ እና የዲፕሎማሲ ግንኙነት ከመተንተን አኳያ የቀረበ ሲሆን ይህጥናት ደግሞ ደብዳቤዎችን ከቃላት አጠቃቀም ፣ ፣ ከፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ አንድምታ አኳያ ደብዳቤዎቹን ከጀርባቸው ያዘሉት መልዕክት ምን እንደሆኑ ፣ የደብዳቤዎቹ ውጫዊ እና ውስጣዊ ይዘት ላይ በማተኮር ያብራራ መሆኑ ነው፡፡ በዚሁ መሰረት የፓንክረስትን የደብዳቤ ትንተና ፅሁፍ በዚሁ ጥናት ውስጥ ደብዳቤዎች ከፖለቲካዊ እና ዲፐሊማሲያዊ አንድምታቸው አኳያ በምን መልኩ መተንተን እንዳለባቸው ለመረዳት ተጠቅሜበታለው፡፡

(Ricard Pankhurst 1910) በኢትዮጵያ ጥናት እና ምርምር ተቋም (Institute of Ethiopianstudies)Discovery of unpublished letter from Ase Tewodros to Etege Yetamennu በሚል ርዕስ የተነተኑት እና ከአፄ ቴዎድሮስ ለእቴጌ ይታመኑ የተፃፉ ደብዳቤ በዚህ ፁሁፍ ውስጥ በተዛማጅ የመረጃ ዳሰሳ ውስጥ ከተካተቱት መካከል አንዱ ነው፡፡ በዚህ ፁሁፍ ውስጥ ፀሀፊው ፓንክረስት እንደገለፁት ዳግማዊ ንጉሰ ነገሰት ቴዎድሮስ ከቀደሙትየኢትዮጵያ መሪዎች በተሻለ በቋንቋ አጠቃቀማቸው እና በደብዳቤዎቹ የሀሳብ ፍሰት የተዋጣላቸው ደብዳቤ ፀሀፊእንደነበሩ ከብራሩ በኋላ በቴዎድሮስ ዘመን የተፃፉ ደብዳቤዎች በግዕዝሳይሆን በአማርኛ መፃፋቸውን ያብራራሉ፡፡ በፀሀፊው አገላለፅ ይታመኑ የወሎ ሙስሊም ኦሮሞ ሚስት ስትሆን ዳግማዊ ቴዎድሮስ ስለ ውበቷ እና ብልሀቷ በማስማቱ ወደ በተመንግስት አስጠርቶ የአፄ ቴዎድሮስ ደብዳቤ ተቀባይ ወይም እንደ ፓንክረስት ገለፃ(the recipient of number of a Tewodross lettersእንዳደረጋት እና በቅምጥነት እንዳስቀመጣት ይገልፃል፡፡ ነገር ግን አፄቴዎድሮስ ለራስማ በፃፏቸው ደብዳቤዎች ላይ ይታመኑን“እቴጌ” ብለው መጥራታቸው ንጉሱ ወይዘሮዋን በቅምጥነት ሳይሆን በሚስትነት እንደተቀበሏቸው የሚያሳይ ነጥብ መሆኑን ፓንክረስት በፁሁፋቸው ላይ ያብራራሉ፡፡ ርቻርድ ፓንክረስት ከአፄ ቴዎድሮስ ለእቴጌ ይታመኑ ለተፃፉ ደብዳቤዎች እና አሁን በእንግሊዝ ለይብረሪዎች ውስጥ ስለሚገኙ ደብዳቤዎች እውነተኛ ፣ የአፃፃፍ ድምፀት (tone)ስለ ተፃፉበት ቋንቋ ፣ ስለ ርዝመታቸው ወዘተ ይገልፃል፡፡ ለምሳሌ እንዲህ ይላል ዳግማዊ ቴዎድሮስ ለይታመኑ የጻፉቸው አብዛኛዎቹ ደብዳቤዎች በጣም አጭር ወይ ከ አምስት እስከ አስራ አንድ መስመር የሚረዝሙ እና በእጅ መፃፋቸውን ያብራራል፡፡ ደብዳቤዎቹ በፀሁፋቸው መጀመሪያ በአምላክ ስም ሰላምታ በማቅረብ እንደ ሚጀምሩም ይገልፃለ፡፡ ደብዳቤዎቹ በዋናነት የተፃፉት (1) ለይታመኑ (2) ለይታመኑ እናት ነገር ግን ሥማቸው አልተገለፀም (3) ወይዘሮ ሰናይት ለምትባል ሴት እና ማንነቷ በውል ላልተብራራ ሴት እና (4) ለአፄ ቴዎድሮስ ለራሳቸው ቤተሰብ መሆኑን ይገልፃል፡፡

ከደብዳቤዎቹ ውስጥ ሁለቱ ብቻ ቀን እንደተፃፉባቸው ይገልፃል፡፡ እነሱም አንዱበጥር2/1859 ዓ.ም መፃፉን ሲገልፀ ሁለተኛው በጳጉሜ 5/1867 መሆኑን ያብራራል፡፡ ከዚህ ባለፈ ሌሎቹ ደብዳቤዎች ቀንም ሆነ አመተ ምህረት ያልተፃፈባቸው እና የፀሀፊው የአፄ ቴዎድሮስ አድራሻ ደብዳቤዎቹን በሚፅፉበት ጊዜ እና ደብዳቤው የተፃፉላቸው “እቴጌ” ይታመኑ ወይም የተቀበይ አድራሻም እንሁም በደብዳቤዎቹ ላይ አለመገለፁን ፀሀፊው ያብራራል፡፡ ከዚህ ባለፈ በተፃፉትደብዳቤዎች ላይ አፄ ቴዎድሮስ ለእቴጌ ይታመኑ ደብዳቤዎቹን የፃፉበት ምክንያት በደብዳቤዎቹ ውስጥ አለመጠቀሱን ያብራራል፡፡ነገር ግን ፀሀፊው

በደብዳቤዎቹ ውስጥ የሰፈሩትን ቃላት እና በተለይ ሁለቱ ቀን እና አመተ ምህረት ያላቸውን ደብዳቤዎች በምሳሌነት በመውሰድ ከታሪክ አኳያ ያላቸውን ፋይዳ እና በደብዳቤዎቹ ላይ የላኪ እና የተቀባይ አድራሻ ባይኖርም የራሱን መላምት በመሥጠት አስቀምጧል፡፡ በዚሁ መሰረት ለምሳሌ በ1859 የተፃፈውን ደብዳቤ በመውሰድ እና በደብዳቤው ውስጥ ቴዎድሮስ ለሰራው መድፍ መንገድ እያስጠረገ መሆኑን እና እየመጣ መሆኑን የሚገልፀውን ሀሳብ በመያዝ እቴጌ ይታመኑ ቀድመው መቅደላ መሄዳቸውን እና አፄ ቴዎድሮስ ደግሞ ከቀድሞ ማዕከላቸው ከደብረታቦር ሆነው ደብዳቤዎቹን እንዳፃፉላቸው ይገልፃል፡፡

ይህ ከላይ የቀረበው ፅሁፍ ከሀይለስላሴ ዘመን እስከ ደርግ ዘመን በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የተፃፉ መደበኛ ደብዳቤዎች ይዘት ትንተና ከሚለው ከዚህ ጥናት ጋር የሚመሳሰለው ሁለቱም ፅሁፎች መደበኛ ደብዳቤን መሰረት አድርገው መፃፋቸው ነው፡፡ ከዚህ ባለፈ ፀሀፊው በደብዳቤዎቹ ውስጥ የተደበቀውን ሀሳብ ለማግኘት የደብዳቤው ፀሐፊ ተጠቀመባቸውን ቃላት የመረመረበት ሁኔታ ይሰተዋላል፡፡ አጥኝዋ በዚህ ጥናት ውስጥም ተመሳሳይ ሥልት ለመከተል ሞክራለች፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ፀሀፊው ደብዳቤውን ከላኪ እና ከተቀባይ አድራሻ አኳያ ፣ ከተፃፈበት ዘመን ወይም መኖር አለመኖር አኳያ ደብዳቤዎቹን ከድምፀት (tone) አኳያ ወዘተ በመመርመር ትንታኔ ለመስጠት ሞክሯል፡፡ አጥኛዋ በምታጠናው ፁሁፍ ውስጥም የተነተነቻቸውን ደብዳቤዎች ከላይ ከቀረቡት ነጥቦች አኳያ ለማየት መሞከሯ የሁለቱን ጥናቶች በከፊል መመሳሰል ያመለክታል፡፡

የጥናቶቹን ልዩነት በምናይበት ጊዜ ርቻርድ ፓንከረስት ደብዳቤዎቹን በሚተነተንበት ወቅት ትንታኔዎቹን ከታሪካዊ ፋይዳቸው አኳያ ነው የተመለከተው፡፡ ነገር ግን አጥኝዋ በዚህ ጥናት ውስጥ ደብዳቤዎቹን የተነተነችው ከተግባራዊ ስነ ልሳን አኳያ የጥልቅ ዲስኩር ትንተና በመጠቀም መሆኑ በሁለቱ ጥናቶች መካከል ልዩነት መኖሩን ያመለክታል፡፡ በሌላ በኩል የፓንለክረስት የደብዳቤ ትንተና በአፄ ቴዎድሮስ ዘመን የተፃፉትን ደብዳቤ ሲተነትን ይህ ጥናት ግን በሀይለ ስላሴ እና በደግር ዘመን የተፃፉ ደብዳቤዎችን ይተነትናል፡፡ በተጨማሪም የሪቻርድ ፓንክረስት ትንተና ደብዳቤዎቹን ከፖለቲካዊ እና ከታሪካዊ ዳራ የተመለከተና በደብዳቤዎቹ ውስጥ ያሉትን ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊ፣ ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ያልሰጠ መሆኑን እንረዳለን፡፡ በዚሁ መሠረት አጥኚዋ በጥናቷ ውስጥ ከላይ የቀረቡትን ክፍተቶች ከስነ ልሳን አኳያ የጥልቅ ዲስኩር ትንተና ዘዴ በመከተል ክፍተቶቹን ለመሙላት ሞክራለች፡፡በሌላ በኩል በዚህ ጥናት ላይ የርቻርድን ጥናት አጥኝዋ የቃላት አተናተን ስልት ፣ ደብዳቤዎችን ከድምፀታቸው (tone) አኳያ እንዴት መተንተን እንደለባቸው ለመረዳት እና በአንድ ደብዳቤ ላይ ቀን ፣ የላኪ አድራሻ የተቀባይ አድራሻ ባይኖር እንዴት መመርመር እና መገመት እንደሚቻል ለመረዳት በመቻሏ በጥናቷ ውስጥ ዘዴውን ለመተግበር የርቻርድን ጥናት ተጠቅማበታለች

በአጠቃላይ በዚህ ጥናት ውስጥ እንደ ርዕሱ አዲስነት በቀደምት ተዛማጅ ጥናት ሊነሱ የሚችሉ ተመሣሣይ ስራዎችን ማግኘት አስቸጋሪ መሆኑን ከላይ የተገለፁትን ብቻ እንደመነሻ በመውሰድ በጥናቱ ውስጥ ተካትተው እንዲቀርቡ ተደርጓል፡፡

### 2.4 ጥናቱ የተካሄደበት አካባቢ ዳራዊ መግለጫ

የደቡብ ምዕራብ የኢትዮጵያ ክፍል በተፈጥሮ ሀብቱ የበለፀገ ከመሆኑም በላይ በመልከአ ምድር አቀማመጡ የበዛ አይነት ገፅታ ያለው አካባቢ ነው፡፡ የአካባቢው የመልከአ ምድር አቀማመጥ 2,000 ሜትር ከፍታ ካላቸው ተራራማ አካባቢዎች 800 ሜትር ከፍታ እስካላቸው ቦታዎች በአካባቢው እና በሱዳን ድንበር በኩል መኖሩን እንረዳለን፡፡ አመታዊ የዝናብ መጠኑን

በምናይበት ጊዜ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ለምለም ከምንላቸው የሀገሪቱ አካባቢዎች እንዲሆን ያደረገው ከ 2400 ሚሊ.ሜትር እስከ 1000 ሚሊ. ሜትር መካከል ባለው ልዩነት ውስጥ አመታዊየዝናብ መጠን እንደሚያገኝ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ አካባቢው በሀገሪቱ ብዙ ህዝብ በአንድ ቦታ ከሚኖሩባቸው አካባቢዎች እና የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች ከመኖራቸው ጋር ተያይዞ ብዙ አይነት ቋንቋ ከሚነገርባቸው የኢትዮጵያ አካባቢዎች በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀስ አካባቢ ነው፡፡Adrian P.wood (1993)

ከዚህ በተጨማሪ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ አካባቢ በቡና ምርቱ በደን ሽፋኑ እና ምርቱ ተጠቃሽ አካባቢ ነው፡፡ በአካባቢው የአረቢካ ቡና በሰፊው የሚገኝ ሲሆን ይህ አካባቢ ለአለም የቡና መገኛ የደን ቀለበት ወይም የደን መቀነት የሚገኝበት አካባቢ መሆኑን የተለያዩ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ በዚህ የተነሳ የአካባቢው መህበረሰብ ህይወት በሰፊው እንደ ቡና ባሉ cash crops ወይም የገንዘብ ወይም የገቢያ ምርቶች ላይ የተንጠለጠለ ነው፡፡ ከዚህ ባለፈ አካባቢው በእንሰት ምርቱ የሚታወቅ ሲሆን በአካባቢው እንሰት በምግብነት በሰፊው ይውላል (Tola Gpmechu Ango 2018 pp1-2)፡፡

## 2.5 የብሔር እና ቋንቋ ብዝሀንነት በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ

(D.sutcliffte 1993):: የተባለ ፀሐፊ እንደሚገልፀው የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ አካባቢ ለተለያዩ ብሄር ብሔረሰቦች እና ብሄረሰቦቹ ለሚናገሯቸው ቋንቋዎች መኖሪያ መሆኑን ያብራራል፡፡ በተለይ ደግሞ ጎፋ በከፋ ፣ በቤንች ማጂ ፣ በሸካ ፣ በጅማ እና መሰልአካባቢዎች በርከት ያሉ ብሄር ብሄረሰቦች መኖራቸውን ይገልፃል፡፡ በዚህ ክልል በዘልማድ የኦሞቲክ የቋንቋ ተናጋሪዎች በስፋት የሚገኙበት አካባቢ መሆኑንም ፀሐፊው ያብራራል፡፡ በአካባቢው ኦሞቲክ የቋንቋ ተናጋሪዎችባለፉ የኩሽቲክ የቋንቋ ተናጋሪዎች እንደሚገኙበት ይገልጻል፡፡ ለዚህም በምሳሌነት የኦሮምኛ ቋንቋን ይጠቅሳል፡፡ በአካባቢው በሸለቆአማው እና ዝቅተኛው አካባቢ የኦሞቲክ ቋንቋ ተናጋሪዎች የሆኑ እና የሱዳን አደኞች እና የፍራፍሬ ለቃሚዎች ፣ ከብት አርቢዎች እና በግብርና የሚተዳደሩ የማህበረሰብ ክፍሎች እንደሚኖሩ ይታመናል፡፡ (P.sutcliffe 1992)

ከዚህ በተጨማሪ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ከሰሜኑ ከምስራቁ የሀገሪቱ ክፍል የመጡና በአብዛኛው በከተማው አካባቢ እና ከተሞች በቅርብ ርቀት ባሉ ገጠራማ አካባቢዎች በብዛት ይገኛሉ፡፡ የነዚህ ማህበረሰቦች በአካባቢው መገኘት በብዛት ቡና አምራች የሆኑ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ አካባቢዎች በርከት እንደሚል (wood 1983) የተባለ ፀሀፊ ይገልፃል፡፡

## ምዕራፍ ሶስት

## 3. የጥናቱ ዘዴና አካሄድ

በዚህ ክፍል ትኩረት ተደርጐ የሚሰራው ለጥናቱ ስራ የሚውሉ መረጃዎች በምን መልኩ እንደሚሰበሰቡና በምን መልኩ ሳይንሳዊ የጥናት ስልቶችን በመከተል ተገቢውን እና ትርጉም አዘል የጥናት ውጤት እንደሚሰጡ ማሳየት ይሆናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በዚህ ጥናት ውስጥ በመሪነት ተዘርዝረው የተቀመጡ ጥያቄዎች ከምርምሩ አላማ እና ግብ አኳያ የተሰበሰቡትን መረጃዎች አግባብነት ባለው የመተንተኛ ስልት በመጠቀም ለጥያቄዎቹ መልስ በምን መልኩ የሚሰጥ መሆኑን እና ጥናቱ በምን አይነት ሁኔታ እንደሚካሄድ በግልፅ የምናይበት ይሆናል (Creswell 2002)::

### 3.1 የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናት በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ከኃይለሥላሴ ዘመነ መንግስት ጀምሮ የተፃፉ መደበኛ የስራ ደብዳቤዎችን ቅርፃዊ ትንተና የተደረገበት ሲሆን ጥናቱን ውጤታማ እና ተገቢውን አላማ እንዲመታ ለማድረግ ለጥናቱ አግባብነት ያላቸውን የተለያዩ የፅሁፍ ውጤቶችን በማንበብ ለጥናቱ በመሰረታዊ የመረጃ ምንጭነት ከሚያገለግሉት መደበኛ ደብዳቤዎች እና ማመልከቻዎች ጋር በማሰናሰል ትርጉም ያለው የምርምር ውጤት ለማቅረብ ጥረት ተደርጓል፡፡ ይህ ጥናት አይነታዊ የምርምር ዘዴን የሚከተል በመሆኑ ለዚህ ጥናት በግብአትነት የሚውሉ ሰነዶችን ወይም መደበኛ ደብዳቤዎችን የአይነታዊ ገላጭ ትንተና ዘዴን በመጠቀም መረጃዎችን ለመተንተን ተሞክሯል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ለዚህ ጥናት ውጤት በግብአትነት ጥቅም ላይ የዋሉ ደብዳቤዎች የገላጭ ትንተና ዘዴን መሰረት በማድረግ በሚተነተኑበት ወቅት የደብዳቤውን ወይም የማመልከቻቸውን ቅርፃዊ ይዘት ማለትም እንደ የራስጌ መሀተም ወይም የተቋም አርማ /logo/፣ ቀን፣ የደብዳቤ ቁጥር፣ የላኪ እና የተቀባይ ወይም የአመልካች እና የማመልከቻው ተቀባይ ስም፣ አድራሻ፣ የሰላምታ አሰጣጥ በምን መልኩ እንደተደረገ እና የተዘረዘሩት ነጥቦች ከተፃፉበት ዘመን አኳያ የነበራቸውን አንድምታ ለማየት ተሞክሯል፡፡ በዚህ ላይ ሰነዶቹ ወይም መደበኛ ደብዳቤዎቹ በውስጣቸው የያዙት መልዕክት ድምፀት (tone) ከቃላት ድግግሞሽ እና በደብዳቤው ውስጥ ያሉ የደብዳቤው መሰረታዊ ቃላት በዙሪያቸው በአጃቢነት ከተሰደሩ ቃላት አንፃር በማየት ለመተንተን ጥረት ተደርጓል፡፡ በዚሁ መሰረት (Norman Fairclough) የተባለ ፀሀፊ እንደሚገልፀው በአንድ ሰነድ የፅሁፍ ምርመራ እና ትንተና ወቅት የተደጋገሙ ቃላትን እና ሌሎች ወሳኝ የፅሁፉን አንኳር ጉዳይ የያዙ ቃላትን በአግባቡ መመርመር ያስፈልጋል፡፡ ምክንያቱም ቃላቱ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ አእምሮአዊ፣ ሞራላዊ አንድምታ ሊኖራቸው ስለሚችል (Norman Fairclough 2014 )ገልፆታል:: እናም በዚህ ፅሁፍ ውስጥ በግብአትነት የዋሉ ደብዳቤዎች እና ማመልከቻዎች ሲተነተኑ ቃላቱ ከምን አኳያ እና ለምን አይነት ሚና በዚያ ፅሁፍ ውስጥ እንደተገኙ ተተንትኗል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በጃንሆይ ዘመን እና በደርግ ዘመን በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የተፃፉ ደብዳቤዎችን በዚህ ፅሁፍ ውስጥ በተተነተኑበት ወቅት የደብዳቤው ፀሀፊ ለፅሁፉ ባለቤት ወይም በደብዳቤው ውስጥ ለሰፈረው ሀሳብ ባለቤት በሚሰጥበት ወቅት በምን መልኩ ባለቤቱ እንደተሰየመ እና ለምን በዛ መልኩ እንደተሰየመ የተተነተነ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ Communication strategies a critical Discourse Analysis of a Business Letter በሚል ፅሁፋቸው ውስጥ Tabassum እና Behzad የተባሉ ፀሀፊዎች እንደሚያስቀምጡት በአንድ መደበኛ ደብዳቤ ውስጥ አንድ ፅሁፍ ለፅሁፉ ከ

«የእኔ» እና «እኔ» ባለቤትነት ይልቅ «የእኛ» እና «እኛ» ባለቤትነት ድምፀት ያላቸው ባለቤቶችን በስፋት የሚጠቁም ከሆነ ፀሀፊው በጉዳዩ ዙሪያ ሀላፊነት ለብቻው መውሰድ አለመፈለጉን ያመለክታል፤ ወይም ፀሀፊው በሚፅፈው ጉዳይ ዙሪያ ሀላፊነት ለመውሰድ ዝግጁ አለመሆኑን ያሳያል፤ ወይም ፀሀፊው በጉዳዩ ላይ መተማመኑ ዝቅተኛ መሆኑን ያሳያል የሚል ትንተና እናገኛለን (Tabassum and Behzad, 2013)። በዚሁ መሠረት አጥኚዋ ደብዳቤዎቹን በምትተነትንበት ወቅት በደብዳቤው ውስጥ ለሰፈሩ ሀሳቦች ባለቤት በምን መልኩ እንደተሰጡ በማየት ተተንትነዋል።በተጨማሪም የጥልቅ ዲስኩር ትንተና መርህን በመጠቀም ጥናቱን ለማድረግ ተሞክሯል። ይህንን መርህ መከተል ያስፈለገው አንድን ባህል፣ ማህበራዊ ልማድ፣ ማህበራዊ ህይወት፣ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ እና ፖለቲካዊ ሁኔታ በግለሰቦች አንደበት እና በተለያዩ ሰነዶች እና ፅሁፎች ውስጥ ትርጉም ያለው ትንተና ለማድረግ ጠቃሚ በመሆኑ ነው። ነገር ግን የጥልቅ ዲስኩር ትንተና መርህ (CDA) እንደ ብቸኛ የመተንተኛ ዘዴ ተደርጐ መወሰድ የለበትም። ለምሳሌ Van Disk የተባለ ፀሀፊ እንደሚያትተው CDA በዋናነት የሚያተኩረው በአንድ የፖለቲካ ወይም የማህበረሰብ ክፍል የላላ የበላይ እና የበታች የማህበረሰብ፣ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ ወዘተ ክፍሎች ዲስኮርስ ላይ ነው ይለናል።

በዚሁ ዲስኮርስ መሰረት በማህበረሰቡ ውስጥ በሚፈጠሩ የፖለቲካ፣ የማህበራዊ፣የኢኮኖሚ ወዘተ የመደብ የበላይነት እና የበታችነት ውስጥ የሚፈጠርን የጨቋኝ እና የተጨቋኝ ሁኔታን ከግለሰቦች፣ ከመገናኛ ተቋማት እና ከፅሁፎች አኳያ በማየት ለመተንተን እንደሚረዳ ይገለፃል ( T.s Van Disk, 1993):: በሌላ በኩል Fairclough የተባለ ፀሀፊ "Critical and descriptivl goals in discourse analysis" በተሰኘ ፅሁፍ ላይ የጥልቅ ዲስኩር ትንተና (CDA) በቀናነት በአንድ ፅሁፍ ወይም ንግግር ውስጥ የስነ ቋንቋ ሁኔታ (linguistic elements) ለመተንተን እንደሚያገለግል ያብራራል። ይህ ፀሀፊ በማዕከል እንደሚያትተው በርከት ያለ የ CDA ተመራማሪዎች በብዛት የባለቤት ትንተና (actor analysis) ላይ እንደሚያተኩሩ ይገለፃል።

ከዚህ ባለፈ Fair Clough(1993) በሌላውAnalysing Discourse በተባለ መፅሀፉ ላይ እንዳተተው የጥቅል ዲስኩር ትንተና እንደተንታኙ የዲስኩር እይታ፣ እምነት፣ የቀደመ ልምድ እና ችሎታ የተለያየ ሊሆን ይችላል። በሌላ በኩል Widdowson የተባለ ፀሀፊ (Discourse Analysis: A critical view)በሚል ፅሁፉ ውስጥ ከላይ በ2003 በ FairClough የቀረበውን ፅሁፍ በከፊል በመደገፍ የጥልቅ ዲስኩር ትንተና (CDA) በተንታኙ እይታ ላይ የተመረኮዘ መሆኑን(user centered)በመግለፅ በጥልቅ ዲስኩር ትንተና ወቅት ከሚተነተነው ንግግር እና ፅሁፍ ወይም ሌላ ባሻገር በትንተናው ላይ የተሳተፉት ተንታኞች ሁኔታ እና ጀርባ መታየት አለበት ይላል።ምክንያቱም የተንታኙ ፍላጐት ወይም ትኩረት የትንተናውን አቅጣጫ የተለየ ሊያደርገው ስለሚችልነው። በዚሁ መሰረት የጥልቅ ዲስኩርትንተና (CDA) አንድ ምልከታ ተንታኙ ወይም ደስኳሪው የደሰኮረበት መንፈስ እና ሁኔታ ወይም መንገድ ነው። በዲስኮራው ወቅት ደስኳሪው ዲስኩሩን አስቦበትም ይሁን ሳያስብበት ያሰፈረው ሃሳብ ዝም ብሎ በዘፈቀደ (arbitrariy) የመጣ ተደርጐ መወሰድ የለበትም (H. widdowson, 1995)።

Chilton እና Schatter የተባሉ ሌሎች አጥኚዎች "Hand book of Discourse analysis"የተባለ ፅሁፍ ላይ እንደሚያትቱት ከሆነ የጥልቅ የዲስኩር ትንተና ዘዴን ተጠቅሞ ንግግሮችን እና ፅሁፎችን የሚተነትን ተንታኝ ትኩረት ሊሰጣቸው ከሚገባቸው ነጥቦች መካከል በንግግሩ ወይም በፅሁፉ ውስጥ ተውላጠ ስሞች በምን መልኩ እንደተሰየሙ እና

በፅሁፉ ውስጥ የያዙትን ሚና እንዲሁም በፅሁፉ ውስጥ ባቀረቡት ሀሳቦች በምን መልኩ የባለቤትነት ይዞታ እንደተሰጣቸው ማየት ይገባል ይላሉ፡፡ Chilton and Schatter (1997)::በሌላ በኩል በአንድ የጥቅል ዲስኩር ትንተና (CDA) በአንድ ክስተት፣ ተግባር እና ፅሁፍ መካከል ያለ ምክንያታዊ እይታ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ CDA በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ያለን የባህል፣የሀይማኖት፣ የፖለቲካ ወዘተ ቅርፅ፣ ግንኙት እና ሂደት እንዴት በፅሁፉ እና በንግግር ውስጥ እንዴት እንደሚንፀባረቅ ወይም እንዴት እንደተንፀባረቀ የምንመረምርበት ዘዴ ነው፡፡ ከዛም ሲያልፍ በአንድ የፖለቲካ ማህበረሰብ ውስጥ ያለን የመደብ ትግል፣ የርዕዮተ አለም የበላይነት፣ የግንኙነት ቅርፅ እና ሲስተም በምን መልኩ እንደተደራጀ የሚያመለክተን ዘዴ ነው፡፡ የጥልቅ ዲስኩር ትንተና ከሌሎች የትንተና ዘዴዎች በዋናነት ከሚለይባቸው ባህሪያቱ መካከል አንድ ጥልቅ (Critical) መሆኑ ነው፡፡ ጥቅል (Critical) የሚለው የሚያመላክተው በአንድ ፅሁፍ ወይም ንግግር ውስጥ የተገለፀን ጥቂም ሀሳብ ወይም መልዕክት በምክንያት እና በውጤት ላይ ተመርኩዞ ስለሚያብራራ ነው (R.Batstone 1995)::

በሌላ በኩል Fairclough የተባለ ፀሀፊ እና በጥልቅ ዲስኩር ትንተናን (CDA) በተመለከተ ብዙ አስተዋፅኦ ያበረከተው ተመራማሪ በ1989 Language and power በሚል መፅሀፉ ላይ እንደሚገልፀው በመፅሀፉ ውስጥ ያሉትን ቃላት፣ የሰዋሰው አጠቃቀም እና የፅሁፉ ወይም የአፃፃፍ ቅርፁን ከግምት በማስገባት የሚከተሉትን ጥያቄዎች እየጠየቀ መመለስ ይኖርበታል፡፡ ለምሳሌ በዚህ ፅሁፍ ውስጥ ከሰፈሩት ቃላት መካከል ወሳኝ ቃላት የትኞቹ ናቸው? በዚህ ፅሁፍ ውስጥ ከሰፈሩት ወሳኝ ቃላት ጀርባ በቀጥታ ያልተነገረው ሚስጢራዊ መልዕክት አለ? ካለስ ለምን፣ እንዴት ብሎ መጠየቅ ወደአሰብነው ግብ ለመድረስ ይረዳናል፡፡ የሰዋሰው አጠቃቀምን እና የፅሁፉን ቅርፅም በተመላከተ እንደዚሁ ጥልቅ (Critical), ጥያቄዎችን መጠየቅ እንዳለብን ይመክራል፡፡

ከላይ ስለ ጥልቅ ዲስኩር ትንተና የተለያዩ ፀሀፊዎች የተለያዩ ምልከታዎችን እና ዘዴዎችን እንዲሁም በትንተና ወቅት ልንከተል የሚገባንን የትኩረት አቅጣጫዎች አመላክተውናል፡፡ በዚሁ መሰረትበዚህ ፅሁፍ ውስጥ ከጃንሆይ የአስተዳደር ዘመን ጀምሮ እስከወታደራዊው የደርግዘመን ድረስበደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የተፃፉ መደበኛ የቢሮ ደብዳቤዎችን እና ማመልከቻዎችን ይሄንኑ ዘዴ በመጠቀም የሰነዶቹን መዋቅር ለመተንተን ተሞክሯል፡፡

### 3.2. የናሙና አመራረጥ

ዝርዝርና ጥልቅ መረጃዎችን በጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ በመሰብሰብየጥናቱን ዓላማ ከግብለማድረስ ጥንቃቄ የተሞላበት የጥናቱን የትኩረት አቅጣጫ በተፈለገው እና ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ ለማስኬድ የሚያስችል የናሙና አመራረጥ አስፈላጊ ጉዳይ እንደሆነ በዘርፉ ምርምር ያደረጉ አጥኚዎች ያስረዳሉ (Zolta 2001)::

አንድ አጥኚ በሚያጠናው ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ያሉትን ሁሉንም የጥናቱን አካላዮች (research population) ማካተትከዋጋ እና ከተደራሽነት አኳያ አስቸጋሪ ነው፡፡ በዚህ የተነሳ በአብዛኛው ጊዜ አጥኚዎች ለጥናታቸው ምቹ የሆነውን የናሙና ዘዴ በመምረጥ ለጥናት ከታሰበው ርዕስ ጋር ካለው የጥናቱ አካላዮች (research population) ውስጥ ወካይ ናሙናዎችን በመምረጥና በናሙናነት በመውሰድ ጥናታቸውን ያስኬዳሉ፡፡ በጥናት ናሙና መረጣ ወቅት ወካይ ናሙናዎችን በጥንቃቄ እና በአግባቡ መምረጥ የጥናቱን አላማ ከግብ ለማድረስ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው ባለሞያዎች ያስረዳሉ፡፡ በተቃራኒው የተሳሳተ

እና ተገቢውን ውክልና ባልያዙ ናሙናዎች የሚሰራ ጥናት የጥናቱን አላማ በተሳሳተ መንገድ ከማስተላለፍ ባለፉ እውነተኛ ያልሆነ እና የተዛባ (distorted) መረጃ እና እውቀት ለህብረተሰቡ ያስተላልፋል (Anol Bahttacherjee 2012)::

በናሙና መረጣ ወቅት የናሙና መረጣ ሂደት (Sampling process) ከፍተኛ ትኩረት ልንሰጣቸው ከሚገቡ ነጥቦች መካከል አንዱ ነው፡፡ በናሙና መረጣ ሂደት ወቅት አጥኚው የሚያጠናው ወይም ለጥናቱ አትኩሮት ያደረገበትን የጥናት አካላይ (study population) ማወቅ እና መረዳት ይኖርበታል (Anol Bhattacherjee 2012):: ለምሳሌ በዚህ ጥናት ውስጥ አጥኚዋ ትኩረት ያደረገችበት የጥናት አካላይ (study population) በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ከኃይለሥላሴ ዘመን እስከ ወታደራዊው ደርግ ዘመን የተፃፉ መደበኛ የቢሮ ደብዳቤዎች እና ማመልከቻዎች ናቸው፡፡ በሌላ በኩል በናሙና መረጣ ወቅት መደረግ ያለበት ነገር አጥኚው/ዋ ለሚያጠናው ጥናት ምቹ የሆነውን መምረጥ እና ቁጥራቸው ምን ያክል መሆን እንዳለበት መወሰን ነው (Chinelo Igwenagu 2016,)::

በዚሁ መሰረት ይህንን ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዘመን እስከ ወታደራዊው የደርግ ስርአት ድረስ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የተፃፉ የመደበኛ ደብዳቤዎች የቋንቋ አጠቃቀም ትንተና ጥናት ለማድረግ በአጥኚዋ የተመረጠው የናሙና አመራረጥ ዘዴ የአመቺ ናሙና ዘዴ ነው፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥ የአመቺ ናሙና ዘዴ የተመረጠው አላማ ተኮር የሆነ አካሄድ ማድረግ ወይም በአንድ ቦታ ላይ ብቻ የተፃፉ ደብዳቤዎችን መተንተን በጥናቱ ውስጥ የተካተቱ ሌሎች ቦታዎች ላይ በጥናቱ የጊዜ ወሰን ውስጥ ያሉ ማመልከቻዎች እና የቢሮ ደብዳቤዎች ተገቢውን ውክልና እንዳያገኝ ሊያደርግ ስለሚችል ትንተናው የአንድ አቅጣጫ ዕይታ ብቻ እንዳይዝ የታቀደበመሆኑ ነው፡፡

## 3.3. የመረጃ ምንጮች

በዚህ ጥናት ውስጥ አጥኚዋ ለጥናቱ አስፈላጊ እና ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችን ከቀጥተኛ ምንጮች ለማሳሰብ ሞክራለች፡፡በጥናቱውስጥ አጥኚዋ በቀጥተኛ ምንጭነት የተጠቀመችው በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ከ1922-1983 ዓ.ም. ድረስ የተፃፉ የስራ ደብዳቤዎችን እና ማመልከቻዎችን ሲሆን ሰነዶቹንም ከጅማ ከተማ አስተዳደር ፅህፈት ቤት የመዝገብ እና ሰነድ ማከማቻ፣ ከጅማ ማዘጋጃ ቤት የሰነድ እና መዝገብ ቤት፣ አዲስ አበባ ከሚገኘው ወልደመስቀል ታሪኩ የሰነድ ማእከል እና ከግለሰቦች ከምችት የአመቺ ናሙና ዘዴ በመጠቀም ከሰበሰበች በኃላ የጥልቅ ዲስኩር ትንተና መርህን በመጠቀም የዘመኑን መንፈስ ለመተንተን ሞክራለች፡፡

ከዚህ ባለፈ ለዚህ ጥናት በምንጭነት አገልግሎት ላይ የዋሉ የቀጥተኛ ምንጮች በዚህ ፅሁፍ መጨረሻ በማስረጃነት በአባሪ መልክ እንዲቀመጡ ተደርጓል፡፡ ይህም በትንተናው ወቅት ለሚነሱ አንዳንድ አዳዲስ ገለፃዎች እና ሀሳቦች ጥርጣሬ ያላቸው አንባቢዎች ወይም በጉዳዩ ዙሪያ ጥናት ለማድረግ ላሰቡ ግለሰቦች በአስረጂነት እንዲያገለግል በማሰብ ነው፡፡ እንደሚታወቀው በአንድ ጥናት ውስጥየቀጥተኛ ምንጭን በተገቢው እና በአግባቡ መቀጠም ለጥናቱ ጥሩ ውጤት እና ያልተዳሰሱ ነጥቦችን ለመዳሰስ ጥሩ መነሻ ይሆናል ተብሎ ይታሰባል፡፡ በዚሁ መሰረት አጥኚዋ የዚህን ጥናት የትንተናክፍል በዋና ምንጭነት የቀጥታ ምንጮችን ተጠቅማለች፡፡

## 3.4. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ

ለዚህ ጥናት ከግብ መድረስ አጥኚዋ ቀጥተኛ የመረጃ ምንጮችን እንደምትጠቀም ቀደም ባለው ርዕስ ላይ ተገልጿል፡፡ እነዚህ መረጃዎች የሚሰበሰቡት በምን አይነት መልኩ እንደሆነ፣ ለጥናቱ የሚውሉት ጥያቄዎች የጥናቱን አላማ ከግብ ከማድረስ አኳያ በምን መልኩ እንደሚሰነድ፣ ጥናቱን ለመስራት የሚያግዙ መሰረታዊ ጥያቄዎች ምን ያክል እንደሆኑ እና በጥናቱ ውስጥ በመሪ መጠይቅነት የቀረቡት ጥያቄዎች በምን መልኩ እና በማን እንደቀረቡ ለማመላከት ነው (Creswell 2007)::

ይህ ጥናት በመረጃ አሰባሰብ ዘዴው ዓይነታዊ የምርምር ዘዴን የሚከተል በመሆኑ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎቹ በጥናቱ ዓይነት የተወሰኑና በአይነት የሚሰበሰቡ ናቸው፡፡ በዚሁ መሰረት ይህ ጥናት በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የአስተዳደር ዘመን ጀምሮ እስከ ወታደራዊው የደርግ የአስተዳደር ዘመን ድረስ የተፃፉ መደበኛ የቢሮ ደብዳቤዎች ቋንቋ አጠቃቀም ትንተና ያደረገ በመሆኑ ለዚሁ ስራ የሚውሉ መረጃዎችን ከጅማ ከተማ አስተዳደር የሰነድ ማከማቻ ማዕከል፣ ከጅማ ከተማ ማዘጋጃ ቤት የሰነድ ማከማቻ ማዕከል፣ ከወልደመስቀል ታሪኩ የሰነድ ማከማቻ ማዕከል፣ ከተለያዩ ግለሰቦች የግልሰነድ ክምችት ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ የቀጥተኛ መረጃዎችን(Primary Sources) በመውሰድ ለጥናቱ በግብአትነት እንዲውሉ ተደርገዋል፡፡ በአጠቃላይ የጥናቱ ዋና አላማ ከ1922-1983 የተፃፉ መደበኛ ደብዳቤዎችን እና ማመልከቻዎችን ቃላት አጠቃቀም እና አጠቃላይ ይዘት ትንተና የሚያደርግ በመሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ዋነኛው እና አስፈላጊው ዘዴ የመዛግብት ፍተሻን መጠቀም ነው፡፡ ስለዚህም ቀጥተኛ መረጃዎችን ከተለያዩ ተቋማት በፎቶ፣ በኮፒ፣ በንባብ፣ በፅሁፍ በመሰብሰብ እንዲተነተኑ ተደርጓል፡፡ በዚህ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ላይ ቃለ መጠይቅ ተጨማሪ ሆኖ ሊያገለግል ይችል ነበር፡፡ ነገር ግን በዘመኑ የነበሩ ማመልከቻ ፀሐፊዎችና ታሪክ አዋቂ ሰዎች በእድሜ በጣም የገፉ ሊሆኑ እንደሚችሉ ከግንዛቤ በማስገባት ሰነድ ፍተሻ ላይ ብቻ ተተኩሯል፡፡

### 3.4.1. ሰነድ ፍተሻ (document analysisi)

ለዚህ ጥናትበዋነኛነት መረጃዎችን ከማስገኘት አንፃር ጥናቱን ስኬታማ ያደርጋል በሚል የተመረጠው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የሰነድ ፍተሻ ነው፡፡ በዚህ ጥናት ላይ አጥኚዋ የሰነድ ፍተሻ ዘዴን እንድትጠቀም ካደረጓት ምክንያቶች አንዱ የጥናቱ ርዕስ በቀደሙት የኢትዮጵያ የፖለቲካ አስተዳደር ዘመን የተፃፉ መደበኛ የቢሮ ደብዳቤዎች ቋንቋ አጠቃቀም ከዘመኑ መንፈስ አኳያ ምን ይመስል እንደ ነበር ለማየት በመሆኑ እናበዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ትንተና ለማድረግ የሰነድ ፍተሻ ዘዴ መጠቀም አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ በጥናቱ ውስጥ እንዲተገበር ተደርጓል፡፡ በዚሁ መሠረት ጥናቱ ከሚያካትታቸው አካባቢዎች የተሰበሰቡ የተለያዩ የቢሮ ደብዳቤዎች ስራ ላይ እንዲውሉ ተደርጓል፡፡ እነዚህ ደግሞ ያለው እንዳወቅ /2006/ በመዛግብት ፍተሻ ስር የሚጠቃለሉ መሆናቸውን ያብራራል፡፡

በዚሁ መሠረት ከጃንሆይ ዘመን ጀምሮ እስከ ወታደራዊው የደርግ ስርአት የተፃፉ መደበኛ የቢሮ ደብዳቤዎችን ለመመተንተን የሰነድ ፍተሻ /ትንተና/ እንዲተገበር ተደርጓል፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥ ከ1922-1983 ባሉት ጊዜያት መካከል የተፃፉ 15 መደበኛ የቢሮ ደብደቤዎችን በመሰብሰብና በሰነዶቹ ላይ የጥልቅ ዲስኩር ትንተና መርህ በመጠቀም ከማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ አንድምታ አኳያ ተገቢውን ትርጉም እንዲይዙ በማድረግ ተተንትኗል፡፡ በሰነድ ፍተሻ ወቅት አጥኚዋ የተሰበሰቡትን የመደበኛ የቢሮ ደብዳቤዎች መዋቅር የመደበኛ የቢሮ ደብዳቤ አፃፃፍ ስልትን ከግምት በማስገባት እና ደብዳቤዎቹ እና ማመልከቻዎቹ ከተፃፉበት የጊዜ መንፈስ አኳያ ምን አይነት መልዕክት እንዳላቸው ለመፈተሽ ተሞክሯል፡፡ ለምሳሌ በደብዳቤው ላይ የተለጠፈውን ቴምብር አርማ፣ በቴምብሩ ላይ የተፃፉትን ፅሁፎች፣ በራስጌ እና በግርጌ መሀተሞች

ላይ ያሉትን አርማዎች እና ፅሁፎች ወዘተ ከግምት በማስገባት በነዚህ ምልክቶች፣ አርማዎች እና ፅሑፎች ጀርባ ያሉ መልዕክቶችን ለመፈተሽና ለመተንተን ተሞክሯል፡፡ በሌላ አቅጣጫ አጥኚዋ የደብዳቤዎቹን ውስጣዊ ይዘት በምትፈትሽበት ወቅት የተለያዩ የኢ-ቀጥተኛ መረጃዎችን በማንበብ እና ለጥናቱ በቀጥተኛ መረጃነት ከተሰበሰቡ ደብዳቤዎች እና ማመልከቻዎች ጋር በማሰናሰል የደብዳቤዎቹን ውስጣዊ ይዘት ለመፈተሽ /ለመተንተን/ ተሞክሯል፡፡ ለምሳሌ በውስጣዊ ይዘት ፍተሻ ወቅት አጥኚዋ ፍተሻውን /ትንተናውን/ ደብዳቤዎቹን ከተፃፉበት የዘመን መንፈስ አኳያ የቃላት አጠቃቀማቸውን፣ የጥቅል ሀሳብ መልዕክታቸውን እና አገላለፃቸውን፣ በፅሁፉ ውስጥ ለሰፈረው ሀሳብ ባለቤት አሰያየማቸውን፣ የአያያዥ እና የአፍራሽ ቃላት አሰያየማቸውን፣ ከፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ከማህበራዊ ፅንሰ ሀሳብ አኳያ ከጀርባቸው ያዘሉትን ትርጉም ወዘተ ለመፈተሽ እና ለመተንተን ተሞክሯል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አጥኚዋ ሰነዶቹን በምትመረምርበት ወቅት ማመልከቻው ወይም ደብዳቤው በተፃፈበት ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ፀሀፊው ስለ ጉዳዩ ያሰማውን ድምፀት(tone) በጥልቀት በመፈተሽ ሰነዶቹ በተፃፉበት ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ለጉዳዩ ባለቤት የሆኑ አካላት ወይም ተቋማትበምን መልኩ እንደተሳሉ እና እንደተወከሉ በሰነድ ፍተሻ ወቅት ትኩረት ለመስጠት ሞክራለች፡፡

## 3.5. የመረጃ መተንተኛ ዜዴ

የአንድ አጥኚ ብስለት እና ምርምር የማድረግ ክህሎት ከሚለካባቸው ነጥቦች መካከል የተለያየ መንገድ ተጠቅሞ የሰበሰባቸውን መረጃዎች ለመተንተን የሚዘይደው ዘዴ አንዱ ነው፡፡ ምክንያቱም በአንድ ጥናትውስጥ መረጃ መሰብሰብ ወሳኝ ቢሆንም መረጃውን ተገቢውን የትንተና ዘዴ ተጠቅመን ወደ ፍቺ ያለው ወይም ትርጉም ያለው መረጃ ካልቀየርነው ሁሉም ነገር ከንቱ መሆኑን አጥኚዎች ይገልፃሉ፡፡ በዚህ የተነሳ አንድ አጥኚ ወይም ተመራማሪ የሰበሰበውን መረጃ መተንተን ከመጀመሩ በፊት ለሰበሰበው መረጃ ተስማሚ የሆነውን የትንተና ዘዴ መምረጥ ይኖርበታል፡፡ ይሄም የሚደረገው ጥናቱ በመነሻ በጥያቄነት የያዛቸውን ነጥቦች ግባቸውን እንዲመቱ ለማድረግ ነው፡፡ በመረጃ ትንተና ወቅት ለጥናቱ በቀጥተኛ ምንጭነት የሚያገለግሉትን መረጃዎች በጥናቱ ውስጥ በምንጭነት ከሚያገለግሉ መረጃዎች ጋር በምን መልክ መሰናሰል ወይም ተግባብተው አብረው መሄድ እንዳለባቸው አጥኚው የጥናቱን ትንተና ከመጀመሩ ቀደም ብሎ በጥልቀት ማሰብ እና በተመሳሳይ ርዕሰ ጉዳይ ላይ የተጠኑ ሌሎች የጥናት ውጤቶች በምን መልኩ እንደተሰሩ በምሳሌነት በማንበብ ለችግሩ መፍትሄ ማበጀት ይኖርበታል፡፡ ነገር ግን ትንተናው ከተጀመረ በኃላ የትንተና ዘዴን ከተሰበሰበው መረጃ ጋር አብሮ አለመሄድን መረዳት ከፍተኛ ጉዳት ያስከትላል፡፡ ምርምሩም አላማውን እንዳይመታ ያደርጋል ( Simon Hearn and Jessicasinclari, 2014,)፡፡

ይህ ጥናት አይነታዊ የምርምር አይነት በመሆኑ እና በተፃፉ ሰነዶች ላይ ትኩረት ተደርጎ የሚሰራ በመሆኑ መረጃዎች በገለፃ እና በፍከራ ዘዴዎች ይተነተናሉ፡፡ በዚሁ መሠረት ከላይ እንደተገለፀው በዚህ ጥናት ውስጥ መረጃዎችን በሰነድ ፍተሻ የተሰበሰበ መሆኑ ተገልጿል፡፡ በመሆኑም ከሰነድ ፍተሻ የተገኙ መረጃዎችን አይነታዊ የትንተና ዘዴዎች ብዙ በመሆናቸው ገለፃንና ፍከራን በመጠቀም መረጃዎችን ግልፅ እና ፍትሀዊ በሆነ መንገድ በአጥኚዋ ለመተንተን ተሞክሯል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አይነታዊ የትንተና ዘዴ የሚጠናውን ጥናት ከተለያዩ አቅጣጫዎች በጥልቅ በመመርመርና በስፋት በመዳሰስ አንባቢው ለሚያነሳቸው ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት አመቺ በመሆኑ Mason (1996) Creswell (2007) ይገልፃሉ፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥ ይህንን የመረጃ መተንተኛ ዘዴ በመጠቀም የተሰበሰቡ ሰነዶችበዚሁ ዘዴ መሠረት ለመተንተን ተሞክሯል፡፡

እነዚህ በሰነድ ፍተሻ የተገኙ መረጃዎች ምንጮቻቸው በተለያየ ቦታ የሚገኙ የሰነድ ማከማቻ ተቋማት፣ ክፍሎች እና ግለሰቦችን በዋናነት መጥቀስ ይቻላል፡፡ ለምሳሌ አጥኚዋ በደቡብ ምዕራብኢትዮጵያ ከ1922-1983 ዓ.ም. የተፃፉ መደበኛ የስራ ደብዳቤዎች ቋንቋ አጠቃቀም ትንተና በሚለው ርዕስ ላይ በወቅቱ የተፃፉ ደብደቤዎችን ከጅማ ዞን አስተዳደር የሰነድክምች ትክፍል፣ ከጅማ ከተማ አስተዳደር የሰነድ ክምችት ክፍል፣ ከወልደመስቀል ታሪኩ የሰነድ ማከማቻ ማዕከል እና ከግለሰቦች እጅ በመሰብሰብ የገለፃና የፍከራ ትንተና ዘዴን በመከተል እንዲተነተኑ ተደርጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የቀጥተኛ መረጃዎችን ለማጠናከር እና የሚተነተነውን ሀሳብ ይዘት ለማጠናከር መረጃዎችን ከመጽሐሀፍት፣ ከመፅሄቶች፣ በተለያየ ደረጃ ከተሰሩ የመመረቂያ ፅሁፎች፣ ከጋዜጦች ወዘተ በመውሰድ ለትንተናው በግበአትነት እንዲያገለግሉ ተደርጓል፡፡ በዚሁ መሠረት በዚህ ጥናት ውስጥ ከተለያዩ ተቋማት እና ድርጅቶች እንዲሁም ከግለሰቦች እጅ የተገኙትን እና ለጥናቱ በዋና መረጃነት የሚውሉትን አስራ አምስት መደበኛ የቢሮ ደብዳቤዎች አንዱን ከሌላው በማመሳከር፣ ጥልቅ ምልከታ እና ምክንያታዊ እይታ በማድረግ ለአንባቢው በማይጐረብጥ እና በማያምታታ መልኩ መልዕክት አዘል ትንተናን ለማስተላለፍ ተሞክሯል፡፡ በአጠቃላይ ከተለያዩ የሰነድ መጠበቂያ ተቋማት እና አብያተ መፅሀፍት በሰነድ ወይም በመዛግብት ፍተሻ የተሰበሰቡ ቀጥተኛ መረጃዎች ከጥናቱ አላማ እና ጥያቄ ውጭ ያፈነገጠ መልዕክ ትያላቸው መረጃዎችን በማጣራት እንዲወገድ ተደርጓል፡፡ ከዚህም ባለፈ በመረጃ ትንተናው ወቅት የትንተና ማጠቃለያ ከመደራጀቱ በፊት በትንተናው ወቅት የተሰሩ አላስፈላጊ ስህተቶችን በማጣራት ስህተቶቹን ለማስወወገድ ጥረት ተደርጓል፡፡ ከተሰበሰቡት መረጃዎች በመነሳት ምክንያታዊ እና ጥያቄ መላሽ ወደሆነ የትንተና ማጠቃላያ ላይ ለመድረስ ተችሏል፡፡

## 3.6. የጥናቱ አካሄድ

በዚህ ጥናት ውስጥ በመሪነት የቀረቡ ጥያቄዎችን ለመመለስ እና የጥናቱን አላማ ከግብ ለማድረስ አጥኚዋ የዚህን ጥናት ሂደቶች በሶሶት ዋና ዋና ክፍሎች ከፍላ ለመስራት ሞክራለች፡፡ በዚሁ መሠረት የመጀመሪያው ሂደት በቅደመ መረጃ ስብሰባ ወቅት የተደረገ ሂደት ወይም ከመስክ የመረጃ ስብሰባ ሂደት በፊት የተደረገ ተግባር ነው፡፡ ሁለተኛው ሂደት በመረጃ ስብሰባ ወቅት የተደረገ እንቅስቃሴ ሲሆን ሶስተኛው የጥናት ሂደት ክፍል ደግሞ ከመስክ መረጃ ስብሰባ በኃላ የነበረውን የጥናት ሂደት የሚያካትት ነው፡፡

### 3.6.1. ቅድመ መረጃ ስብሰባ

አጥኚዋ ከመስክ የመረጃ ስብሰባ ሂደት በፊት አንድ አንድ ተግባራትን ለመከወን ሞክራለች፡፡ ከነዚህ ተግባራት መካከል ዋና ዋናዎቹ የመስክ መረጃ ስብሰባ ስለሚደረግባቸው ተቋማት እናለ ቦታዎች በቂ መረጃ መሰብሰብ ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በመስክ የመረጃ ስብሰባ ወቅት ለመረጃ አቀባይ ተቋማት የሚሆን ህጋዊ ደብዳቤ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡ ለመስክ መረጃ ስብሰባው የሚያስፈልጉ ግብአቶች እንደ ደብተር፣ እስኪብርቶ፣ ወረቀት፣ እርሳስ፣ የፎቶ ማንሻ ካሜራ እና መረጃዎቹ የሚገኙበት ተቋምን መገኛ የሚያሳይ አጭር የፅሁፍ መግለጫ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አጥኚዋ በሁሉም የጥናቱ ክፍሎች ላይ የጥናቱን አላማ አና ጥናቱ ሊመልሳቸው የተዘጋጀባቸውን መሪ ጥያቄዎች ደጋግማ ደጋግማ በማስታወስ ከጥናቱ ጋር ውህደት ለመፍጠር እና ጥናቱ መስመሩን እንዳይለቅ ወይም በእንግሊዘኛው (Line of inquir) የሚባለውን እንዳይስት ጥረት አድርጋለች፡፡ ከዚህ በተጨማሪበዚህ በመጀመሪያው የቅድመ መረጃ ስብሰባ የጥናት ሂደት ውጤት አጥኚዋ ጥናቱን በምታደርግበት ወቅት የሚያጋጥማትን ማንኛውንም እንቅፋት እና ፈተና በታጋሺነት ለመወጣት የስነልቦና ዝግጅት እና መነሳሳት አድርጋለች፡፡

### 3.6.2. የመስክ መረጃ ስብሰባ ሂደት

በሁለተኛው እና በመስክ የመረጃ ስብሰባ ወቅት በቅድመ የመስክ ስራ ለመስኩ የመረጃ ስብሰባ ይጠቅማሉ የተባሉት ግብአቶች እና ዝግጅቶች እንዳይረሱ በወረቀት በመፃፍ እና መኖራቸውን በማረጋገጥወደ ስራ ተገብቷል፡፡ ከዚህ በመቀጠል ለመስክ የመረጃ ስብሰባ የተፃፉትን ደብዳቤዎ ች ለሚመለከታቸው ተቋማት በመስጠት ፍቃድ ለማግኘት ተችሏል፡፡ በዚህሂደት ውስጥ ከፍተኛ ችግር የነበረው በዚህ ጥናት ውስጥ በግብአትነት የሚውሉት በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ እና በደርግ ዘመን የተፃፉ ደብዳቤዎች በመሆናቸው በአንዳንድ ተቋማት ውስጥ እነዚህ ደብዳቤዎች በአንድ ክፍል ውስጥ ለረጅም አመታት ሳይከፈቱ በመቆየታቸው ሰነዶቹን በቀላሉ ለመለየት አስቸጋሪ መሆኑ ነበር፡፡ ከዚህ ባለፈ ሰነዶቹላሉበት ክፍል በሀላፊነት የተሰየመ ሰው ባለመኖሩ አብዛኛውን ጊዜ የጥበቃ ሰራተኞች ናቸው በሩን በመክፈት የሚያገለግሉት፡፡ በአንዳንዶቹ ተቋማት ደግሞ ሰነዶቹ ያሉበት ክፍል ለረጅም ጊዜ ባለመከፈቱ የክፍሉ ቁልፍ እስከመጥፋት እና ማንጋ እንደለ ያለመታወቅ አጋጣሚም ተከስቷል፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት በሚደረግበት እና የመስክ ስራ በሚሰራበት ወቅት በተለያዩ ምክንያቶች ሰነዶቹ በቀላሉ ማግኘት አስቸጋሪ ነበር፡፡ የሆነው ሆኖ አጥኚዋ በመስክ ስራ ወቅት የተለያዩ መሰናክሎችን በማለፍ ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑትን ሰነዶች ከሚገኙባቸው የተለያዩ ተቋማት ኮፒ በማድረግ ፎቶ በማንሳት እና አጫጭር ማስታወሻዎችን በመያዝ ሰብስባለች፡፡ በሌላ በኩል በመስክ መረጃ ስብሰባ ወቅት መረጃዎችን ለመሰብሰብ የተለያዩ አብያተ መጻሕፍቶችን ለመፈተሽ እና ከሚጠናው ርዕሰ ጉዳይ ጋር ቀረቤታ ያላቸውን የጥናት ውጤቶች በኮፒ መልክእና አጫጭር የእጅ ፅሁፎችን በመፃፍ ለማስቀረት ጥረት ተርጓል፡፡

### 3.6.3. ድህረ መረጃ ስብሰባ

ከመስክ የመረጃ ስብሰባ በኃላ በመስክ የመረጃ ስብሰባ ወቅት የተሰበሰቡ ቀጥተኛ እና ኢ-ቀጥተኛ መረጃዎችን በዘርፍ በዘርፋቸው ወይም በፈርጅ በፈርጃቸው በመለየት እና እላያቸው ላይ መለያ /ኮደ/ በመፃፍ ለጥናቱ ዝግጁ እንዲሆኑ ተደርገዋል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ የተደረገው አጥኚዋ በየፈርጃቸው የተቀመጡትን የቀጥተኛ መረጃዎች ደጋግማ በማንበብ ከጥናቱ አላማ እና ጥያቄዎች ጋር ግንኙነት እንዲፈጠር ማድረግ እና ሀሳቡን በደንብ ማብላላት ነበር፡፡ በዚሁ መሰረት በተለይ ለጥናቱ በግብአትነት የሚውሉትን ደብዳቤዎች እና ማመልከቻዎች ከተፃፉበት የዘመን መንፈስ አኳያ ለመረዳት ተደጋጋሚ የሆነ እና ጥሞና የተሞላበት ንባብ እንዲነበብ ተደርጓል፡፡ ይህንን ማድረግያስፈለገው ጥናቱ የታለመለትን መስመር እንዳይስት በማሰብ ነው፡፡

ከበቂየ ድግግሞሽ ንባብ እና ማብራራት በኃላ የተሰራው ስራ የቅድመ መረጃ ትንተና ስራነው፡፡ በዚህ ወቅት አጥኚዋ መረጃውን በምትተነትንበት ጊዜ ትኩረት መስጠት ያለበትን ነጥቦች እንዳይረሱ በመስፈርትነት በፅሁፉ በመዘርዘር ሰነዶቹ ከመስፈርቶቹ አኳያ ምን አይነት አንድምታ እንዳላቸው ለመገምገም ጥረት አድርጋለች፡፡ በዚህ መሠረት የማብላላት፣ የማጣራት እና የማዋቀር ስራዎችን በአግባቡ እንዲሄዱ ከተደረገ በኃላ ለተሰበሰቡት መረጃዎች የመረጃ ትንተና ትርጉማ በመስጠት ለጥናቱ ማጠቃለያ ለመስጠት ተችሏል፡፡

## 3.7. የጥናቱ ተአማኒነት መለኪያ (Validity)

የአንድን ጥናት ተአማኒነት (validity) መለካትን በተመለከተ Jacques Barzun እና Henry F. Graff የተባሉ ፅሁፎች modern Research በሚለው መፅሀፋቸው ላይ እንደሚገልፁት አንድ ተመራማሪ ከሚፅፈው ፅሁፍ ወይም ከሚሰራው ምርምር ጋር በተያያዘ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መጠየቅ ይኖርበታል፡፡ እየተፃፈ ያለው ወይም እየተተነተነ ያለው ሀሳብ እውነተኛ፣ የሚታመን እና ሙሉ (complete) ነው?፣ እየተፃፈ ያለው ፅሁፍ ግልፅ፣ ለግንዛቤ የማያስቸግር /ያልተወሳሰበ/ እና

ለማስታወስ ቀላል ነው? እንዲሁም ለፅሁፉ በግብአትነት የዋሉት መረጃዎች ከሚፃፈው ርዕሰ ጉዳይ ጋር ግንኙነት አላቸው? የሚሉትን ጥያቄዎች ደጋግሞ በመጠየቅ እና ለጥያቄዎቹ የተዛባምላሽ እንዳይሰጥ በመጠንቀቅ የአንድ ጥናትንተአማኒነት ከፍ ማደድረግ ይቻላል (Jacques Barzun and Henry F. Graff, 1993)፡፡

በዚህ መሠረት በዚህ ጥናት ውስጥ የጥናቱን ተአማኒነት ከፍ ለማድረግ በማሰብ ለጥናቱ በግብአትነት እንዲውሉ የተሰበሰቡትን መረጃዎች ከጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ጋር አብረው መሄድ አለመሄዳቸውን ፍተሻ በማድረግ ለጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ በመረጃነት ለማዋል ከላይ በተዘረዘሩት መለኪያዎች በመለካት አስፈላጊ ያልሆኑት መረጃዎች እንዲቀነሱ ተደርጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የጥናት ስራዉን የተወሳሰበ መላ ምቶችን ባለመጠቀም ለአንባቢው ግልፅ እና ለመረዳት የማያስቸግር ለማድረግ ጥረት ተደርጓል፡፡ ይህም በተሰነዘሩት ሀሳቦች ዙሪያ አንባቢው ግልፅ መረጃ እንዲያገኝ በማድረግ እና ከጥርጣሬ እንዲርቅ በማድረግ እምነቱን ከፍ ለማድረግ በማሰብ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የተሰበሰቡትን ቀጥተኛ መረጃዎች በተለያየ መልኩ መስቀለኛ ጥያቄዎች ውስጥ በማስገባት ከጥናቱ አላማ እና ከጥናቱ መሪ ጥያቄዎች ጋር በምክንያታዊ እና በጥያቄ መላሽነት ግንኙነት ያላቸውን መረጃዎች በመውሰድ የጥናቱን ተአማኒነት ለማጉላት ጥረት ተደርጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የጥናቱን ተአማኒነት ከፍ ለማድረግ የጥናቱን ፍሬ ሀሳቦች በመልክ በመልካቸው የተለያዩ አርዕስቶች በመስጠት እንዲተነተኑ ተደርጓል፡፡ ከላይ የተጠቀሱትን የጥናት ተአማኒነት መጨመሪያ በጥናቱ ውስጥ ለመተግበር ከተሞከረ በኃላ እና በመረጃዎቹ መሠረት ትንተና ከተደረገ በኃላ ማጠቃለያ ላይ ለመድረስ ተችሏል፡፡

## 3.8. የምርምር አከናወን ስነ ምግባራዊ ጉዳዮች (Ethicla concideration)

በምርምር ወቅት ስነ ምግባራዊ ጉዳዮችን በተመለከተ Mason የተባለ ፀሀፊ Qualitative Research በሚል ርዕስ ስር በፃፈው ፅሁፍ ላይ እንዳመለከተው አንድ አጥኚ አይነታዊ ጥናት በሚያደርግበት ወቅት የተጠኚውን አካል ግላዊ እና ቡድናዊ መብት፣ ፍላጐት እና ባህል የማክበር ሞያዊ እና ሞራላዊ ግዴታ እንዳለበት ይገልፃል (Mason 1996.)::

በዚሁ መሠረት አጥኚዋ ጥናቱን በምታደርግበት ወቅት የሚጠኑ የማህበረሰብ ክፍሎች በማስረጃነት በተሰበሰቡት ደብዳቤዎች በተፃፉበት የዘመን መንፈስ ትክክለኛ አገላለፅ የነበሩ ነገር ግን አሁን ባለንበት የዘመን መንፈስ ደብዳቤዎቹ ገለፃዎቻቸው ወይም የቃላት ውክልናዎቻቸው የማይፈልጓቸው በመሆኑ በትንተና ወቅት በደብዳቤው ውስጥ ያሉትን የቀድሞ የቃላት ውክልናዎች እና አገላለፆች ደብዳቤዎቹ በተፃፉበት ማህበረሰብ ተቀባይነት ያላቸውን አዳዲስ የቃላት ውክልናዎችን በመጠቀም በመተካት ተሞክሯል፡፡ በሌላ በኩል ፀሀፊዋ በመረጃ ስብሰባ ወቅት መረጃ የሚሰበሰብባቸውን ተቋማት ህግና ስርአት በሚፈቅደው መሰረት ለመንቀሳቀስ ሞክራለች፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ የጥናቱ ርዕስ የቆዩ ደብዳቤዎችን ምርመራ የሚያደርግ በመሆኑ መረጃውን የሚፈቅዱት አካላት ጥርጣሬ ውስጥ በሚገቡበት ወቅት ስለጥናቱ ሁኔታ እና አላማ የጥናቱ ስነ ምግባር በሚፈቅደው መሠረት በትዕግስት ማብራሪያ ለመስጠት ተሞክሯል፡፡

# ምዕራፍ አራት

## 4. በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ከ1922-1983 ዓ.ም ድረስ የተፃፉ ደብዳቤዎች ቋንቋ አጠቃቀም ይዘት ትንተና

### 4.1. በጃንሆይ ዘመን በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የተፃፉ ደብዳቤዎች ቋንቋ አጠቃቀም ይዘት ትንተና

#### 4.1.1. ፖለቲካዊ ጉዳዮች ትንተና

በጃንሆይ ዘመን በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የተፃፉ ደብዳቤዎች የቋንቋ አጠቃቀም ይዘት ከፖለቲካዊ አንድምታቸው አንፃር በምንመረምርበት ጊዜ በዘመኑ የነበረውን የመደብ የበላይነት እና የበታችነት እንዲሁም ተያያዥ ትግሎችን አመላካች ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡በዚሁ መሠረት በአብዛኛዎቹ ደብደቤዎች ላይ በፖለቲካ እና በመደቡ ከፍ ያለው የማህበረሰብ ክፍል የክቡርነት፣ የጌትነት፣ የልበ ብርሃንነት፣ የአዋቂነት፣ የወርቅነት፣ የእንቁነት፣ የፍትህ ምንጭነት፣ የአስተዋይነት፣ የሃሳብ አመንጭነት እና ችግር ፈችነት፣ የደፋርነት እና ምህረት ሰጭነት ውክልና ሲሰጠው፤ በታችኛው የመደብ ዕርከን ላይ ያለው የማህበረሰብ ክፍል ደግሞ በአንፃሩ የደካማነት፣ የአላዋቂነት፣ የችግር ፈጣሪነት፣ የምህረት ጠባቂነት ወዘተ ወክልና ተሰጥቶት እናገኛለን፡፡ ይህ አይነት ውክልና በወቅቱ ሳይታሰብበት እንዲሁ በዘፈቀደ የዳበረ እና ያደገ ሳይሆን ታስቦበት እና ታቅዶ የታችኛውን የመደብ ክፍል በአላስፈላጊ ፍረጃ በመተብተብ የላይኛወን መደብ የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ የበላይነት እንዳይጋፋ እና የበላይነትን ለማስቀጠል ከማሰብ የመነጨ ፍላጎት ነው ብለን መናገር እንችላለን፡፡

በሌላ በኩል በጃንሆይ ዘመን በተፃፉ ደብዳቤዎች ላይ የተፃፉት ደብዳቤዎች በራስጌ አርማነት የሚጠቀሙትን ምልክት ከአባሪ ቁጥር አንድ እስከ ዘጠኝ ባሉት ላይ በምናይበት ጊዜ የዘውዳዊውን የፖለቲካ ስርዓት የሚያሳይ እና በቀኝ የፊት እግሩ አናቱ ላይ የመስቀል ቅርፅ ባለው ረጅም ብረት መሳይ ዘንግ የኢትዮጵያን ሠንደቅ አላማ ያነገበ ጎፈር ያለው አንበሳ ይታያል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በጎፈራሙ አንበሳ ጭንቅላት ላይ የዘውድ ዙፋን ተደፍቶ ይታያል፡፡ ይህ እንግዲህ የሚያሳየው በወቅቱ የነበረው የፖለቲካ ስርዓት ራሱን ሞአ አንበሳ ወይም የይሁዳ አንበሳ ብሎ በመሰየም የስርዓቱን ሀያልነት እና አይበገሬነት በህዝቡ ውስጥ ለማስረፅ በማሰብ እና ህዝቡን ፀጥ ረጭ አድርጎ ለመግዛት ከማሰብ ይመስላል፡፡ በሌላ በኩል የተመረጠው አንበሳ ጎፈር ያለው መሆኑን በምናይበት ግዜ በወቅቱ የነበረው የፖለቲካ ቡድን ለፆታዊ እኩልነት የነበረውን ቦታ እንድንመለከት ያስችለናል፡፡ ምክንያቱም በራስጌ አርማነት የሚታየው ጎፈራማ አንበሳ ወንድ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በወቅቱ የወንዶች የበላይነት መኖሩን እና ሥርዓቱ ለሴቶች ዝቅተኛ ግምት ይሰጥ እንደነበር ሊያሳየን ይችላል፡፡ እንዲሁም አንበሳው በፊት የቀኝ እግሩ ባነገበው የሰንደቅ ዓላማ መያዣ ዘንግ አናት ላይ ያለው መስቀል የሚያሳየው በወቅቱ የነበረው የፖለቲካ ስርዓት ክርስትናን እንደ ብሄራዊ ሀይማኖት አውጀ ይተገብር እንደነበር ነው፡፡ በመሆኑም የሃይማኖት እኩልነትን በተመለከተ በወቅቱ ያለው ሁኔታ አድሏዊነት የሚታይበት ጊዜ ነው ማለት እንችላለን፡፡ በአንበሳው አናት ላይ የተደፋው የዘውድ ዙፋን ደግሞ ሀገሪቱ በወቅቱ ዘውዳዊ የፖለቲካ ስርዓት ተከታይ መሆንዋን ያሳየናል፡፡

በአባሪ ቁጥር አንድ ላይ የተፃፈውን ደብዳቤ ከፖለቲካዊ የቃላት አጠቃቀም ይዘት አኳያ በምናይበት ጊዜ ደብዳቤው በተፃፈበት ጊዜ የከፋ ጠቅላይ ግዛት ገዢ ለነበሩት መስፍን ስለሺ "ክቡር ጌታችን ደጃዝማች" የሚል የተደራረበ የአክብሮትና የሹመት ማዕረግ ተሰጥቶ እናገኛለን፡፡ ከእነዚህ የአክብሮት ቃላት መካከል በተለይ "ጌታችን" የሚለውን በምናይበት ጊዜ በወቅቱ የነበረው የፖለቲካ ስርዓት በገዥው እና በተገዥው መካከል የነበረውን የመደብ ልዩነት እና ጭቆና የሚያሳይ ተደርጎ ለወሰድ ይችላል፡፡ ምክንያቱም አመልካቾቹ አንድን በወቅቱ የነበረን ባለስልጣን "አምላክ" ከሚለው አገላለፅ ጋር በአንጻራዊነት

ተቀራራቢነት ባለው “ጌታችን” በሚል ማዕረግ መጥራታቸው እና ውክልና መስጠታቸው ለዚህ ሁነኛ አመላካች ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ከዚህም በወቅቱ በነበረው የፖለቲካ ስርዓት ህዝቡ ሹማምንትን ከማክበር ይልቅ ፍርሃት እንደነበረበት ያሳያል፡፡ ይህንን ቃል ሲጠቀም በሌላ ጎኑ ስለራሱ “ሎሌነት” ወይም ፍፁም ተገዥነት እያመለከትም መሆኑን ልብ ልንለው ይገባል፡፡ በተያያዥ በፖለቲካዊ እና ማህበራዊ ህይወቱ በታችኛው የመደብ ዕርከን የሚገኘው የማህበረሰብ ክፍል የድህነት እና የፍትህ ተመፅዋችነት ውክልና ተሰጥቶት እናገኛለን፡፡ ለዚህ ማጠናከሪያ “…በየስማችን አቅጣጫ የፈረምን ድሆችዎ …” እና “…መምሬ ወሰኔ በመቅረታቸው የተነሳ እኛ ድሆችዎ …” የሚሉ አገላለፆችን ማየት አመላካች ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ ይህ ከፍትህ ባለመብትነት ይልቅ የፍትህ ተመፅዋችነት፣ ከመሪ አክባሪነት ይልቅ የፖለቲካ ሹማምንትን የመፍራት ውክልና ምንጩ በፖለቲካ እርከኑ ላይ ያለው አካል የፖለቲካ ስልጣኑን ያለ ተቀናቃኝ ለማስቀጠል ከማለም የመነጨ ሊሆን ይችላል፡፡ በተመሳሳይ በደብዳቤው ላይ “የጌትነት” መአረግ ለተሰጠው ለበላይ ሹማምንት የተፃፈ ደብዳቤ መሆኑን ስንመለከት በነበረው ስርዓት እና በህዝቡ መካከል የነበረው ግንኙነት የአገልጋይ እና የተገልጋይ ሳይሆን የጌታና የሎሌ ወይም “የባርያ” እና የአሳዳሪ አይነት እንደነበር ሊያመለክት ይችላል፡፡

በአባሪ ቁጥር አንድ ላይ በቀረበው ደብዳቤ ላይ “ወርቅ አንፋሽዎ” የሚል ቃል ሰፍሮ ይገኛል፡፡ ይህ አገላለፅ የሚያሳየው አሁንም የመደብ ልዩነትን እና የላይኛው መደብ ለራሱ እንደ ወርቅ፣ አልማዝ ወዘተ ያሉ ውድ ስያሜዎችን በመስጠት የበላይነት ውክልናን ሲፈጥር በተቃራኒው ሌላው የታችኛው መደብ ደግሞ ለራሱ ተቃራኒ የሆኑ ቃላትን በውክልና እንዲጠቀሙ በተዘዋዋሪ የሚገልፅበት ወይም የሚያዝበት መንገድ ሊሆን ይችላል፡፡ ከላይ እንደተገለፀው የዚህ ውክልና መነሻው ስልጣንን እና ተፅዕኖ አድራጊነትን ለማስቀጠል ከማሰብ የመነጨ ነው፡፡

Edward Said የተባለ ፀሐፊ Oriantalism በሚለው መፅሐፉ ላይ ስለ በቃላት መወከል ወይም “representation” ሲፅፍ እንዲህ ይላል፡- በቃላት አንድን ማህበረሰብ፣ የፖለቲካ ቡድን፣ የሃይማኖት ቡድን ወይም ሌላ ከፍ አድርጎ ወይም ዝቅ አድርጎ መወከል ወይም መሳል ዝም ብሎ የሚመጣ ሳይሆን ታስቦበት እና ታቅዶ ሥልጣንን እና የበላይነትን ለማስቀጠል ከማሰብ የሚመነጭ ነው ይላል (E. Said 1978)::

በአባሪ ቁጥር ሁለት ላይ በቀረበው ደብዳቤ ላይ ፍትህ ፈላጊ የማህበረሰብ ክፍሎች ላጋጠማቸው ችግር ቅሬታቸውን ያቀረቡት በወቅቱ የከፋ ጠቅላይ ግዛት በሚል ስያሜ በሚጠራው እና ለጠቅላይ ግዛት አስተዳደር ነው፡፡ እዚህ ላይ አንድ ነገር ልብ ልንል ይገባል፡፡ ቅሬታ አቅራቢዎቹ ሰው ከተገደለባቸው ፍርድ ቤት ነበር ማመልከቻቸውን ማስገባት የነበረባቸው፡፡ ከዚህ ባለፈ ፍርድ ቤት እንኳን ፍርድ አጓድሎባቸው ነው ወይም ፍርድ አዘግይቶባቸው ነው ብለን እንዳናስብ በማመልከቻው ላይ እንደዚህ አይነት ጭብጥ የያዘ አረፍተ ነገር ወይም ገለፃ በማመልከቻው ውስጥ አልሰፈረም፡፡ ከዚህ የምንረዳው ይህ ማመልከቻ በተፃፈበት ዘመን በነበረው የፖለቲካ የአስተዳደር ሥርአት ህግ አውጪ፣ ህግ አስፈፃሚ እና ህግ ተርጓሚ የምንላቸው የአስተዳደር አካላት እና የስልጣን ክፍፍሎች በተግባር አለመኖራቸውን ያመለክተናል፡፡ ወይም ደግሞ እነዚህ ሦስት የመንግስት አስተዳደር አካላት በህግ አስፈፃሚው የበረታ ጫና ሥር በመውደቃቸው የታችኛው የህብረተሰብ ክፍል ለከፋ የፍትህ እጦት መጋለጡን ሊያሳየን ይችላል፡፡ ከዚህ ባለፈ ገዥው መበደብ በወቅቱ የነበረውን ህገ መንግስት ለይስሙላ ካልሆነ በስተቀር በተግባር እንደማይጠቀምበትም ሊያመላክተን ይችላል፡፡ ለምሳሌ እ.አ.አ በ1931 በኃይለሥላሴ ዘመን የተፃፈው የመጀመሪያው የተፃፈ ህገ መንግስት ምዕራፍ ስድስት ከአንቀፅ 50 እስከ አንቀፅ 54 ድረስ የዳኞችን እና የህግ ተርጓሚውን ሥልጣን እና ተግባር ይዘረዝራል፡፡ በሌላ በኩል በዚሁ በ1931 ህገ መንግስት ምዕራፍ አምስት ላይ ከአንቀፅ 48

እስከ 49 ድረስ የአስፈፃሚውን ሥልጣን እና ተገባር ይዘረዝራል (Ethiopian constitution of 1931, 1969):: እንግዲህ በ1947 ዓ.ም በተፃፈው እና በአባሪ ቁጥር ሁለት ላይ ያለው ተግባር እና በወቅቱ የነበረው ህግ ከህግ አንፃር የሚጋጭ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ይህ ደግሞ በወቅቱ የነበረው ማህበረሰብ ፈጣን ፍትህ እንዳያገኝ ያደረገው ይመስላል፡፡ ከዚህ ባለፉ ይህ የሚያሳየን በወቅቱ በነበረው ስርዓት የሥልጣን መደራረብ የኃላፊነት ግልፅ ያለመሆን ወይም የሀላፊነት መዘበራረቅ መኖሩን እና ይህ ደግሞ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በማህበረሰቡ ላይ የፍትህ ችግር እንደፈጠረ መረዳት ይቻላል፡፡ በተመሳሳይ በአባሪ ቁጥር ሁለት አንቀፅ አንድ ላይ "...... የሰሩትን የግፍ ድርብ ወንጀል......" የሚል አገላለፅ ይገኛል፡፡ ይህም የሚያሳየው አመልካቾች ምን ያክል በደል ይደርስባቸው እንደነበር ነው፡፡ እንዲሁም ከበላይ ሹማምንት ምን ያክል የበላይነት እና የዘገየ ፍትህ እንደነበር "...... ሁለተኛ ማመልከት ግዴታ ስለሆነብን ......." የሚል ሃሳብ መኖሩን በማጣቀሻነት ማንሳት ይቻላል፡፡ የደብዳቤው ፀሐፊዎች ለፍትህ ያላቸውን ጉጉት ለማሳየት ደግሞ "...... ለፍፃሜ ባለ ሙሉ ተስፋ እየሆንን እንጠባበቃለን፡፡" ከሚለው ገለፃ መረዳት እንችላለን፡፡ ከዚህ ባለፈ አባሪ ቁጥር ሁለት ላይ በቀረበው ደብዳቤ ላይ "...... ከአሁን በፊት በጠላት ወረራ ጊዜ በ1927ዓ.ም ...... ደሀ ጠባቂ ዳኛ የለም ነበር ......." በማለት የተገለፀው ሀሳብ በጣሊያን ወረራ ጊዜ የህግ የበላይነት ምን ያክል ደካማ እንደነበር እና የታችኛው መደብ ወይም ደብዳቤውን የፃፉት ማህበረሰቦች በሚኖሩበት አካባቢ የኢ-ፍትሀዊ የማህበራዊ፣ የፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖ ይደርስባቸው እንደነበር ማሳያ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ ይህ ደግሞ ህዝቡ ለውጭ ሀይል ለመንበርከክ ዝግጁ ካለመሆኑ የተነሳ የወራሪው አካል ልዕልናውን ለማሳየት እና ለማስጠበቅ ያደረገው ሊሆን ይችላል፡፡ በሌላ በኩል አመልካቾቹ በዚህ ገለፃ ውስጥ ወይም 1947 ዓ.ም በፃፉት ደብዳቤ ላይ አሁን ዘመኑ ተቀይሯል ሌላ ድሃ ጠባቂ ዳኛ መጥቷል፤ እሱም እናንተ ማመልከቻውን የፃፍንላችሁ አካላት ናችሁ የሚል መልክት ለማስተላለፍ የፈለጉ ይመስላል፡፡ በሌላ በኩል በማመልከቻቸው አንቀፅ ሁለት ላይ "...... እንደ ድንጋይ ተጭኖ ከህግ ውጭ ያስተደደሩን ነበር፡፡" የሚል አገላለፅ ሰፍሮ ይገኛል፡፡ ይህ ሀሳብ አሁንም ይህ ማመልከቻ ከተፃፈበት ዘመን በፊት የነበረው የአስተዳደር ስርዓቱ በማህበረሰቡ ላይ ያደርስ የነበረውን የአስተዳደር በደል እና የፍትህ እጦት ሊያመላክት ይችላል፡፡ በአንፃሩ በአገላለፁ ወስጥ የደብዳቤዎቹ ፀሐፊዎች በወቅቱ የነበረውን ሥርዓት እና ደብዳቤውን የፃፉለትን አካል ለማባበል በሚመስል አኳኋን "...... እንደ ድንጋይ ተጭኖ ከህግ ውጭ ያስተደደሩን ነበር፡፡" የሚለው ገለፃ ሰፍሮ ይገኛል፡፡ በዚህ ገለፃ ውስጥ "ነበር" የሚለውን ቃል በመጠቀም አሁን ያለው ሥርዓት ከበፊቱ ይሻላል በሚል አይነት አባባይነት መፃፉን ሊያሳየን ይችላል፡፡ እናም አመልካቾች በጠላት ወረራ ጊዜ "ዳኛ ጠፍቶ" በማለት የገለፁት አገላለፅ የሚያሳየው ጣሊያን ለአምስት አመት ኢትዮጵያን በያዘችበት ወቅት የፍትህ እጦት እና ሥርዓት አልበኝነቱ የት ድረስ እንደነበር እንድንረዳ አመልካች ከመሆኑ ባለፈ ወራሪው ሀይል ለበላይነት (hegpmony) ምን ያክል ጭቆና ያደርስ እንደነበር ያሳየናል፡፡

በጃንሆይ ዘመን የተፃፉ ደብዳቤዎችን የቋንቋ አጠቃቀም እና ገለፃን መሰረት በማድረግ በደብዳቤዎች ውስጥ ለሀሳቦች ባለቤት ውክልና እና ምስጠራን በምናይበት ጊዜ በአብዛኞዎቹ ደብዳቤዎች ላይ ከ"እኔ" የባለቤትነት ውክልና ይልቅ የ"እኛ" የባለቤትነት ውክልና ተንፀባርቆ ተገኝቷል፡፡ ነገር ግን አልፎ አልፎ የ"እኔ" የባለቤትነት ውክልና ያዘሉ ሀሳቦችም እንዲሁ በደብዳቤዎቹ ላይ ይታያሉ፡፡ በአባሪ ቁጥር አራት ላይ ያለውን ደብዳቤ ብንመለከት በደብዳቤው ውስጥ የ"እኔ" ባለቤትነት የበዛባቸው ሀሳቦች መኖራቸውን እንመለከታለን፡፡ ለምሳሌ "......የመሬት ቅየሳ እና አገማመት በቅርብ ተመልካች ሆኜ እንደገመትኩት ጥናቱ በህግ አግባብ ተሰርቷል ለማለት አልደፍርም......."፡፡ በዚህ ገለፃ ውስጥ ከሰራቸው የተሰመረባቸው

ቃላት በምናይበት ጊዜ ከ"እኛ" ይልቅ የ"እኔ" ውክልናን ያዘሉ መሆናቸውን እንረዳለን፡፡ ይህ ደግሞ በወቅቱ በነበረው የፖለቲካ ሥርዓት ደብዳቤውን የፃፈው የአስተዳደር ክፍል በጉዳዩ ዙሪያ ከተቋም ወይም ከቡድን ሀላፊነት ይልቅ በግለሰብ ደረጃ ሃላፊነት ለመውሰድ ዝግጁ መሆኑን እና ለ normalization ያልተጨነቁ መሆኑን እንረዳለን፡፡ ከዚህ ባለፈ ፀሀፊው እራሱ የፃፈለት የጉዳዩ አካል ወይም የችግሩ ተጎጂ እንዲሁም በሚፃፍበት ጉዳይ ላይ የያዘውን አቋም እና እምነት መሆኑን እንረዳለን፡፡ አሁንም በዚህ ደብዳቤ ውስጥ "…….ባለስልጣኑ በጉዳዩ ላይ አንድ እርምጃ እንደሚወስድበት እርግጠኛ ነኝ" የሚል ሀሳብ ሰፍሮ እናያለን፡፡ በዚህ ገለፃ መቋጫ ላይ "እርግጠኛ ነኝ" የሚለው ቃል የ"እኔ" ባለቤትነት የተሰጠ መሆኑን እና በጉዳዩ ዙሪያ ሀላፊነት ለመውሰድ ያለን ዝግጁነት ሊያሳይ ይችላል፡፡

ሌላው በአባሪ ቁጥር አራት ላይ በሰፈረው ደብዳቤ ላይ "በስራ ላይ የዋሉት ባለስልጣኖች ለበላይ በስሪያ ቤት ማሳሰብ እና ማስፈፀም ድርሻቸው ሲሆን እነሆ አንድም ሰው ያላሰበበት በመሆኑ መንግስትም ሆነ ህዝብ በዚህ መሬት ሊጠቀምበት አልቻለም፡፡" የሚል ገለፃ ሰፍሮ እናገኛለን፡፡ ከዚህ ሀሳብ የምንረዳው ደብዳቤው በተፃፈበት ዘመን በነበረው የአስተዳደር ክፍል በአካባቢው ያለውን የመሬት ሀብት በአግባቡ ይጠቀምበት እንዳልነበረ እና ከማህበረሰቡም ለጠፍ መሬት የለም መሬት ግብር ይሰበስብ ስለነበር ህዝቡ በግብር ሰበብ ይበዘበዝ እና ከመሬቱ ይፈናቀል እንደነበር ያሳያል፡፡ለዚህ ሀሳብ ማጠናከሪያ ከደብዳቤው ውስጥ "…..የመንግስት መሬት የሆነው ሁሉ በቆላና በደጋው የሚገኘው በሙሉ ለም ተብሎ የተገመተ በመሆኑ …….'' የሚለውን ሀሳብ ማየት በቂ ነው፡፡

በአባሪ ቁጥር አምስት ላይ በሰፈረው ደብዳቤ ላይ የቃላት አጠቃቀም ይዘት ከፖለቲካዊ አንድምታቻው አኳያ በምንተነትንበት ጊዜ በወቅቱ ማህበረሰቡ ፍትህን ከማግኘት አኳያ በህገመንግስቱ ላይ ከመተማመን ይልቅ በበላይ ሹማምንት በጎ ፍቃድ ላይ ይንጠለጠል እንደነበር ነው፡፡ለዚህ ማሳያ "…..ለክብርነትዎ የምናመለክተውን በብርሃናዊ ልቦናዎ ተመልክተውልን ….ድምጥማጡን እንዲያጠፉልን በተስፋ እናምናለን፡፡" የሚለውን ገለፃ ማየት ተገቢ ነው፡፡ በተጨማሪ "ቀኝ አዝማች ስዩም አሮሬ የዶንጋና ጥንባሮ ወረዳ ገዥ ስልጣናቸውን በመተማመን ባልታወቀ መንገድ መንደር ለመንደር እየሄዱ በሀዲይኛ እየተናገሩ በአውራጃው ውስጥ ያሉትን በአምስቱ ወረዳ የሚገኙትን ሀድዮች እየሰበሰቡ በአውራጃው ውስጥ በሚገኙት ጎሳዎች ላይ እንዲነሳሱና…..፡፡" በሚለው ገለፃ ውስጥ "ባልታወቀ መንገድ" ከሚለው አገላለፅ የምንረዳው በወቅቱ በነበረው የፖለቲካ ስርዓት ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ ችግር እንደነበረ ሊያመለክተን ይችላል፡፡ ምክንያቱም በስውር የሚንቀሳቀሱትን ሀሳብን በነፃነት መግለፅ ስለማይፈቀድ ሊሆን ስለሚችል ይሆናል፡፡ በደብዳቤው ውስጥ "…..አስተዋዩ እና አርቆ ተመልካች ንጉሰ ነገስታችን ዳግማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ አህጉራችንን አፍሪካን አልፎ ተርፎም በኢኮኖሚና በማህበራዊ ኑሮ አለምን አንድ ለማድረግ በሚጥሩበት……"፡፡ በሚለው የገለፃ ድምፀት ውስጥ "…..በኢኮኖሚአፍሪካን አልፎ ተርፎም አለምን አንድ ለማድረግ….." ከሚለው የተጋነነ ድምፀት (Tone) የምንረዳው በወቅቱ ስለ ጃንሆይ ለህብረተሰቡ የተጋነነ እና የተዛባ የፕሮፓጋንዳ ገለፃ ይሰጥ እንደነበር ነው፡፡ ይህም የሚደረገው በህብረተሰቡ ዘንድ የንጉሱን ስልጣን አይነኬነት እና ፍፁማዊነት በማስረፅ ማህበረሰቡ ጥያቄ እንዳያነሳ እና በተስፋ መቁረጥ አርፎ እንዲገዛ ለማድረግ በማሰብ ይመስላል፡፡

በአባሪ ቁጥር አምስት እና ስድስት ላይ የቀረበውን ሃሳብ በምንመረምርበት ጊዜ ደብዳቤው በተፃፈበት ዘመን የህዝቡ የቅርብ ተጠሪ የሆኑት ሹማምንት ህዝቡን በአገልግሎት አሰጣጥ ረገድ ያጉላሉት እንደነበር እና ህዝቡም መብቱን ለመጠየቅ በሚሞክርበት ጊዜ እንደ አመፅኛ ይቆጠር እንደነበር እና ሹማምንቱ ግን የተሳሳተ መስመር ቢከተሉ እንኳን እንደ ትክክለኛ ይታዩ እንደነበር እንረዳለን፡፡ ይህም የነበረው ስርዓት ለእኩልነት፣ ሀሳብን በነፃነት ለመግለፅ ወዘተ መብቶች በፈረንጅ

አቆጣጠር በ1931 እና በ1955 ያወጣቸው ህጎች ከወረቀት ያላለፉ መሆናቸውን ያሳየናል፡፡ ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው ለዚህ ዋነኛው ምክንያት የበላይነትን እና ስልጣንን ለማስቀጠል ከማሰብ የመነጨ ሊሆን ይችላል፡፡ በሌላ በኩል በአባሪ ቁጥር ስድስት ላይ “ተመልክተነዋል”“ተረድተነዋል” እና “እናስታውቃለን” የሚሉ ቃላትን በምናይበት ጊዜ ደብዳቤው ለጉዳዩ ኃላፊነት የሚወስደው አካል በ“እኛ” ባለቤትነት ለመመስጠር ጥረት ማድረጉን መረዳት ይቻላል፡፡ የዚህ ምስጠራ ዋና ምክንያት ኃላፊነትን ለመውሰድ ከመፍራት ወይም ደግሞ በጉዳዩ ላይ መተማመን ከማጣት ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ ካልሆነ ደግሞ ጉዳዩን ዲፕሎማሲያዊ በሆነ መንገድ ለመግለፅ ከማሰብ የመነጨም ሊሆን ይችላል፡፡

በሌላ በኩል ነገሮችን ለመመስጠር ከማሰብ እና ከተፈለገው አካል ውጭ ለሌላው ግልፅ እንዳይሆኑ በማሰብ በጃንሆይ ዘመን በተፃፉ ደብዳቤዎች ላይ ሞያዊ ቃላት (Terms of Jargns) ይስተዋላሉ፡፡ ለምሳሌ በአባሪ ቁጥር አንድ እና ስድስት ላይ በወቅቱ በነበረው ስርዓት የሚከተሉት ፖለቲካዊ የሞያ ቃላት ሰፍረው ይገኛሉ፡፡ “ከወርቅ አንፋሸዋ”፣ “ከመልከኛው”፣ “በጅሮንድ”፣ “የባላባት መተማመኛ” ወዘተ፡፡ R.A. Hudson የተባለ ፀኃፊ Sociolingustics በተባለ ፅሁፉ ላይ እንደሚያትተው የማመልከቻ ወይም የደብዳቤ ፀኃፊዎች ሞያዊ ቃላት (Terms of Jargons) የሚጠቀሙት በሁለት መሰረታዊ ምክንያቶች ነው፡፡ አንደኛው የአንባቢውን ወይም የተፃፈለትን አካል ቀልብ ለመግዛት ከማሰብ ሊሆን ይችላል፡፡ ሌላኛው ሀሳቡን በመመስጠር ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው አካላት ብቻ እንዲረዱት ለማድረግ በማሰብ ነው ይላል F.A. Hudson (1930) ፡፡ ለምሳሌ ከላይ በምሳሌነት ከቀረቡት ቃላት መካከል “ከመልከኛው” የሚለውን ብናይ መሳሪያ ያነገበ ወይም ነፍጥ የተሸከመ የሚል አቻ ቃል እንዳለው መረዳት እንችላለን፡፡ በዚሁ መሠረት የቃላት ምስጠራው ከላይ ከቀረቡት ምክንያቶች በአንድ ሊሆን ይችላል ማለት ነው፡፡

R. Horweg የተባለ ፀኃፊ እንደሚገልፀው አንድን ደብዳቤ ወይም ፅሁፍ በምንመረምርበት ጊዜ ሌላኛው ልብ ልንለው የሚገባን ነገር የፅሑፉን ድምፀት (Tone) ነው R. Horweg (1978)፡፡ በዚሁ መሰረት በአባሪ ቁጥር ሰባት እና ስምንት ላይ የቀረቡትን ደብዳቤዎች ስናይ የአባባይነት ድምፀት፣ የመሰወር (Aabstraction) ድምፀት እና የፖለቲካ ዲፕሎማሲያን ድምፀት የሚስተዋልባቸው አገላለፆች ይገኛሉ፡፡ ለምሳሌ በአባሪ ቁጥር ስምንት ከሚኒስተር መስሪያ ቤት ለአውራጃ የተላለፈውን የግብር ምህረት በአውራጃው ተቀባይነት ባለማግኘቱ የአውራጃው እንቢ ማለት የአገር ግዛት ሚኒስትሩን ኃላፊ ሚኒስተር እንደ ግለሰብ ሳይሆን እንደ ተቋም መሆኑን ለማሳየት የመልሱን ደብዳቤ ድምፀት ከግለሰባዊ መልስ ለማራቅ እና ተቋማዊ ቁመና እንዲኖረው ለማድረግ እንደተሞከረ አባሪውን በማየት ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

በአባሪ ቁጥር ሰባት ላይ “...... ግብራቸውን መክፈል የሚችሉት በጠቅላይ ግዛት መስሪያ ቤትና በበጅሮንድ አማካኝነት እንዲከፍሉ፡፡” የሚል አገላለፅ ይገኛል፡፡ እንግዲህ በዚህ አገላለፅ ውስጥ “እንዲከፍሉ” የሚለው ቃል የትዕዛዝ ድምፀት (Tone) ያለው ሲሆን አልከፍልም የሚሉ ከሆነ ደግሞ እርምጃ ይወሰድባቸዋል አይነት ትዕዛዝ ያዘለ የሚመስል ጠንከር ያለ ድምፀት ያለው አገላለፅ ይመስላል፡፡ ይህ እንግዲህ በወቅቱ ግብር መክፈል የማይችሉ ወይም አቅሙ የሌላቸው ግለሰቦች እንኳን ምንም አይነት ምርጫ ሣይኖራቸው ትዕዛዙን እንዲፈፅሙ የሚያደርጉ የፖለቲካ ሹማምንት መኖራቸውን፣ የገዥው መደብ በተገዥ መደብ ላይ ከውይይት እና ከማሳመን ይልቅ ትዕዛዝን ይከተል እንደነበር ሊያመለክተን ይችላል፡፡

በአባሪ ቁጥር ዘጠኝ ላይ በቀረበው ደብዳቤ ላይ ስለ ፖለቲካዊ አስተዳደር ዘዴ “የአገሩ ባህል ምንም ልዩ ልዩ ቢሆን......የአስተዳደር ዘዴ ህግ አንድ ሰለሆነ......” የሚል ገለፃ ተቀምጧል፡፡ በገለፃው እንደምንረዳው ደብዳቤው በተፃፈበት

ዘመን ለብዝሀነት ዝቅተኛ ትኩረት ይሰጥ እንደነበረ እና ሁሉንም በተመሳሳይ መንገድ የእድገት፣ የጂኦግራፊ፣ የአኗኗር ዘይቤ፣ የብሄር፣ የሃይማኖት ወዘተ ጉዳዮችን ከግምት ባለማስገባት ይሰራ እንደነበረ መረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአባሪ ቁጥር ዘጠኝ ላይ ከቀረበው እና ከላይ ከተገለፀው ነጥብ የምንረዳው ደብዳቤው በተፃፈበት ዘመን ከብዝሀዊነት የፖለቲካ ርዕዮት አለም ይልቅ የአሀዳዊነት የፖለቲካ ርዕዮት አለም በሠፊው ይቀነቀን እንደነበረው ነው፡፡

**4.1.2. ማህበራዊ ጉዳዮች ትንተና**

በጃንሆይ ዘመን በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የተፃፉ ደብዳቤዎችን ከማህበራዊ አንድምታዎች አኳያ በምናይበት ጊዜ በአባሪ ቁጥር አንድ በሰፈረው ደብዳቤ ላይ "...... በካርኒ በደረሰኝ የገበርንበትን ቅድመ ርስታችንን የስሞን መሬት መምሬ ወሰኔ ገዝሙ የተባሉ ቢነቅሉን...... አርሰን ነግደን የምንተዳደረውን ህዝቦች ወዲህ ገዥ ወዲህም የመንግስት መሬት ነው እያሉ በራሳቸው ፊርማ እየመሰከሩ......." የሚል ሀሳብ ሰፍሮ እናገኛለን፡፡ ከዚህ የምንረዳው ሀይማኖት በህብረተሰቡ እና በአስተዳደር ክፍሉ ውስጥ ያለውን ተቀባይነት ተገን በማድረግ የሀይማኖትን መጠሪያ ሽፋን ያደረጉ ግለሰቦች ከማህበረሰቡ ጋር ያላቸውን የኑሮ መስተጋብር እና ያደርሱ የነበረውን ጫና ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የተባሉት ሠው "መምሬ" በመሆናቸው ብቻ የሃይማኖት ከለላ በማድረግና በማን አለብኝነት በግለሠቦች ላይ የሚፈጥሩት ጫና ከሃይማኖቱ የበላይነት ጋር ተያይዞ የሚታይ ጉዳይ ሊሆንም ይችላል፡፡ ከዚህ ባለፈ በገለፃው ውስጥ "በራሳቸው ፊርማ እየመሰከሩ" የሚለው አገላለፅ አሁንም የሀይማኖት አባትነት በማህበረሰቡ እና በፖለቲካ ሰርዓቱ ውስጥ ያላቸውን ተቀባይነት ምርኩዝ በማድረግ በህብረተሰቡ ላይ ያደረሱ የነበረውን ጭቆና አመላካች ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ ከዚህ ባለፈ "በራሳቸው ፊርማ እየመሰከሩ" የሚለው አገላለፅ በወቅቱ በማህበረሰቡ ውስጥ የሃይማኖት አባቶች የተሻለ የተማሩ እንደነበሩ አመላካች ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ በመሆኑም ከቀለም ትምህርት ይልቅ የቤተክህነት ትምህርት ጉልህ ድርሻ እንደነበረው ማሳያ ተደርጎ ሊቀርብ የሚችል ነው፡፡ በሌላ በኩል አባሪ ቁጥር አምስት ላይ የቀረበው ደብዳቤ ላይ "...... በአንዳንዶች ባልተማሩና ባልተመራመሩ ሰዎች አእምሮ ውስጥ ተቀርፆ ያለውን ለኢትዮጵያዊነታችን ጠንቅ የሆነውን አነጋገር እና የጎሳ ድምጥማጡን እንዲያጠፉልን በተስፋ እናምናለን፡፡" የሚል ሃሳብ ሰፍሮ እናገኛለን፡፡ ከዚህ አገላለፅ የምንረዳው በወቅቱ በነበረው ማህበረሰብ ውስጥ ጎጠኝነት እና ጎሰኝነት ያላዋቂ ያስብል እንደነበረ እና ከጎሳ ብሄረተኝነት ይልቅ የሀገር ብሄረተኝነት በአዋቂነት፣ በአስተዋይነት እና በተመራማሪነት ያስመድብ እንደነበር እንረዳለን፡፡ ከዚህ ባለፈ እንደሚታወቀው በአንድ ግለሰብ አመለካከት እና አስተሳሰብ ላይ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተፅዕኖ ከሚያሳድሩ ነገሮች አንዱ የማህበረሰብ አመለካከት እና አስተሳሰብ ነው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ ከላይ በቀረበው አገላለፅ ውስጥ በተለይ "በአንድ አንድ ባልተማሩ እና ባልተመራመሩ ሰዎች" የሚለው አገላለፅ ከደብዳቤው አጠቃላይ ገለፃ አንፃር ስናየው መግለፅ ወይም ማስተላለፍ የፈለገው ነጥብ ፊደል ከመቁጠር እና ከመማር አንፃር ሳይሆን በወቅቱ በማህበረሰቡ ቅቡል ተደርጎ ከሚወሰደው አስተሳሰብ፣ አስተምሮ እና አመለካከት የወጣ እና ተቀባይነት ያፈነገጠ አስተሳሰብ ያላቸውን ቡድኖች ለማመልከት ይመስላል፡፡ ከዚህ ባለፈ ከላይ በቀረበው አገላለፅ የምንረዳው በወቅቱ በነበረው ማህበረሰባዊ ስርአት ውስጥ ከብዙሀኑ ያፈነገጠ አስተሳሰብ እና አመለካከት ያላቸውን ግለሰቦች ወይም ቡድኖች ሀሳባቸውን ከማክበር ይልቅ ውግዘቱ ይበረታባቸው እንደነበር እና ባለ አዋቂነት ያስፈረጃቸው እንደነበር መረዳት ያስችለናል፡፡ በተመሳሳይ በአባሪ ቁጥር አምስት በተፃፈው ደብዳቤ በአንቀፅ አንድ ላይ "...... የከምባታ አውራጃ ህዝብ በኢትዮጵያዊነት የምንኮራ በቤተሰብ ሳይሆን በህብረተሰብ የምናምን በጎሳ ሳይሆን በዜግነታቸው ደስ የምንሰኝ......" የሚል አገላለፅ ሰፍሮ እናገኛለን፡፡ ከዚህ አገላለፅ ውስጥ "በጎሳ ሳይሆን በዜግነታችን ደስ የምንሰኝ" የሚለውን ገለፃ በምናይበት ጊዜ በወቅቱ በማህበረሰቡ ውስጥ ከቡድን

ብሄረተኝነት ይልቅ ግለሰባዊነት በሰፊው ይቀነቀን እንደነበር እና የማህበረሰቡ ማንነት ከጎሳ ብሄረተኝነት ይልቅ ዜግነት ላይ መሰረት ባደረገ ግለሰባዊነት እና ብሄረተኝነት ላይ መሰረት ያደርግ እንደነበር አመላካች ሀሳብ ተደርጎ መወሰድ ይችላል፡፡ ከዚህ ባለፈ ከላይ በሰፈረው ገለፃ "በቤተሰብ ሳይሆን በህብረተሰብ የምናምን በጎሳ ሳይሆን በዜግነት" የሚለውን ገለፃ በምናይበት ጊዜ አሁንም በወቅቱ በነበረው ማህበረሰብ ውስጥ የmoral እሴቶች ወይም የግብረገብ እሴቶች ከዘር፣ ከጎሳ እና መሰል ጉዳዮች ይልቅ ሰው በሚለው ፅንሰ ሀሳብ ላይ መሰረት ያደረጉ እንደነበር እና ከዘር፣ ከጎሳ እና መሰል ብሄረተኝነት በበለጠ ሀገራዊ ብሄረተኝነቱ ግዙፍ እንደነበር ማሳያ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ በሌላ በኩል በደብዳቤው የመጨረሻ አንቀፅ ላይ "..... ከቡርነትዎን የምንለምነው የአወራጃውን ህዝብ ፀጥታ ለመጠበቅ ከእግዚአብሄርና ከንጉሰ ነገስቱ አደራ የተቀበሉ ስለሆነ......" የሚለው ገለፃ ይገኛል፡፡ ከዚህ ገለፃ እንደምንረዳው ደብዳቤው በተፃፈበት ዘመን በማህበረሰቡ ውስጥ ያለው አመለካከት እና እምነት ለመንግስት ሹማምንት ስልጣናቸው ከህገ መንግስት እና ህዝብ ሳይሆን ከእግዚአብሄር ይላክላቸው እንደነበር እንረዳለን፡፡ ለዚህም መነሻ የሚሆነን በገለፃው ውስጥ የአውራጃው ገዥ ፀጥታን ለመጠበቅ እና የህዝቡን ደህንነት ለመጠበቅ ከእግዚአብሄር አደራ የተቀበሉ ተደርጎ መሳሉ ነው፡፡ በተለይ "አደራ የተቀበሉ" የሚለው አገላለፅ በወቅቱ ማህበረሰቡ እራሱን ከእግዚአብሄር እና ከንጉሰ ነገስቱ ለአከባቢው ሹማምንት የአደራ ሥጦታ አድርጎ ይመለከት እንደነበር እንረዳለን፡፡ ይህ አይነት ማህበራዊ እምነት በህብረተሰቡ ውስጥ እንዲያድግ እና እንዲሰርፅ መደረግ ህብረተሰቡ ሀይማኖተኛ መሆኑን ከማመልከቱ ባለፈ የፖለቲካ ቡድኖች ህብረተሰቡ የሚፈራውን፣ የሚያምነውን፣ እና ያለ ጥያቄ የሚገዛለትን እምነቱን ተገን በማድረግ ያለ ተቃውሞ ለመግዛት ወይም ለመሪዎች የቅድስና ካባ በማልበስ ተቃውሞን ለመቀነስ ታስቦ ማህበረሰባዊ አስተሳሰብ እንዲሆን የተደረገ ይመስላል፡፡

**4.1.3. ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ትንተና**

በጃንሆይ ዘመን በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የተፃፉ ደብዳቤዎች ከኢኮኖሚያዊ አንድምታቸው አኳያ በምንመረምርበት ጊዜ ደብዳቤዎቹ በተፃፉበት የዘመን መንፈስ በላይኛውና በታችኛው መደብ መካከል የነበረውን የኑሮ ልዩነት እና ትግል አመላካች ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በደብዳቤዎቹ ውስጥ በግብር ከፋዩ እና በግብር አስከፋዩ መካከል ያለውን ግንኙነት የሚያሳዩ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ በተጨማሪም በደብዳቤዎቹ ውስጥ መሬትን መሰረት አድርገው ይደረጉ የነበሩ ትግሎችን እና መሰል ሀሳቦችን ደብዳቤዎቹ ከተፃፉበት የዘመን እና የፖለቲካ ስርዓት አንፃር እንደሚከተለው ለመተንተን ተሞክሯል፡፡ በዚሁ መሠረት በአባሪ ቁጥር አንድ ላይ ያሰፈረውን ደብዳቤ በምናይበት ጊዜ በደብዳቤው ውስጥ መሬት ዋነኛው የኢኮኖሚ እና የኑሮ መሠረት መሆኑን የሚያሳዩ አገላለፆች ሰፍረው እናገኛለን፡፡ ለምሳሌ በደብዳቤው ላይ ".....ርስታችን ተወስዶብን እኛ ድሆችዎ መግቢያ አጣን......" የሚለው አገላለፅ ከላይ እንደተመለከትነው መሬት በህብረተሰቡ ዘንድ የመኖርና ያለመኖር ጉዳይ መሆኑን ከማሳየቱም ባለፈ የህብረተሰቡ ከዛም አለፍ ሲል የሀገሪቱ ኢኮኖሚ በግብርና ላይ የተንጠለጠለ መሆኑን በግልፅ ያሳያል፡፡

በተጨማሪ ".....አርሰን ነግደን የምንተዳደረውን ሕዝቦች......" ከሚለው አገላለፅ መሬት በማህበረሰቡ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ ለንግድ እንቅስቃሴም የነበረውን ሚና በማሳያነት ልንጠቀምበት እንችላለን፡፡ ምክንያቱም የደብዳቤው ፀሐፊዎች መሬታቸውን በመነጠቃቸው የኢኮኖሚ ሁኔታቸው መጎዳቱን ለማሳየት ".....አርሰን ነግደን የምንተዳደረውን ሕዝቦች......ደሆችዎ መግቢያ አጣን በነፃነታችን ተበደልንብዎ፡፡" የሚለውን ገለፃ ማየት ጥቅም አለው፡፡ በተመሳሳይ "ከአሁን ቀደም በርስትነት በካርኒ በደረሰኝ የገበርንበትን ቅድመ ርስታችንን የስሞን መሬት መምሬ ወሰኔ ገዝሙ የተባሉ ቢነቅሉን......"

የሚለው አገላለፅ በወቅቱ በመሬት ዙሪያ በቤተ እምነቶች እና በማህበረሰብ መካከል የነበረውን ችግር በማሳያነት ሊወሰድ ይችላል፡፡ በመሬት ይገባኛል ትግሉ ወቅት በደብደቤው ላይ እንደተመለከትነው "የስሞን መሬት" (የቤተክርስቲያን መሬት) መምሬ ወሰኔ በደብዳቤው ፀሐፊዎች የገቢ ምንጭ የሆነውን መሬት ከፖለቲካ አስተዳደር ጋር በመቀናጀት በመንጠቃቸው የተነሳ ችግር ላይ መውደቃቸውን ገልፀዋል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ በደብዳቤው ላይ "ወዲህ ገዥ ወዲህም የመንግስት መሬት ነው እያሉ በራሳቸው ፊርማ እየመሰከሩ......ውስጡን በማያውቀው መስሪያ ቤት እያመለከቱ ገዝቸዋለሁ በማለት....." የሚለው አገላለፅ በጃንሆይ ዘመን የመሬት ግዥ እና ሽያጭ መኖሩን ከማሳየቱ ባለፈ በኢኮኖሚ እና ገቢ ምንጭነት ያገለግል እንደነበረ ከማሳየቱ ባለፈ ለታችኛው መደብ የጭቆና እና የብዝበዛ መሳሪያ መሆኑን ያመለክታል፡፡ በሌላ በኩል ቤተ እምነቶች እና የሃይማኖት አባቶች በማህበረሰቡ እና በፖለቲካ ስርዓቱ ያላቸውን ተቀባይነት እና ተሰሚነት ተገን በማድረግ የግል ሀብታቸውን ለማካበት ህብረተሰቡ ላያ ጫና ያደርጉበት እንደነበር በማሳያነት ልንወስደው እንችላለን፡፡

በጃንሆይ ዘመን ከተፃፉ ደብዳቤዎች ውስጥ በገዥው እና በተገዥው መካከል የነበረውን የኢኮኖሚ ግንኙነት ከሚያሳዩ ደብዳቤዎች መካከል በአባሪ ቁጥር አራት ላይ የሚገኘው ደብዳቤ አንድ ነው፡፡ በዚህ ደብዳቤ ላይ ".....የመንግስት መሬት የሆነው ሁሉ በቆላና በደጋ የሚገኘው በሙሉ ለም ተብሎ የተገመተ ለመሆኑ መዝገቡ ያስረዳል፡፡......በዚህ አገማመት ስራ ላይ የዋሉት ሰራተኞች ያለ ጥንቃቄ እና ያለማስተዋል የፈፀሙት አመዳደብ በመንግስት ገቢ ላይ የቱን ያህል ጉዳት እንዳደረሰበት......" የሚል ሃሳብ ሰፍሮ ይገኛል፡፡ ከዚህ ሃሳብ የምንረዳው በወቅቱ የመሬት ምደባ ጠፍ የሆነው መሬት ሁሉ በለም መሬት ስም የግብር ብዝበዛ ለማድረግ ይውል እንደነበር ነው፡፡ ከዚህ ባለፈ መክፈል ያልቻለው ደግሞ ከመሬቱ ይፈናቀል እንደነበር ያሳየናል፡፡ ይህ ደግሞ የሚያሳየው በወቅቱ በገዥው እና በተገዥው ማህበረሰብ መካከል የነበረው የኢኮኖሚ ግንኙነት የበዝባዥ እና የተበዝበዥ መሆኑን ነው፡፡ በሌላ በኩል ጠፍ የሆነው መሬት ለም በሚል የተሳሳተ ስያሜ ውስጥ በማረፉ እና መሬቱን በግዥ፣ በኮንትራት በመግዛት እና ግብር በመክፈል የሚገለገልበት በመጥፋቱ የተነሣ የመንግስት ገቢ መጎዳቱ በደብዳቤ ላይ ተመልክቷል፡፡ ይህ የሚያሳየው ደብዳቤው በተፃፈበት ዘመን የማእከላዊ መንግስት ገቢ ከሌሎች ዘርፎች በበለጠ ከመሬት ጋር በተያያዙ ገቢዎች ላይ ጥገኛ መሆኑን ሊያመለክተን ይችላል፡፡ ከዚህ ባለፈ ከአገላለፁ መሬት ለማእከላዊ መንግስቱ ህልውና የነበረውን ስፍራም ልናይበት እንችላለን፡፡

በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ በጃንሆይ ዘመን የነበረውን የኢኮኖሚ ሁኔታ ለመመርመር ከሚረዱን ደብዳቤዎች መካከል በአባሪ ቁጥር ሰባት ላይ የቀረበው ደብዳቤ ይገኝበታል፡፡ በዚህ ደብዳቤ አንቀፅ ሁለት ላይ ".....መክፈል ባለመቻላቸው በችግር ምክንያት የለቀቁት ግን ደህው በጥብቅ እየተመረመረ......" የሚል አገላለፅ ሰፍሮ ይገኛል፡፡ ይህ የሚያሳየው በአካባቢው ወይም ደብዳቤው በተፃፈበት በከፋ ጠቅላይ ግዛት አካባቢ የሚኖሩ አርሶ አደሮች የኢኮኖሚ ሁኔታ ደካማ ከመሆኑ የተነሳ ግብር እንኳን መክፈል ያቅታቸው እንደነበር እንረዳለን፡፡ የግብሩ ሁኔታም ማህበረሰቡን ያማከለ ሳይሆን እንዲሁ ለተፈለገው አካል ገቢ እንዲሆን የማመቻቸት ሂደት መሆኑን እንረዳለን ከዚህ በተጨማሪ " ደህው በጥብቅ እየተመረመረ" የሚለው ገለፃ በደሃ ስም የሚመጣውን እድል ከበርቴው ይገለገልበት እንደነበር ነው፡፡ አርሶ አደሮቹ ግብር ሊከፍሉ ለምን አልቻሉም የሚለውን ጥያቄ በምንጠይቅበት ጊዜ ሁለት ምላሾችን ልናገኝ እንችላለን፡፡ አንዱ በወቅቱ የነበረው ስርዓት በአርሶ አደሮቹ ላይ ከአቅም በላይ ግብር በመጣሉ የተነሳ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ ካልሆነ ደግሞ የአርሶ አደሩ ምርታማነት በተፈጥሮአዊ እና ሰው ሰራሽ ምክንያቶች ከእጅ ወደ አፍ ሆኖ ለገበያ የሚተርፍ ምርት ባለመመረቱ ሊሆን ይችላል፡፡ ለምሳሌ በቁጥር አንድ ላይ

በምክንያትነት የተጠቀሰውን ሀሳብ በከፊል የሚያጠናክርልን ደብዳቤው ውስጥ የሰፈረውን “.....የመሬቱ አገማመት በደንብ ባለመሆኑ እንደገና እንዲገመት......” የሚለውን በጠቋሚነት መውሰድ ይችላል፡፡

በአባሪ ቁጥር ዘጠኝ ላይ ከተፃፈው ደብዳቤ የምንረዳው በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ እንዳጠቃላይ ደብዳቤው በተፃፈበት አካባቢ በተለይ የኢኮኖሚ የገቢ ምንጭ ከአንድ ሰብል ጥገኝነት ይልቅ በርካት ወዳሉ እና በገበያ ተፈላጊነት ወዳላቸው ሰብሎች ትኩረት ያደረገ አዋጅ መታወጅ እንዳለበት የሚያመለክት አይነት አንድምታ ያለው ደብዳቤ መሆኑን ነው፡፡ ከዚህ የምንረዳው ደብዳቤው በተፃፈበት አካባቢ ይኖሩ የነበሩ የማህበረሰብ ክፍሎች ለምሳሌ ኢኮኖሚያቸው በእንሰት ላይ በሰፊው ጥገኛ በመሆኑ በገቢያቸው ላይ ተፅዕኖ እንደነበረው እና የአመራረት ለውጥ አስፈላጊ መሆኑን ያሳያል፡፡ በሌላ በኩል ከደብዳቤው እንሰት ገበያ ወጥቶ በሚሸጥበት ወቅት ከገቢ ምክንያት አኳያብዙ ገንዘብ የማያስገኝ መሆኑን ሊያመለክተን ይችላል፡፡ ምናልባትም እንሰት በወቅቱ ለነበረው አርሶ አደር ዝቅተኛ የገቢ ምንጭ መሆን በህብረተሰቡ ላይ  የገቢ ጫና በማሳደሩ የተነሣ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በሀገር ኢኪኖሚ ላይ ተፅዕኖ ያደርሳል በሚል አንድምታ ይመስላል በደብዳቤው ላይ “.....በያይነቱ የሀገር ጥቅም የሚሰጠውን ሁሉ እንዲሰራ የመንግስት ትዕዛዝ ተላልፎ በአዋጅ......” የሚለል ሃሳብ ሰፍሮ የሚገኘው ፡፡

በአጠቃላይ በጃንሆይ ዘመን በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የተፃፉ ደብዳቤዎችን ከኢኮኖሚያዊ አንድምታ አኳያ በምንመረምርበት ጊዜ መሬት በግለሰብ ደረጃ ይሁን በሀገር ደረጃ ትልቅ የኢኮኖሚ ምሰሶ መሆኑን እና መንግስት ህዝቡን ለማገዝ በመሳሪያነት ይጠቀምበት እንደነበር እንረዳለን፡፡ ከዚህ ባለፈ በወቅቱ የመሬት ሽያጭ ህጋዊ እንደነበር እና ህብረተሰቡ በችግሩ ጊዜ መሬቱን ሽጦ በመጨረስ ለችግር እንደሚጋለጥ እና በአጭበርባሪ ግለሰቦች እንደሚታለል በደብዳቤዎቹ ውስጥ ተመልክቷል፡፡ ይህም ሠፊው ህዝብ በባላባቶች ስር እንዲወድቅ እና የመደብ ልዩነት እና ትግሉ እንዲጨምር አድርጎታል፡፡ በሌላ በኩል ተገቢ ባልሆነ የግብር አሰባሰብ እና የግብር አተማመን ጋር ተያይዞ አርሶ አደሩ የኢኮኖሚው እና የኑሮው ህልውና የሆነውን መሬት ይነጠቅ እንደነበር በደብደቤዎቹ ላይ ከሰፈሩት ሀሳቦች መገንዘብ ይቻላል፡፡ በተመሳሳይ በግብር አሰባሰብ ዙሪያ በገዥው እና በተገዥው መደብ መካከል የበዝባዥነት እና የተበዝባዥነት አመላካች ግንኙነቶች መኖራቸው ለመረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህም ጋር አያይዞ አጠቃላይ በዘመኑ የነበረው የኢኮኖሚ ዋልታ መሬትና ከመሬት ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ማለትም ግብር እና መሬት ሽያጭ እንዲሁም እርሻ መሆናቸውን ከተገለፁት ደብዳቤዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

## 4.2. በደርግ ዘመን በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የተፃፉ ደብዳቤዎች ቋንቋ አጠቃቀም   ይዘት ትንተና

### 4.2.1. ፖለቲካዊ ጉዳዮች ትንተና

Norman Fairclough የተባለ ፀሐፊ Analysing Discourse የሚለው መፅኀፉ ላይ እንደማያትተው አንድ ተንታኝ መዛግብትን ወይም ሰነዶችን በሚተነትንበት ጊዜ በመዛግብቱ ወይም ሰነዶቹ ላይ የሚገኙትን ቃላዊ እና ምልክታዊ መገለጫዎች ላይ በመመርኮዝ ደብዳቤው በተፃፈበት ወቅት ሥለነበረው የፖለቲካ ርዕዮተ አለም፣ ማህበራዊ አመለካከት፣ የፖለቲካ ግንኙነት፣ የጨቋኝ ተጨቋኝ ግንኙነት፣ የገዢ ተገዢ ግንኙነት፣ የማህበራዊ እና ማህበረሰባዊ ለውጥ፣ የኢኮኖሚ ሁኔታ የስልጣን ግንኙነት ወዘተ መግለፅ ይቻላል ይላል፡፡ Norman Fair clough,(2003)::

በዚህ መሰረት ከላይ በአባሪ ቁጥር አሥር እና አስራ አንድ ላይ የቀረቡትን ደብዳቤዎች በጃንሆይ ዘመን ከተፃፉ ደብዳቤዎች አንፃር በምናይበት ጊዜ ልዩነቶችን እናስተውላለን፡፡ ለምሳሌ በደብዳቤዎቹ ላይ በራስጌ አርማነት ከተቀመጠው አንበሳ እና ከተያዘው አርማ ብንነሳ በጃንሆይ ዘመን በተፃፉ ደብዳቤዎች ላይ በአንበሳው አናት ላይ ዘውድ ተጭኖ እንመለከት ነበር፡፡ ነገር

ግን በወታደራዊ የደርግ ስርዓት በተፃፉት ደብዳቤዎች ላይ በአባሪ ቁጥር አሥር እና አሥራ አንድ ላይ እንደሚታየው በአንበሳው አናት ላይ ምንም አይነት የዘውድ ምልክት የለም፡፡ ይሄም የሚያሳየው የዘውዳዊ ሥርአት በኢትዮጵያ ማብቃቱን እና አዲስ አይነት ርዕዮት አለም መምጣቱን ነው፡፡ ይህ አዲስ የፖለቲካ ርዕዮተ አለም ደግሞ ዘውዳዊ አለመሆኑን ለማሳየት ከአንበሳው አናት ላይ ዘውዱን አንስቶታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በጃንሆይ ዘመን በተፃፉ ደብዳቤዎች ላይ ቀደም ባለው "በጃንሆይ/ (በሀይለስላሴ) ዘመን የተፃፉ ደብዳቤዎች ፖለቲካ ትንተና" በሚለው ጭብጥ ሥር እንደተመለከተው በራስጌ አርማው ላይ አንበሳው በቀኝ የፊት እግሩ የያዘው የሰንደቅ አላማ መያዣ ዘንግ አናቱ ላያ የመስቀል ምልክት ነበረው፡፡ ይህም በወቅቱ የነበረው የጃንሆይ የአስተዳደር መንግስት ክርስቲያናዊ መሆኑን እንደሆነ ተጠቁሟል፡፡ ነገር ግን ወታደራዊ መንግስት ወደ ስልጣን ከመጣ በኃላ እና ሕብረተሰባዊነት (Socialism) ከታወጀ በኃላ ይሄንን አናቱ ላይ የመስቀል ምልክት ያለውን የሰንደቅ አላማ መያዣ ዘንግ መስቀሉን በማንሳት ወደ ሹልነት እንደተቀየረ በአባሪ ቁጥር አሥራ እና አንድ አንድ ላይ ያሉትን ደብዳቤዎች በማየት ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ በአንፃሩ በጃንሆይም ይሁን በወታደራዊው የአስተዳደር ሥርዓት በሰንደቅ ዓላማ አንጋቢነት የተመረጠው አንበሳ ጎፈር ያለው ወንድ አንበሳ መሆኑን በሁለቱም የአስደዳደር ዘመን የፆታ እኩልነት ያለውን ቦታ ሊያሳየን ይችላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በደርግ ከሽግግሩ የወታደራዊ ስርዓት በኃላ የተፃፉ ደብዳቤዎች በራስጌ አርማነት በሚጠቀሙት ምልክት ላይ አንበሳውን በማንሳት በሞፈር እንደተኩት አባሪ ቁጥር አስራ አምስትን በማየት ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ ይህም የሚያሳየን የወታደራዊ ደርግ መንግስት "ልማታዊ ነኝ" የሚል ሽፋን ይፈልግ እንደነበር ነው፡፡ ከዚህ ባለፈ የሞፈሩ መኖር የሀገሪቱ ኢኮኖሚ በግብርና ላይ የተመሰረተ እንደነበር በማሳያነት ሊወሰድም ይችላል፡፡ በሌላ በኩል በደርግ ወታደራዊ አገዛዝ ዘመን የተፃፉ ደብዳቤዎች መግቢያ "የኢትዮጵያ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግስት" የሚል መጀመሪያ ላይ ሲይዙ በኃይለሥላሴ ዘመን የተፃፉ ደብዳቤዎች በአንፃሩ "የኢትጵያ ንጉሰ ነገስት መንግስት" የሚል መግቢያ ነበራቸው፡፡ ይህም የሚያሳየው የፖለቲካ ርእዮት አለም ሽግሽግ መኖሩን ነው፡፡ በተያያዥነት በጃንሆይ ዘመን ይፃፉ በነበሩ ደብዳቤዎች ላይ በደብዳቤው መደምደሚያ ላይ "ከሠላምታ ጋር" "ከአክብሮት ጋር" ወዘተ የሚሉ ቃላትን ይጠቀሙ እንደነበር በጃንሆይ ዘመን የተፃፉ ደብዳቤዎች ከአባረዎቹ ላይ በመመልከት መረዳት ይቻላል፡፡ ነገር ግን በወታደራዊ የደርግ ስርዓት "ከሠላምታ ጋር" እና "አክብሮት ጋር" በሚለው ቦታ "ኢትዮጵያ ትቅደም"፣ "ከህብረተሰባዊት ኢትዮጵያ ጋር ወደፊት" ወዘተ በሚሉ ገለፃዎች ወይም መፈክሮች ተተክተው እናገኛለን፡፡ ይሄም የሚያሳየው በደርግ ዘመን ከግለሰባዊነት ይልቅ ኢትዮጵያዊነት በሰፊው ይቀነቀን እንደነበር ከማሳየቱም ባለፈ ሀገራዊ ብሄረተኝነት ከፍተኛ ደረጃ መድረሱን እና ከሁሉም ነገር በፊት ሀገር የሚል መልዕክት ያለው ስያሜ ይመስላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የግርጌ መሀተሙን በምንመለከትበት ጊዜ በወታደራዊ የደርግ ዘመን የተጻፉ ደብዳቤዎች በወቅቱ የነበረችውን የኢትዮጵያ ካርታ በውስጡ ይዞ በኢትዮጵያ ካርታ መሀል ላይ "ኢትዮጵያ ትቅደም" የሚል ፅሁፍ ሰፍሮ ይታያል፡፡ በጃንሆይ ዘመን በነበሩ የግርጌ መሀተሞች ላይ በአንፃሩ የዘውዳዊውን አገዛዝ የሚያንፀባርቁ ምስሎች እና የቀዳማዊ ሀይለስላሴ ስም መያዛቸውን እናያለን፣ ይህ የሚያሳየው በደርጉ ዘመን የነበረው ሀገራዊ ብሄረተኝነት (Nationalism) እንደነበረ እና በአንፃሩ በንጉሳዊው አገዛዝ ስርዓት ንጉሱ ምን ያህል የፖለቲካውን፣ የአስተዳደሩን፣ ሀገራዊ ምስሉን እና ብሄረተኝነቱን ተጭነውት እንደነበረ እና የግለሰብ የበላይነትን ከሀገራዊ ብሄረተኝነት የበለጠ ለማጉላት ትኩረት ይደረግ እንደነበር ነው፡፡

በሌላ በኩል በደርጉ ሥርዓት የተፃፉ ደብዳቤዎችን አንድ አንድ አገላለፅ በምንመረምርበት ጊዜ የጃንሆይ ዘመን አልፎ አዲሱ የወታደራዊ ደርግ ስርዓት በሚመጣበት ወቅት የፖለቲካ አሥተዳደር ማህበራዊ ለውጥ ለማምጣት እየጣርኩ ነው የሚል አዓይነት መልዕክት ያላቸው ቃላት እና ገለፃዎች እንመለከታለን፡፡ ለምሳሌ በአባሪ ቁጥር አሥር ላይ በቀረበው ደብዳቤ ውስጥ

"ሁለት ዓመት በእስር ሲንገላቱ ከቆዩ በኃላ ነፃነታቸው ሲመለስ መፈታታቸውን እና እስከዛሬ በግብርና ስራ የሚተዳደሩ መሆኑን........" የሚል ገለፃ ይገኛል፡፡ ከዚህ ሃሳብ በመነሳት ወደ ትንተና ስንገባ የሚከተለውን እንመለከታለን፡- አዲሱ ወታደራዊ ስርዓት ለሀገር ባለውለታ የነበሩ እና የውጭ ወረራን የተዋጉ አርበኞች በቀደመው (በጃንሆይ) ስርዓት በቂ የሆነ ማህበራዊ ክብርና ኢኮኖሚያዊ ድጎማ አልተደረገላቸውም በማለት የቀደመውን ስርዓት ለመኮነን የተጠቀመበት ሁኔታን ማየት ይቻላል፡፡ በአንፃሩ አዲሱ ወታደራዊ ስርዓት ግን እነዚህን የሃገር ባለውለታዎች ትኩረት ሠጥቶ አስታውሰናቸዋል የሚል መልዕክት እንዳለው አመላካች ሊሆን ይችላል፡፡ በተለይ በገለፃው ውስጥ "እስከዛሬም" የሚለው አባባል አዲሱ የህብረተሰባዊነት የደርግ ስርዓት ሃሣቡን ለማግዘፍ እና ያለፈው ሥርዓት የሠራውን ስህተት ለማጉላት የተጠቀመው አካሄድ መሆኑን ያሣየናል፡፡ በ "እስከዛሬም" አገላለፅ ውስጥ ቁጭት፣ ንዴት፣ አሁን በ "እኛ" ስርዓት እንደማይደገም፣ እና...... የሚሉ መልዕክቶች ለማስተላለፍ ታስቦ የቀረበ ሊሆን ይችላል፡፡

Norman Fairclough የተባለ ፀሐፊ እንደሚገልፀው በአንድ የሰነድ ትንተና ወቅት ወሳኝ የሆኑ ቃላት እና አያያዦች ስለሚተነተነው ሰነድ ትልቅ የአመልካችነት ሚና እንዳላቸው ይገልፃል፡፡ Norman Fairclough (2003)፡፡

በሌላ በኩል "እንገልፃለን" እና "እየገለፅን" የሚሉ የሃሳብ ማሠሪያ ቃላት ተጠቅሰዋል፡፡ ይህም የተገለፀው ሃሣብ የግል ምልከታ ወይም የትኩረት አቅጣጫ ሳይሆን እንደ ቡድን ወይም እንደ ተቋም የተላለፈ በመሆኑ ሥርዓቱ ከግለሰቦች ይልቅ በቡድን ወይም በተቋም ላይ መሠረት ያደረገ ነው የሚል አንድምታ እንዳለው ለማሳየት የታሠበ ይመስላል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ Tabassum Iqbal እና Behzad Anwar የተበሉ ፀሀፊዎች እንደሚገልፁት ሃሳቦችን በቡድን ባለቤትነት መስጠት ወይም እኛ በሚል አገላለፅ ሃሣብን ማስፈር በሚፃፈው ጉዳይ ዙሪያ ሃላፊነትን መውሰድ ከመፍራት የሚመነጭ መሆኑን ይገልፃሉ፡፡ ስለዚህም በዚህ ደብዳቤ ውስጥ እነኚህ ከላይ የተጠቀሱ አገላለፆች መጠቀሳቸው ምንአልባትም ሃሳቡ ስለመተግበሩ ምንም አይነት መተማመኛ ባለመኖሩ ከዚህ ጋር ተያይዞ ስለሚመጣው ተጠያቂነት ራስን ለማሸሽ ታስቦ የተደረገ ስልታዊ ማፈግፈግ ሊሆን እንደሚችልም አመላካች ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ይህንን ሃሣብ በአባሪ ቁጥር አስራ አንድ ውስጥም በጉልህ ተገልፆ እንመለከተዋለን፡፡

በአባሪ ቁጥር አሥራ አንድ ላይ በቀረበው ደብዳቤ ውስጥ እንደሚታየው ደብዳቤው በተፃፈበት ዘመን የነበረው የፖለቲካ አወቃቀር የትእዛዝ አሰጣጥ በሚታይበት ጊዜ ከግለሰብ ይልቅ ቡድንና ተቋም ጉልህ ሥፍራ እንደነበር ነው፡፡ በዚህ መሠረት በደብዳቤው ላይ "የእኛ" ባለቤትነት ሰፊውን ድርሻ ይዞ ይታያል፡፡ እንደ Norman Fairclogh ገለፃ አንዳንድ ሰነድ በምንመረምርበት ወቅት በሰነዱ ውስጥ የሰፈረው ሃሳብ ባለቤቱ እንዴት እንደተወከለ ማወቅ በወካዩ እና በተወካዩ መካከል ያለውን ግንኙነት እንድንረዳ ያመለክታል፡፡Norman Fairclogh (2003)::

በአባሪ ቁጥር አሥራ ሁለት ላይ የቀረበውን ደብዳቤ በምናይበት ጊዜ "ለብዙ አመታት በችግር በድንቁርናና በበሽታ ሲሰቃይ የኖረው ሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ..." የሚል ይገኛል፡፡ በዚህ ሃሳብ ውስጥ "ድንቁርና" የሚለውን አገላለፅ እና ቃል በምናይበት ጊዜ በወቅቱ በነበረው ፖለቲካ ማህበረሰቡ የነበረው የፖለቲካ ንቃት እና ተሳትፎ ዝቅተኛ መሆኑን ሊያሳየን ይችላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ "በበሽታ" "በስቃይ" እና "ብዝበዛ" የሚሉት ቃላት መሪው በተመሪው ላይ ከማገልገል ይልቅ ይገለገልበት እንደነበረና ህዝቡም የፖለቲካ መብቱን እንዲጠቀም የማይፈቀድለት እንደነበረ ያሳያል፡፡ በተመሳሳይ በአባሪ ቁጥር አስራ ሁለት ላይ በሰፈረው ደብዳቤ ላይ ደብዳቤው በተፃፈበት ዘመን የነበረው ወታደራዊ የደርግ ስርዓት የ"አብዮታዊነት" ውክልና እና ስያሜ ተሰጥቶት እናያለን፡፡ ለዚህም ማሳያው በደብዳቤው ውስጥ የደርግ ስርዓት እንደ "በዝባዥ" እና "ጨቋኝ" የሚሉ

ስያሜዎችን ባለመጠቀም እና በህዝቡ ላይ ይደርስ የነበረው አስተዳደራዊ በደል ማለፉን በመሳል እራሱን ወይም የደርጉን ስርዓት እንደ ለውጥ ሀዋርያ እና ነፃነት ሰጪ አድርጎ ለማቅረብ የሞከረበት ነው ብለን ማቅረብ እንችላለን፡፡ ምክንያቱም የደርጉ ስርዓት የጃንሆይን ሥርዓት "ጨቋኝ" "በዝባዥ" "የድንቁርና" መሰረት ወዘተ እያለ ሲገልፅ የራሱን ሥርዓት ከዚህ የፀዳ መሆኑን እና ያለፈውን እያወገዘ መሆኑን አማላካች ሆኖ ሊታይ ይችላል፡፡ ከዚህ ባለፈ በደብዳቤው ውስጥ የደርግን ስርዓት "በመለስተኛ ብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ"መንግስትነት ሰይሞት እናገኘዋለን፡፡ ይህንን ለማድረግ የተሞከረው ወታደራዊው ደርግ የነበረበትን የአንባገነንነትን ሥርዓት ዲሞክራሲያዊነትን የሚያላብሱ ስያሜዎችን በመጠቀም ውዥንብር ለመፍጠር እና የፖለቲካ ስርዓቱን በጥልቀት ለማያውቁ ሀገራዊ እና አለማቀፋዊ ተቋማት ዲሞክራሲያዊ ስርዓት የሰፈነ በማስመሰል የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት ታስቦ ይመስላል፡፡

በሌላ በኩል በዚህ ደብዳቤ ውስጥ የወታደራዊውን የደርግ ስርዓት "አብዮታዊነት" (Revolutionary Government) ስያሜ ተሰጥቶት እንመለከታለን፡፡ እንደሚታወቀው አብዮት በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የሚደረግ ፈጣን፣ መሠረታዊ የሆነ የአስተዳደር ስርዓት ተቋማዊ ለውጥ የሚያመጣ፣ በፖለቲካዊ፣ በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊ ወዘተ መዋቅር ላይ መሰረታዊ በሆነ መልኩ ፈጣን ለውጥ የሚያመጣ ከመሆኑ ባለፈ አንድ የአስተዳደር ስርዓት ወይም መንግስት ስለፈለገ የሚያውጀው ሳይሆን በጊዜ ሂደት ውስጥ ሁኔታዎች ሲፈቅዱ እና አስገዳጅ ሲሆኑ ከቁጥጥር ውጭ በሆነ መልኩ ሂደቱን ጠብቆ የሚፈነዳ ህዝባዊ እንቅስቃሴ ነው፡፡በዚህ የተነሳ "Revolutions are not made" ይባላል፡፡ ነገር ግን በዚህ ደብዳቤ ላይ የወታደራዊ ደርግ መንግስት እራሱን እንደ የአብዮት ፈጣሪ እና ሀዋርያ በመሳል እና በመሰየም እንዲሁም ለውጥ ያመጣ በማስመሰል በህብረተሰቡ ቅቡልነትን ለማግኘት በማሰብ ይመስላል የአብዮታዊነት ስያሜ ለስርዓቱ የሰጠው፡፡ በተመሳሳይ በደብዳቤው ውስጥ ሁለተኛው አንቀፅ ላይ "ያለ አድሎ" የሚል ቃል ሰፍሮ እናገኛለን፡፡ ይህም የሚያሳየው በወቅቱ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ እና ኢኮኖሚያዊ ግለጋሎቶችን መደብን እና የስልጣን ደረጃ መሰረት ባደረገ መልኩ ከእኩልነት ውጭ ተግባር ላይ ይውሉ እንደነበር ሊያመላክት ይችላል፡፡ እንዲሁም "ያለ አድሎ የትምህርት ተሳትፎ በኢትዮጵያ" በሚል መፈክር በሚመስል መልኩ በደብዳቤው ሁለተኛው አንቀፅ ላይ የሰፈረውን ሀሳብ በምናይበት ጊዜ ምንአልባት ከ1966ቱ የኢትዮጵያ አብዮት በፊት የነበረውን የፊውዳሉን ስርዓት ምንነት ለማመልከት የታሰበ ይመስላል፡፡ ይህም ማለት በፊውዳሉ ስርዓት የትምህርት እድል በአመዛኙ ከብዙሃኑ የህዝብ ልጅ እና ከጭሰኞች ልጅ ይልቅ ለፊውዳሉ እና ለገዢው መደብ በሰፊው ይደርሰው እንደነበር ለማመልከት ታስቦ የቀረበ ይመስላል፡፡ ወይም ደግሞ ባጭሩ የእኩልነት እና የፍትሃዊ የሀብት ክፍፍል ችግር መኖሩን አመላካች ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡

በአባሪ ቁጥር አስራ ሦስት ላይ የመሰረተ ትምህርትን አስመልክቶ በተፃፈ ደብዳቤ ላይ "በሀገር ውስጥ መወደድን፣ በማህበረሰብ ዘንድ አድናቆትን ያተረፈው የብሄራዊ መሰረተ ትምህርት ዘመቻ ፕሮግራም……" በሚለው ገለፃ ውስጥ "መወደድ" እና "አድናቆት" የሚሉትን ቃላት ከደብዳቤው መሰረታዊ ፅንሰ ሀሳብ ጋር በማስተሳሰር በምናይበት ጊዜ በወታደራዊው የደርግ ስርዓት የሚወጣው ፖሊሲ ፍፁም የተሟላ ነው በህብረተሰብ ውስጥ ተቀባይነት አለኝ ምንም አይነት ተቃውሞ የለም በማለት የመንግስትን የበላይነት እና በህዝቡ ዘንድ ያለውን ተቀባይነት ህጋዊነት (legitimacy) ለማሳየት እና ለማስቀጠል በማሰብ የቀረበ ሀሳብ ይመስላል፡፡ በተጨማሪ በደብዳቤው ውስጥ መሰረተ ትምህርትን ለማስፋፋት "ዘመቻ" መደረጉ ይገልፃል፡፡ በገለፃው ውስጥ "ዘመቻ" የሚለውን ቃል በምናይበት ጊዜ በዘመቻ ውስጥ አዝማች አለ እንዲሁም ዘማች አለ፡፡ በመሆኑም ለዘመቻው አዝማች የሚሆነው መንግስት ሲሆን ዘማቹ ደግሞ ለዘመቻው በዘማችነት የተመለመለው ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ይህም

አዝማች በዘማቹ እና በተዘማቹ የማህበረሰብ ክፍል ያለውን የፖለቲካ የበላይነት፣ ከአሳታፊነት ይልቅ የአዛዥነትን ሚና ይጫወት እንደነበር ነው፡፡ በተመሳሳይ በደርጉ ዘመን የተፃፉ ደብዳቤዎች ላይ የሚታዩ አብዮት፣ ዘመቻ፣ ህብረተሰባዊነት ወዘተ የሚሉ ቃላትን በየቦታው መመልከታችን በወቅቱ የነበረው ሥርዓት መሰል አደናጋሪ ቃላትን ሽፋን በማድረግ ህብረተሰቡን ከመምራት እና በፖለቲካው ውስጥ ከማሳተፍ ይልቅ ከኃላ ሆኖ ይነዳው እንደነበር ሊያሳየን ይችላል፡፡ ወይም ደግሞ ባዶ ቅስቀሳዎችን ተጠቅሞ ተቀባይነት ለማግኘት የሚጠቀምበት መንገድ ሊሆን እንደሚችል እንረዳለን፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በደብዳቤው ላይ "....... በገንዘብ መዋጮ ከፍተኛ ድጋፍ......." የሚል አገላለፅ አለ፡፡ በተለይ ከዚህ አገላለፅ ውስጥ "ድጋፍ......" የሚለውን ቃል ስንወስድ መሪው በተመሪው ላይ ያሳድር የነበረውን ጫና በተለሳለሱ ቃላት ለማድበስበስ ይጥር እንደነበር ያሳየናል፡፡ ነገር ግን ይህ የገንዘብ መዋጮ በመመሪያ እና በህግ የተላለፈ እና "ግዳጅ" እንደነበር በደብዳቤው በአራተኛው አንቀፀ ላይ የተገለፀ መሆኑን እናስተውላለን፡፡ በዚሁ መሠረት በወቅቱ ግዳጅ የሆኑ ተሳትፎዎችን እና ክንውኖችን በተለሳለሰ እና ዲፕሎማሲያዊ ቋንቋዎች እንዲቀርቡ የሚደረገው የስርዓቱን ከህዝብ ይሁንታ ውጭ ድርጊቶችን እና አንባገነናዊነትን ለማድበስበስ በማሰብ ሊሆን ይችላል፡፡

በአባሪ ቁጥር አሥራ አራት ላይ በቀረበው ስለ ግል ንብረት ባለቤትነት በሚያትተው ደብዳቤ ላይ "በህዝብ ቁጥጥር ስር ስለዋሉት የግል ትምህርት ቤቶች አመራርና አስተዳደር" የሚል አገላለፅ ሰፍሮ ይገኛል፡፡ በዚህ ገለፃ ውስጥ "በህዝብ ቁጥጥር" የሚለውን በምናይበት ጊዜ በወቅቱ የነበረው የአስተዳደር ክፍል በመንግስት የተወሰዱትን እርምጃዎች ህዝባዊነት በማላበስ ከኃላፊነት እና ተጠያቂነት ለመሸሽ ያደረገው ሊሆን ይችላል፡፡ምክንያቱም የድርጊቱን ባለቤት በጅምላ "ህዝብ" ለሚባል ክፍል መስጠት የትኛው ህዝብ; የሚለውን ጥያቄ የማይመልስ እና ለምስጠራ አመቺ የሆነ አገላለፅ በመሆኑ ለተጠያቂነት አስቸጋሪ ስለሆነ ነው፡፡ በሌላ በኩል "በህዝብ ቁጥጥር ስር" የሚለው አገላለፅ ምንም እንኳን በወቅቱ የነበረው ስርአት አምባ ገነናዊ ስርዓት ቢሆንም እንደዚህ ያሉ ገለፃዎችን በሰባኪነት በመጠቀም እና ወደ ህብረተሰቡ እንዲሰርፅ በማድረግ የስልጣን ዘመን ለማራዘም እና ተቃውሞን ለማቀጨጭ ታስቦ የቀረበ ሊሆን ይችላል፡፡

በአባሪ ቁጥር አስራ አምስት ላይ በቀረበው ደብዳቤ ላይ "በቀድሞው የአሜሪካን ማሲዬን ኃላም ቤተል መካነ ኢየሱስ ይባል የነበረው የትምህርት ቤት አዲስ ስያሜ እንዲሰጥ በታሰበው ሀሳብ መሠረት ከቀረቡት ስያሜዎች መካከል 'የለውጥ ፍሬ' በመባል እንዲሰየም......" የሚል ገለፃ ይገኛል፡፡ በዚህ ገለፃ ወስጥ መረዳት የምንችለው በወቅቱ በነበረው የፖለቲካ ስርዓት መንግስት እና ሃይማኖት የተለያዩ ናቸው የሚል መርህ የሚያራምድ መሆኑን ያሳየናል፡፡ከዚህ ባለፈ "የለውጥ ፍሬ" እንዲባል መደረጉ በወቅቱ የነበረው ስርዓት ባደረገው ትግል የተገኘ መሆኑን እና ማህበረሰቡም የለውጡ ተካፋይ መሆኑን ውክልና ለመስጠት ታስቦ የተደረገ ሊሆን ይችላል፡፡ ሌላው ነጥብ ለትምህርት ቤቱ የሰጠው አዲስ ስም ትምህርት ቤቱ በሚገኝበት አካባቢ የብሄር ቋንቋ ተተርጉሞ መቅረቡ በወቅቱ የነበረው የህብረተሰባዊት ኢትዮጵያ ርዕዮት አለም አራማጅ መንግስት ለብሄረሰብ ቋንቋ እውቅና ይሰጥ እንደነበር ለማመልከት የተደረገ መሆኑን ያሳየናል፡፡

#### 4.2.2. ማህበራዊ ጉዳዮች ትንተና

በደርግ ዘመን በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የተፃፉ የስራ ደብዳቤዎች ከማህበራዊ ትርጉማቸው አንፃር ለማየት በአመላካችነት በአባሪ ቁጥር አስራ ሁለት ላይ የቀረበውን ደብዳቤ ማየት ይቻላል፡፡ በዚህ ደብዳቤ ላይ ከአጠቃላይ ማህበራዊ ግልጋሎት፣ ማህበራዊ አመለካከት እና ንቃት አኳያ የነበረውን ሁኔታ አመላካች ነጥቦች ተቀምጠው ይገኛሉ፡፡ በዚሁ መሰረት በደብዳቤው ላይ "...... ለብዙ አመታት በችግር እና በድንቁርና በበሽታ ሲሰቃይ የኖረው ሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ ...... የተዛባውን

የትምህርት ስርዓት ችግር በትክክለኛ መረጃ ተመርኩዞ ....” የሚል አገላለፅ ሰፍሮ እናገኛለን፡፡ ከዚህ አገላለፅ ውስጥ “ለብዙህ አመታት በችግርና በድንቁርና” የሚለው ገለፃ የማህበረሰቡን የኑሮ ሁኔታ ከማሳየቱ ባለፈ “ድንቁርና” የሚለው ቃል ማህበረሰቡ እንደ ማህበረሰብ የነበረበትን የስልጣኔ እና የዕድገት ደረጃ ያመለክታል፡፡ ይህ ማለት ደግሞ የሕብረተሰቡ አኗኗር ከምክንያታዊነት፣ ከጠያቂነት እና ከለምን ባይነት ይልቅ በዝምታ ሁሉን ተቀባይነት ባህሉ አድርጎት ይኖር እንደነበር ሊያመላክተን ይችላል፡፡ ወይም ደግሞ “.....ንጉስ አይከሰስ” የሚለውን ምሳሌያዊ አነጋገር የተገበረ መሆኑን ሊያሳይ እንደሚችል የገለፁበት ሊሆን ይችላል፡፡ በተጨማሪ “በበሽታ ሲሰቃይ የኖረው ሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ ....... ለአያሌ ዘመናት የተዛባውን የትምህርት ስርዓት ችግር .....” ከሚለው አገላለፅ የምንረዳው በወቅቱ የትምህርት ስርዓቱ ከሰፊው ህዝብ ይልቅ በኢኮኖሚ እና በፖለቲካ ከፍተኛ ሥፍራ ላላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ይሰጥ እንደነበር እና የማህበራዊ ግልጋሎት በአንድ አካባቢ በሚኖሩ ማህበረሰቦች መካከል በእኩልነት የመስጠት ችግር መኖሩን ያመላክተናል፡፡ለዚህም ማሳያ የሚሆነን “አያሌ ዘመናት የተዛባውን የትምህርት ስርዓት ችግር” የሚለው ነጥብ ነው፡፡ በተመሳሳይ በማህበረሰቡ ውስጥ ትምህርት እንደ ባህል እና መሰረታዊ ጉዳይ ሳይሆን እንደ ቅንጦት ይወሰድ እንደነበር በዚሁ በአባሪ ቁጥር አስራ ሁለት እና በአባሪ ቁጥር አሥራ ሦስት ላይ የቀረቡት ሀሳቦች አመላካች ተደርገው ሊወሰዱ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ “ያለአድልዎ የትምህርት ተሳትፎ” የሚለው ገለፃ በአባሪ ቁጥር አስራ ሁለት ላይ በቀረበው ደብዳቤ በአንቀፅ ሦስት ላይ በምናይበት ጊዜ ከላይ ለመገለፅ እንደተሞከረው በማህበረሰቡ ውስጥ ከማህበራዊ፣ ከኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ የበላይነት እና የበታችነት ጋር በተያያዘ እኩል ያልሆነ የማህበራዊ አገልግሎት ተጠቃሚነት እንደነበር በአማላካችነት ሊወስድ ይችላል፡፡

በአባሪ ቁጥር አስራ አምስት ላይ በተያያዘው ደብዳቤ በአንቀፅ አንድ ላይ “...... ትምህርት ቤት በሚገኝበት የብሄረሰብ ቋንቋ ተተርጉሞ ስያሜው እንዲሆን......” የሚል አገላለፅ ሰፍሮ እናገኛለን፡፡ ከዚህ አገላለፅ የምንረዳው በወቅቱ ማህበረሰቡ የባህል አንድ መሠረታዊ ነጥብ የሆነውን ቋንቋውን ለማንነቱ መግለጫ እና ከሌላው ብሄረሰብ ጋር እራሱን በማስተዋወቂያ እና ማስተሳሰሪያነት ይገለገልበት እንደነበር ሊያሳየን ይችላል፡፡

#### 4.2.3. ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ትንተና

በአባሪ ቁጥር አስራ ሁለት ላይ የቀረበው እና በ1978 ዓ.ም የተፃፈው ደብዳቤ ላይ “.....ሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ አብዮቱ ከመጣለት እና የበዝባዡን ስርአት ማህበር ከጣለ ወዲህ......” የሚል አገላለፅ ሰፍሮ ይገኛል፡፡ ከዚህ አገላለፅ ውስጥ “የበዝባዥ ስርዓት” የሚለውን በምናይበት ጊዜ ደብዳቤው ከተፃፈበት የወታደራዊ ደርግ ሥርዓት በፊት የነበረው የዘውዳዊ አገዛዝ የአስተዳደር አካል በማህበረሰቡ ላይ ያደርስ የነበረውን የኢኮኖሚ ጫና በአመለካችነት ሊያሳየን ይችላል፡፡ ከዚህ ባለፈ “በዝባዥ” የሚል ቃል ካለ “ተበዝባዥ” የሚል ቃል መኖሩ ግድ ይላል ምክንያቱም በዝባዥን ያለ ተበዝባዥ ብቻውን ማቆም ስለማይቻል፡፡ በዚሁ መሠረት በወቅቱ ሁለት ዋና ዋና የኢኮኖሚ መደብ መኖሩን ሊያሳይ ይቻላል፡፡ እነሱም በዝባዡ እና የላይኛው መደብ አንድ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ተበዝባዥና የታችኛው መደብ ነው፡፡ ነገር ግን በኢኮኖሚ የመካከለኛ መደብ ወይም የቡርዣ መደብ የሚለው በወቅቱ እምብዛም ሥር የሌለው መሆኑንም ሊያመለክተን ይችላል፡፡ ወይም ደግሞ በሌላ አገላለፅ በኢኮኖሚው ረገድ ያለው መደብ የፊውዳሉ ወይም በዝባዥ ሚል ስያሜ የቀረበ የመሬት ከበርቴው እና የስልጣን ባለቤት የሆነው ሲሆን ሌላው እና ተበዝባዥ የሆነው የታችኛው መደብ ወይም ጭሰኛው የሚለውን እይታ እንድናዳብር ሊያደርገን ይችላል፡፡

በሌላ በኩል በአባሪ ቁጥር አሥራ አራት በቀረበው ደብዳቤ ሁለተኛ አንቀፅ ላይ የግል የሆኑት ትምህርት ቤቶች በህዝብ ቁጥጥር ስር እንዲውሉ በአዋጅ መደንገጉን የአዋጅ ቁጥር በመጥቀስ ያብራራል፡፡ ይህ የሚያሳየን በወቅቱ የነበረው የአስተዳደር የኢኮኖሚ ስርዓት እና ፖሊሲ ከነፃ ገበያ ይልቅ የዕዝ የኢኮኖሚ ስርዓት አራማጅ መሆኑን እና ከግል ንብረት ይልቅ የወል ንብረት ማፍራት የሚበረታታ እንደነበር እና የህብረተሰባዊነት የኢኮኖሚ ሥርዓት በሀገሪቱ በሕጋዊነት በአዋጅ ይሰራ እንደነበር ያሳየናል፡፡ በተጨማሪ በኢኮኖሚው ውስጥ የግሉ የአገልግሎት ዘርፍ እንቅስቃሴ ደካማ መሆኑን እና በግሉ የኢኮኖሚ የአገልግሎት ዘርፍ ለመሳተፍ የሚፈልጉ ዜጎች ንብረታቸው በሕዝብ ሥም ይወረስ እንደነበር በዚሁ በአባሪ ቁጥር አሥራ አራት ላይ የቀረበው ደብዳቤ ያሳየናል፡፡ ይህም በወቅቱ የነበረው ርዕዮት አለም በግሉ የኢኮኖሚ እና የአገልግሎት ዘርፍ ዙሪያ የሚከተለውን የኢኮኖሚ ፖሊሲ በአመላካችነት ሊያሳየን ይችላል፡፡ ከዚህ ሌላ በዚህ ደብዳቤ ላይ የተነሱት ሃሳቦች የሚያሳዩን የህብረተሰባዊነት ርዕዮት አለምን ከለላ በማድረግ የቀደመው ስርዓት የግል ንብረት ያፈሩ እና ለአዲሱ ስርዓት ችግር ሉሆኑ የሚችሉ አድህሪዎችን “መሬት ላራሹ” በሚል እና መሰል እርምጃዎች አቅማቸውን በማዳከም በህብረተሰቡ ውስጥ የኢኮኖሚ እኩልነት መጥቷል የሚል እይታ ለመፍጠር ታስቦ የመጣ ሲሆን ይችላል ብለን እንድናስብ ሊያደርገንም ይችላል፡፡ በተጨማሪ ከግል ይልቅ የወል ሀብቶች እንደሚበረታቱ ለማሳየት ከግለሰቦች የተወረሱትን ንብረቶች በመንግስት ቁጥጥር ሥር ዋሉ ከሚለው አገላለፅ ይሳቅ “በህብረተሰቡ ቁጥጥር ስር የዋሉትን” የሚል አገላለፅ መጠቀሙን እናያለን፡፡ ይህም የሚያሳየን የወቅቱ የአስተዳደር ሥርዓት ፍትሀዊ የኢኮኖሚ ስርአት እየገነባ መሆኑን ለማሳየት የተጠቀመበት መሆኑን ሊያሳየን ይችላል፡፡

## 4.3. በኃይለሥላሴ እና በደርግ ዘመን በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የተፃፉ ደብዳቤዎች

### *መዋቅራዊ ሁኔታ እና ከዘመን ዘመን ያሳዩዋቸው ለውጦች*

ከመዋቅር አኳያ በጃንሆይ ዘመን የተፃፉ ደብዳቤዎችን በምናይበት ጊዜ አብዛኛዎቹ ደብዳቤዎች በርዕስ አሰጣጣቸው ላይ አባባይ፣ አሞካሽ እና ድርብርብ የማዕረግ ስሞችን በመጠቀም ይጀምራሉ፡፡ ለምሳሌ በወቅቱ በርዕስ እና በደብዳቤዎቹ መግቢያ ላይ በሰፊው የሚስተዋሉ ገለፃዎች ወይም የቋንቋ አጠቃቀሞች የሚከተሉት ናቸው፡- ለክቡርነትዎ፣ ለክቡር ጌታችን፣ ለክቡር ጌታችን ደጃዝማች፣ ግራዝማች፣ ቀኝ አዝማች ፊታውራሪ ወዘተ፣ ለክቡር ሌፍተናንት፣ ለክቡር ጄኔራል፣ለክቡር አቶ፣ ለልበ ብርሃኑ እና መሰል የሹመት ስያሜዎች እና የማባበያ ቃላትን በመጠቀም ይፃፍ እንደነበር ከአባሪ ቁጥር አንድ እስከ አባሪ ቁጥር አስር በጃንሆይ ዘመን የተፃፉ ደብዳቤዎችን በማየት ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ እነዚህ አይነት አገላለፆች እና የማባበያ ቃላትን ለምን በወቅቱ በሠፊው ጥቅም ላይ ዋሉ ለሚለው በጃንሆይ ዘመን በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የተፃፉ ደብዳቤዎች የቋንቋ አጠቃቀም ይዘት ትንተና በሚለው ርእስ ስር ተብራርቷል፡፡ በአንፃሩ በደርግ ዘመን የተፃፉ ደብዳቤዎች ርዕስ አሰጣጥ እና መግቢያ አፃፃፍ በምናይበት ጊዜ በጃንሆይ ዘመን ከተፃፉት የተለዩ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ ከላይ እንደተገለፀው በጃንሆይ ዘመን የተፃፉ ደብዳቤዎች ንጉሰ ነገስቱን እና የንጉሰ ነግስቱን ሹማምንቶች በሰፊው የሚያወድሱ ሀሳቦች እና ቃላት በርዕሶቻቸው እና በመግቢያዎቻቸው ላይ ሲንፀባረቁ በደረጉ ዘመን የተፃፉ ደብዳቤዎች ግን በርዕሳቸው እና በመግቢያቸው ላይ አብዮትን፣ ህብረተሰባዊነት ኢትዮጵያን፣ ዘመቻን፣ ኢስፖን እና ወዘተ ሀሳቦችን የሚያጎሉ እና የሚያንፀባርቁ ሆነው እናገኘዋለን፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ምንድን ነው ለሚለው በደርግ ዘመን በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የተፃፉ ደብዳቤዎች ቋንቋ አጠቃቀም ይዘት ፖለቲካ ትንተና በሚለው ርዕስ ስር ሰፍሮ ይገኛል፡፡

ከደብዳቤ ሀተታ አፃፃፍ አኳያ በምንቃኝበት ጊዜ በጃንሆይ ዘመን የተፃፉ ደብዳቤዎች አሁንም ስለሚፈፀመው ጉዳይ ተፈፃሚነት የህግ እና የአሰራር ትክክለኛነት ሳይሆን የሹማምንቶች ቅን ልቦች መሰረታዊ እንደነበር የሚያሳይ እና ከርዕስ ጉዳዩ ይልቅ የሹማምነቱ ወዳሴ የሚበዛበት መሆኑን መረዳት እንችላለን፡፡ ለማሳያነት አባሪ ቁጥር አንድን እና አምስትን ማየት

እንችላለን፡፡ በአንፃሩ በደርጉ ዘመን የተፃፉ ደብዳቤዎችን ሀተታ በምናይበት ጊዜ አዋጆችን መጥቀስ፣ ያለፈውን ስርዓት መውቀስ፣ አዲሱን የህብረተሰባዊት (Socialist) ስርዓት ማወደስ የበዛበት እንደነበር ከአባሪ ቁጥር አስራ ሁለት ጀምሮ ያሉትን ደብዳቤዎች በማየት ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት ወታደራዊው መንግስት ካለፈው አገዛዝ ፍፁም የተለየ መሆኑን ለመግለፅና ተቀባይነትን ለማግኘት ሊሆን እንደሚችልም መግለፅ ይቻላል፡፡

ከደበዳቤ መደምደሚያ አሰጣጥ አኳያ በምናይበት ጊዜ እንዲሁ በጃንሆይ ዘመን የተፃፉት ደብዳቤዎች አልፎ አልፎ ከሀተታ ውጭ መደምደሚያ የሌላቸው አሉ፡፡ ለምሳሌ በአባሪ ቁጥር ዘጠኝ ላይ ያለውን መውሰድ ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል ሌሎቹ ደብዳቤዎች ስለፃፉለት ጉዳይ ሹማምንቱን ፈጣን እና ቀና ምላሽ እና የጉዳዩን ፈጣን ተፈፃሚነት በልመና መልክ በመግለፅ "ከሰላምታ ጋር", "ከአክብሮት ጋር", "በማክበር" ወዘተ ቋንቋዎችን ይጠቀሙ ነበር፡፡በአንፃሩ በደርግ ዘመን የተፃፉ ደብዳቤዎችን መደምደሚያ አሰጣጥ በምናይበት ጊዜ ኢትዮጵያ ትቅደም፣ ከህብረተሰባዊት ኢትዮጵያ ጋር ወደፊት ወዘተ ቋንቋዎችን በመጠቀም ይደመድሙ ነበር፡፡ ይህ ደግሞ ስለሚከተሉት ርዕዮት አለም፣ የአስተዳደር ስርዓት እና ወዘተ ልዩነቶችን ያሳየናል፡፡

## ምዕራፍ አምስት

# 5. ማጠቃለያ መደምደሚያ እና አስተያየት

## 5.1 ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ከ1922-1983 ዓ.ም. ድረስ የተፃፉ የስራ ደብዳቤዎችን የቋንቋ አጠቃቀም መተንተን እና መመርመር መሆኑ በቀዳሚዎቹ ምዕራፎች ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ በዚህም መሠረት በጥናቱ በቀዳሚነት መልስ እንዲገኝላቸውየተቀመጡት መሠረታዊ ጠያቄዎች የሚከተሉት ነበሩ፡፡

- ከ1922-1983 ዓ.ም. ድረስ የተፃፉ የስራ ደብዳቤዎች የቋንቋ አጠቃቀም ሲመረመር ደብዳቤዎቹ በተፃፉበት የዘመን መንፈስ የነበረው ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ሁኔታ ምን ይመስል ነበር?
- በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ከ1922-1983 ዓ.ም. ድረስ የተፃፉ የስራ ደብዳቤዎች አጠቃላይ የአፃፃፍ ስልታቸው ምን ይመስል ነበር?
- ከ1922-1983 ዓ.ም. ድረስ የተፃፉ የስራ ደብዳቤዎች መዋቅር ወይም መግቢያ፣ ሀተታና መደምደሚያ ከዘመን ዘመን ያላቸው ልዩነቶች ምንድን ናቸው?

ከላይ በመሪነት የቀረቡትን የጥናቱን መሰረታዊ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት እንዲቻል ከ1922-1983 ዓ.ም. ድረስ በተለያዩ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የተፃፉ መደበኛ የስራ ደብዳቤዎችን ከተለያዩ ተቋማት ለምሳሌ ከጅማ ከተማ አስተዳደር፣ ከሀዲያ ዞን፣ ከቤንች ማጂ ዞን እና ከአዲስ አበባ ወልደመስቀል ታሪኩ የሰነድ ማዕከሎች በመሰብሰብ ለጥናቱ ምቹ የሆኑትን ደብዳቤዎች የጥልቅ የዲስኩር ትንተና ዘዴን በመከተል ለመተንተን ተሞክሯል፡፡ አጥኚዋ ለትንተና የተመረጡትን ደብዳቤዎች እና በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ያሉት አካባቢዎች ብዙ ከመሆናቸው የተነሳ ደብዳቤዎቹን የመረጠችው አመቺ ናሙና ዘዴን በመጠቀም ነው፡፡ በትንተናው ወቅት አጥኚዋ በትንተና ላይ ያዋለቻቸው የመደበኛ ደብዳቤ ብዛትም አስራአምስት ሲሆን የእነዚህን ደብደቤዎች መዋቅር እና ቃላት አጠቃቀም የተለያዩ ፅሁፎችን በዳራነት በመጠቀም እና የጥልቅ ዲስኩር ትንተና መርህን በመከተል ለመተንተን ሞክራለች፡፡ ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው በዚህ ጥናት ውስጥ ዋነኛው የመረጃ ምንጭ ጥናቱ በሚያካትተው ዘመን እና ክልል /አካባቢ/ የተፃፉ መደበኛ ደብዳቤዎች ናቸው፡፡ በመረጃነት የተወሰዱትን ደብዳቤዎች መሠረት በማድረግም ለጥናቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ተሞክሯል፡፡ በትንተናው ወቅትም የደብዳቤዎቹን መዋቅር ማለትም እንደ ቀን፣ የደብዳቤ ቁጥር፣ የላኪ እና የተቀባይ አድራሻ አቀማመጥ፣ ትንተና እና መዝጊያ አሰጣጥ፣ ፊርማ፣ የመስሪያ ቤት አርማ፣ ማህተም ወዘተ ነጥቦችን Abirdeen (2011) እና Sundrive (2006) በምን መልኩ መፃፍ እንዳለባቸው የገለፁትን ገለፃ በመከተል እና ከዘመን ዘመን ያላቸውን ለውጥ ለማብራራት እና ደብዳቤዎቹን ከነዚህ ነጥቦች አኳያ ለመተንተን ተሞክሯል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በትንተና ወቅት የሚተነተኑትን ደብዳቤዎች ትክክለኛነት ወይም ያልተጭበረበሩ መሆኑን ለማረጋገጥ ደብዳቤዎቹ በተፃፉበት ዘመን የነበሩ ታሪኮችን እና ከሌሎች ተመሳሳይ ደብዳቤዎች ጋር በማረጋገጥ ወይም በወቅቱ በነበረው ሹም ሰው ስም የወጡ ሌሎች ደብዳቤዎችን በማየትና በማመሳከር እንዲሁም በማስተያየት የመረጃ ምንጮቹን እውነተኛነት ለማረጋገጥ ተሞክሯል፡፡

በትንተና ወቅት ወይም የደብዳቤዎቹን ቋንቋ አጠቃቀም ይዘት በሚተነተንበት ወቅትም ከዚህ ቀደም ኢትዮየጵያ እና ከኢትዮጵያ ውጭ የተለያዩ ፀሀፍት በተለያዩ የትምህርት ዘርፎች የደብዳቤዎችን የቋንቋ አጠቃቀም ይዘትና መዋቅር ትንተና አካሄድ በምሳሌነት በመውሰድ ለመስራት ጥረት ተደርጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በጥናቱ ውስጥ ደብዳቤዎቹ ከአርማ አጠቃቀም አና ውስጣዊ ይዘት አኳያ በተለያዩ ጊዜያት የነበራቸውን ለውጥ ለማየት ተሞክሯል፡፡ ለምሳሌ በጃንሆይ ዘመን ይፃፉ የነበሩ አብዛኛዎቹ ወይም ሁሉም በሚባል ደረጃ በራስጌ አርማነት የአንበሳ ምስል እና አንበሳው በቀኝ የፊት እግሩ ባንድራ ያነገበ በሰንደቅ አላማ መያዣነት በአንበሳው የቀኝ የፊት እግር የተያዘው ዘንግ አናት ላይ የመስቀል ምልክት ያለው እንዲሁም በአንበሳው አናትላይ ደግሞ የዘውድ ምልክት መኖሩን እና በዘውዱ አናት ላይ የመስቀል ምልክት መኖሩን እና ከነዚህ ምልክቶች እና አርማ ጋር በተያያዘ በምዕራፍ አራት ላይ ትንተና ተሰጥቷል፡፡

በሌላ በኩል በደርግ ዘመን የተፃፉትን ደብዳቤዎች በምናይበት ጊዜ ከላይ የተጠቀሰው አንበሳ ቢኖርም በአንበሳው አናት ላይ ያለው ዘውድ አለመኖሩን እና የዚህን አንድምታ እንዲሁም ሰንደቅ አላማው በአንበሳው ቀኝ እጅ ቢነገብም ሰንደቅ አላማ መያዣው አናት ላይ የነበረው መስቀል አለመኖሩን እና የዚህን አንድምታ በምዕራፍ አራት ማየት ይቻላል፡፡ ከዚህ ባለፈ ከቃላት አጠቃቀም አኳያም እንዲሁ ከዘመን ዘመን ልዩነቶች መኖራቸውን በደብዳቤዎቹ ውስጥ ይፃፉ የነበሩ ደብዳቤዎች ንጉሰ ነገስቱን እና የንጉሰ ነገስቱን ሹማምንት የጌትነት፣ የልበ ብርሃንነት፣ የአዋቂነት ወዘተ ስያሜ በመስጠት አብዝተው ሲያወድሱ በደርጉ ዘመን የነበሩት ደብዳቤዎች ደግሞ ኢሰፓን እና ኢትዮጵያን የሚያወድሱ እንደ «ኢትዮጵያ ትቅደም»፣ «ሁሉም ነገር ወደ ጦር ግንባር»፣ «አድሀሪነት ይውደም» «መሀይምነት ይውደም» ወዘተ የመሳሰሉት እና በንጉሱ ዘመን ከነበረው በተለየ አብዮትን እና ሀገርን የሚያወድሱ ገለፃዎች መብዛታቸውን ከተተነተኑት ደብደቤዎች መረዳት ይቻላል፡፡ ይህንንም በሶሶት መሰረታዊ ጉዳዮች ለይተን ማየት እንችላለን፡፡ 1. የደርጉ ስርዓት የነበረበትን ድክመት በመሸፈን በማህበረሰቡ ተቀባይነትን ለማግኘት፤ 2.ለውጥ የመጣ በማስመሰል በማህበረሰቡ ውስጥ የፖለቲካውን ስርዓት ለማስረፅ፤ 3. በመፈክሮች ስር በመጠለል ያለፈውን ስርዓት ለማጠልሸት እና የራሱን ስርዓት አጉልቶ ለማሳየት በማሰብ ሊሆን ይችላል፡፡ እንደውም ከደብዳቤዎቹ አኳያ የደርጉ ዘመን የመፈክር ዘመን ልንለው በምንችለው ደረጃ በደብዳቤዎቹ ውስጥ መፈክሮች ሲንፀባረቁ በጃንሆይ ዘመን የተፃፉ ደብዳቤዎች በአንፃሩ ለታችኛው መደብ የደካማነት፣ የድህነት፣ ያላዋቂነት እና ወዘተ ውክልና ሲሰጥ የላይኛው መደብንና ንጉሰ ነገስቱን ደግሞ በብዙ መልኩ ሲያወድሱ ይስተዋላሉ፡፡

በዚህ ጥናት ውስጥ ደብዳቤዎቹ ሲተነተኑ የታየው ሌላኛው ነጥብ ደብዳቤ ለሚፅፉት ሀሳቦች የባለቤትነት አሰጣጥ ላይ ያተኮረ ነበር፡፡ ፀሀፍቶች እንደሚያትቱት አንድ ደብዳቤ ፀሀፊ የሚፅፈውን ሀሳብ ባለቤትነት የቡድን ባለቤትነት ወይም የተቋም ባለቤትነት የሚሰጥ ከሆነ በሚፅፈው ሀሳብ ዙሪያ ሀላፊነት ለመውሰድ ዝግጁ አለመሆኑን እና በጉዳዩ ዙሪያ በራስ መተማመኑ ዝቅተኛ እንደሆነ ያብራራሉ፡፡

ከዚህ በተቃራኒው ደግሞ ሌሎች ፀሀፊዎች አንድ ፀሀፊ ደብዳቤ በሚፅፍበት ወቅት ነገሮችን በባለቤትነት ሲጠቀም ጉዳዩን ለማገራቅ እየሞከረ ነው ይላሉ፡፡

በሌላ በኩል አንድ ፀሀፊ በሚፅፍበት ወቅት የ «እኔ» ስሜት ባለው አገላለፅከሚገልፅ በ «እኛ» ስሜት ባለው ገለፃቢጠቀም ከትህትና እናከዲፕሎማሲያዊ አገላለፁ የመነጨ መሆኑን እና ይህም ጠቃሚ መሆኑን ያብራራሉ፡፡ እንግዲህ አጥኚዋ በደብዳቤዎቹ ውስጥ እነዚህን ነጥቦች ከላይ ከቀረቡት አገላለፆች አኳያ እንደ ደብዳቤዎቹ የቋንቋ አጠቃቀም ይዘት፣ ስሜት እና ገለፃ (tone) ለመተግበር እና ለመተንተን ሞክራለች፡፡ በዚህ መሠረት በጃንሆይም በደርጉም ዘመን የተፃፉት ደብዳቤዎች ላይ አልፎ አልፎ የሃሳቦች ባለቤት ምስጠራ ተሰጥቷል፡፡ በሌላ በኩል በጃንሆይና በደርግ ዘመን በተፃፉ ደብዳቤዎች ላይ ከሃሳቦች

ባለቤት ምስጠራ ባለፈ የሀሳቦች ምስጠራም የተስተዋለባቸው ደብዳቤዎች መኖራቸውን በምዕራፍ አራት ላይ ከትንተናው ሃሳብ ላይ መረዳት ይቻላል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ከ1922-1983 ዓ.ም. የተፃፉ ደብዳቤዎች በተፃፉበት የዘመን መንፈስ የነበረውን የፖለቲካ፣ የማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ አንድምታ አመላካች ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ለምሳሌ አባሪ ቁጥር አንድን መሠረት አድርጎ በተተነተነው ትንተና ላይ የደብዳቤዎቹ ፀሀፊዎች እራሳቸውን «ድሆችዎ» በማለት ሲገልፁ የደብዳቤውን ተቀባይ ደግሞ «ጌታችን» በሚል አገላለፅ ይገልፁታል፡፡ እንግዲህ ምዕራፍ አራት ላይ እንደተተነተነው እነዚህ አገላለፆች በወቅቱ የነበረውን የፖለቲካ የበላይነት እና የበታችነት፣ የማህበራዊ የመደብ ልዩነት፣ ከገደብ ያለፈ ጫናን ያመለክታሉ፡፡ ከዛ ባለፈ በተመሳሳይ ደብዳቤ ላይ እንደሰፈረው በወቅቱቤተክህነት እና የቤተክህነት አገልጋዮች የነበራቸውን የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ እና ማህበራዊ የበላይነት እና ተሰሚነት ያመላክታል፡፡ የበለጠ ለመረዳት የምዕራፍ አራትን ትንተና እና አባሪ ቁጥር አንድን መመልከት ይቻላል፡፡

በሌላ በኩል ከ1922-1983 ዓ.ም. ድረስ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የተፃፉ ደብዳቤዎችን እና ማመልከቻዎችን በምንመለከትበት ወቅት በደብዳቤዎቹ ውስጥ ከዘመን ዘመን የነበረን የመደበኛ ደብዳቤ መዋቅር ልዩነት መኖሩን እንረዳለን፡፡ በዚህ መሠረት ከመዋቅር አኳያ በጃንሆይ ዘመን የተፃፉ ደብዳቤዎችን በምናይበት ጊዜ አብዛኞቹ ጃንሆይን እና የጃንሆይ ሹማምንትን ከፍ ከፍ የሚያደርጉ ሲሆኑ በደርግ ዘመን ደግሞ ህብረተሰባዊት ስርዓትን፣ ዘመቻን፣ ኢትዮጵያን የሚያወድሱ ርዕሶች ሰፍረው ይገኛሉ፡፡ በደብዳቤዎቹ ሀተታ ላይም እንደዚሁ በጃንሆይ ዘመን የተፃፉ ደብዳቤዎች ላይ ለጉዳዩ ተፈፃሚነት አስፈላጊ የሚሆነው የህግና ያሰራር እንዲሁም የአሰራር ልዕልና ሳይሆን የሹማምንቱና የንጉሰ ነገስቱ በጎ ፍላጎት ወይም ፍቃድ ላይ ተመርኩዞ ጉዳዩ ፍትህ እንደሚሰጠው የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ላመሰያነት አባሪ ቁጥር አንድን እና አምስትን ማየት ይቻላል፡፡ በአንፃሩ በደርጉ ዘመን የተፃፉ ደብዳቤዎች አዋጆችን መጥቀስ፣ ያለፈውን ስርዓት መውቀስ፣ አዲሱን ስርዓት ማወደስና ከሚፃፈው ጉዳይ ጋር እያሰናሰሉ ማቅረብ በአብዛኛዎቹ ደብዳቤዎች ላይ ተስተውሏል፡፡ ከደብዳቤ መደምደሚያ አንፃር ደግሞ በጃንሆይ ዘመን የተፃፉ ደብዳቤዎች ከሠላምታ ጋር፣ ከአክብሮት ጋር ወዘተ አገላለፆችን ሲጠቀሙ በደርጉ ዘመን ደግሞ ኢትዮጵያ ትቅደም፣ ከህብረተሰባዊት ኢትዮጵያ ጋር ወደፊት ወዘተ የሚሉ አገላለፆችን ይጠቀሙ ነበር፡፡ በተመሳሳይ ከ1922-1983 ዓ.ም. በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የተፃፉ ደብዳቤዎችን ከርዕስ አሰጣጥ አኳያ ከዘመን ዘመን ያላቸውንልዩነት በምናይበት ጊዜ በጃንሆይ ዘመን ይፃፉ የነበሩት ደብዳቤዎች ርዕስ አሰጣጥ ንጉሰ ነገስቱን እና ባለሟሎቻቸውን በማሞካሸት እና ከፍ በማድረግ ላይ የተጠመዱ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ በሌላበኩል በደርግ ዘመን የተፃፉትን አወዳሽ መፈክሮች እና አርዕስቶች የንጉሳዊውን ስርአት ደግሞ በተቃራኒው ኮናኝ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ ለማረጋገጥ አባሪዎቹን መመልከት ይቻላል፡፡

## 5.2 መደምደሚያ

የጥናቱን ውጤትና ማብራሪያ መሠረት በማድረግ ከሚከተሉት መደምደሚያዎች ላይ ተደርሷል፡፡

- ከ1922-1982 ዓ.ም. ድረስ የተፃፉ መደበኛ የስራ ደብዳቤዎች ደብዳቤዎቹ ከተፃፉበት የዘመን መንፈስ፣ የፖለቲካ ማህበራዊ ሁኔታ አንፃር ሲተነተኑ የተፃፉበትን ዘመን የፖለቲካ ስርአት፣ ፖለቲካዊ እና ሀይማኖቱ የነበራቸውን ቁርኝት፣ ፖለቲካዊ እና ሀይማኖቱ በተለያዩ ዘመናት የነበራቸውን የግንኙነት ሁኔታ ያሳየ ነበር፡፡ ለምሳሌ በደብዳቤዎቹ ላይ የነበሩትን አርማዎች እና አገላለፆችበምናይበት ጊዜ በጃንሆይ ዘመን ክርስትና የሀገሪቱ ብሄራዊ ሀይማኖት እንደነበር እንረዳለን፡፡ በተቃራኒው በደርግ ዘመን የተፃፉ ደብዳቤዎች ደግሞ ሀገርን ማስቀደም እና «ኢትዮጵያ ትቅደም» የመሳሰሉ መፈክሮችን በማስቀደም የንጉሳዊውን ስርአት ማብቃት እና ሌላ ርዕዮተ አለም

መምጣት ለማሳየት በህይማኖት እና በመንግስት መካከል ልዩነት መኖሩንም ለማሳየት በጃንሆይ ዘመን በመንግስት የስራደብዳቤዎች በአርማነት ይውል የነበረውን መስቀል በማንሳት የፖለቲካ ለውጡን አሳይቷል፡፡ በዚሁ መሠረት ደብዳቤዎቹ የነበረውን ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ለማየት ሁነኛ መረጃ መሆናቸውን ለመረዳት እንችላለን፡፡

- በጃንሆይ ዘመን በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የተፃፉ ደብዳቤዎች ከቋንቋ አጠቃቀም አንፃር ከደርጉ ዘመን ለየት ያሉ ቃላትን ይጠቀሙ እንደነበረ ለምሳሌ ደብዳቤዎቹ ላይ «ወርቅ አንፈሽዎ»፣ ልበ ብርሃን፣ ጌታችን እና ወዘተ የሚሉ ቃላት ይታያሉ፡፡ ይህ የቋንቋ አጠቃቀም በደርጉ ዘመን በብዛት ስራ ላይ አይውልም፡፡ ከዚህ ባለፈበደርግ እና በህይለስላሴዘመን የቢሮ እና ሞያዊ ቃላት አጠቃቀም ልዩነት መኖሩን እንረዳለን፡፡ ለምሳሌበጀሮንድ፣ አጋፋሪ፣ ጠቅላይ ግዛት፣ አውራጃ ወዘተ በጃንሆይ ዘመንበተፃፉ ደብዳቤዎች ላይ በስፋት ይስተዋላሉ፡፡ በደርግ ዘመንደግሞ ኢሰፓ፣ ጊዜያዊ ወታደራዊ፣ ሁሉም ነገር ወደ ጦር ግንባር፣ ዘመቻ፣ ኢትዮጵያ ትቅደም፣ አብዮት ልጆቿን ትበላለች፣ ህብረተሰባዊነት ወዘተ አገላለፆች በደብዳቤዎቹ ውስጥ ማየት የተለመደ ነው፡፡ በሌላ በኩል አንድ አንድ ቃላትን በተገቢው ሁኔታ አለመጠቀም በተለይ በጃንሆይ ዘመን በተፃፉ ደብደቤዎች ላይ በጉልህ ይታያል፡፡ ከዚህ ባለፈ ከመዋቅር አኳያ በጃንሆይና በደርግ ዘመን የተፃፉ ደብዳቤዎችን መግቢያ፣ ሀተታ እና መደምደሚያ በምናይበት ጊዜ ከዘመን ዘመን የነበረውን ልዩነት መመልከት ችለናል፡፡
- ከ1922-1983 ዓ.ም. በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የተፃፉ ደብዳቤዎችን በምናይበት ጊዜ በደርግም በአብዛኛው ግን በጃንሆይ ዘመን የተፃፉ ደብዳቤዎች መግቢያ፣ ሀተታእና መደምደሚያን ደረጃውን በጠበቀ መልኩ አለመፃፋቸውን እንረዳለን፡፡ ይህም ማለት በጃንሆይ የተፃፉ ደብዳቤደዎች መዋቅር በትክክለኛ የደብዳቤ አፃፃፍ ስልት ላይ ያልተመረኮዘ እና ከዚህም ይልቅ ንጉሰ ነገስቱ፣ ሹማምንቱንና ግለሰቦችን ሲያወድስ በደርግ ዘመን የተፃፉት ደብዳቤዎች ደግሞ በአንፃሩ ህብረተሰባዊት ኢትዮጵያንና አብዮቱን በማወደስ በተቃራኒው ደግሞ የፊውዳሉን ስርዓት በመኮነን ላይ የተጠመደ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ እነዚህ ነጥቦች በምዕራፍ አራት ላይ እንደተተነተኑት የበላየረነትን ለማስቀጠል እና ርዕዮተ አለምን በህብረተሰብ ውስጥ በማስረፅ ከማሰብ የመነጩ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

## 5.3 አስተያየት

በዚህ ጥናት ሂደት ውስጥ ለመረዳት እንደተቻለው የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ይዘቶች በሰፊው ለማጥናት የሚያስችል የሰነድ ክምችት በየመስሪያ ቤቶቹ ተከማችተው እንደሚገኙ እና በዘርፉ በቂ የሆነ ጥናት አለመደረጉን ነው፡፡ ሰነዶቹ በተለያዩ መስሪያ ቤቶች በርከት ብለው ቢገኙም ቅሉእነዚህን ሰነዶች በተለይ ከስነ-ልሳን እና ቋንቋ አኳያ ለምርምርግባአትነት /መረጃነት/ በማዋል የተሰሩ ምርምሮች እጅግ አናሳ ናቸው ወይም በድፍረት የሉም ብሎ መናገር ይቻላል፡፡ ነገር ግን በታሪክ እናበፖለቲካ ሳይንስ የትምህርት ክፍሎች እነዚህን ሰነዶች በአንፃራዊነት በማስረጃነት በመጠቀም ምርምሮችን እና ትንተናዎችን ያደረጉ በጣት የሚቆጠሩ ተመራማሪዎች መኖራቸውን በዚህ ጥናት የመረጃ ስብሰባ ወቅት ለመረዳት ተችሏል፡፡

በመሆኑም በቀደመው ዘመን የተፃፉ ደብዳቤዎችን እና ማመልከቻዎችን እንደ ማስረጃ በመጠቀም ምርምር ለማድረግ የሚፈልጉ አካላት ወይም ተመራማሪዎች ሰነዶቹ በውስጣቸው ያልተነኩ እና ያልተዳሰሱ መረጃዎችን ይዘው ስለሚገኙ ቢጠቀሙባቸው ትልቅ ግብአት ነው፡፡ ምክንያቱም ሰነዶቹ /ደብዳቤዎቹ/ ከስነ ልሳን፣ ከፖለቲካ፣ ከታሪክ፣ ከስነህዝብ፣ ከስነ

ቋንቋ ጥናት (tilology) ወዘተ አኳያ ብዙ በረከት አዝለው በመገኘታቸው ነው፡፡ ነገር ግን ጥናቱ በሚደረግበት ወቅት እና መረጃ በሚሰበሰብበት ወቅትትክክለኛ ያልሆኑ ሰነዶችን በጥልቀት በመመርመር ከትክክለኛዎቹ ደብዳቤዎች /ሰነዶች/ መለየት የሁሉም አጥኝ ስራ ሊሆን ይገባዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በትንተና ወቅት ግለሰቦች፣ አጥኚዎች፣ ወይም ተመራማሪዎች ትንተናውን በተቻለ መጠን ከኖሩት ህይወት እና ከመጡበት ማህበረሰብ ወይም የቀደመ የአኗኗር ዘይቤ ተፅዕኖ ነፃ በማድረግ መተንተን ይኖርባቸዋል፡፡ ምክንያቱም አንድ ዲስኩር ደስኳሪ ወይም ተንታኝ የመጣበት ማህበረሰብ፣ ያለፈበት የቀደመ ህይወት በትንተናው ላይ ተፅዕኖ እንደሚያሳድርበት Edward car (1961) ያብራራል፡፡

ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው የደብዳቤ ሰነዶችን በመረጃ ምንጭነት በመጠቀም የተሰሩ ተዛማጅ ፅሁፎችን ማግኘት በዚህ ጥናት ውስጥ ትልቁ ፈተና ነበር፡፡ ነገር ግን ይህ ጥናት ወደ ፊት በተመሳሳይ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ምርምር ለማድረግ ለሚፈልጉ ተመራማሪዎች እና ተማሪዎች በመነሻ ሀሳብ ሰጭነት እና በመንገድ አመላካችነት ያገለግላል የሚል እምነት ስላለ በተመሳሳይ ርዕሰ ጉዳይ ጥናት የሚያጠኑ አጥኚዎች በማጣቀሻነት ሀሳቦችን በመውሰድየራሳቸውን ሀሳብ አስፋፍተው እንዲገልፁ ጠቃሚ ይሆናል፡

## ዋቢ መፅሀፍት


ያለው እንዳወቅ፡፡ /2006/ የምርምር መሠረታዊ መርሆዎች አተገባበር፡፡

አዲስ አበባ፡፡ አልፋ አሳታሚ፡፡

Aberdeen. (2011). “Formal letter writing”.

Aliya, Almoldina and Sholpan, Zharkynbekora. (2014). “Incorporating Authenticmodels in to Busines letter writing with in the ESP Course”. Kazakhstan University H.U Journal.

At kins, Andrew. (2002). “critical Dissourse Analysis: A letter to expatriates from the Rt. Hon. Sir Norman Fowler MP.

Barzun, facques and F. Graff, Henry.(1993). Modern Research”.Tubitake publisher.

Bausi.(2006). “The Axumit Background of the Ethiopic courses panonun”. In proceedings of the 15th international conference of Ethiopian studies.Wiesbaen.

Batstone, R. (1995). “Grammar in discourse: Attitude and Deniability”. In G. Cook and B. Seidlhofer, ceds) principle and practice in applied linguistics. Oxford: Oxford University Press.

Bergamo. (2010). “letter wirtng in latemodern Europe”.University of Florences. Italy.

Bhattacherjee, Anol. 2012. “Social Science Research: Principles, methods, and practices”. University of south Florida, Tampa, Forida, USA.

Car, Edward Halter. (1961). What is history. New yourk.

Caulk, R.A. (1982). “The Abyssinian Difficulty by Darrell Bates; The Amharicletters of Emperor Theodore of Ethiopia to Queen Victoria. International Journal ofAfrican Historical studies.Vol. 15, No.1.published by: Boston University African studies center.

Creku, Ashley. (2005). The Art and Rhetoric of letter writing:How letter writing manuals haveevolved and preserved rhetorical strategies through outcenturies. Okland University.

Creswell.(2000). “Research Design Qualitative. Quantitative and mixed approaches”. University of Nebaska. Linocoln.

Crum, Erin. (2018). “How to address a legal letter to the court”.

Commissions andletters of requests, online source accessed from www.delhinighcourt.nic.in Accessed on moday 03/09/2018, at 11:24 AM.

Coulmas, Florin. (2017). “writing systems: An introduction to their linguistic analysis.” Cambridge University press.

Damprow, peter.(2006). “The origins of writing as a problem of Historical Epistemology.” Cuneform Digital library initiative.

Delpech, riviane.(2012). “Two Amharic letters of Debetera Tewolde medihinof wolqayt.” It yopis publisher.

Dijk, van T.A. (1993). “Elite Discourse and Racism.” Newburypark, sage.

Ding, H. (2007). “Generee analysisof personal statement: Analysisofmoves in Applicationessaysof medical and dental school.” Englishfor specificpurposes.

Fair clough, Norman. (2003). Analysing Discourse. London.

__________________. (1989). Analysing Discourse. London.

__________________. (1992). Discourse and social change.Londo. Polity press

Harweg, R. (1978). “substitutional text linguistics in: Dressler”. Berlin

Hearn, Simon one Sinclair, Jessica. (2014). “overview: Data collection and analysis methods in Impact Evaluation.”RMIT University.

Hudson, R.A. (1980). Sociolingustics.Cambridge University press.

Igwenagu,chinelo. (2016). “Fundamentals of research methodology and Data collection.” Enugu state University of science and Techonology.

Iqbal, Tabassum and Anwar, Behzad. (2013). “Communicationstrategies: A critical Discourse Analysis ofa Business letter.” Middle-east journal of scientific research. Vol. 16,No.5.

Mason, Marianne. (1996). “Qualitative Research”. In london structure and discursive features of letters of leniency as a genere.” In the International pragmatics association.

Melika, Hadaria and mostafa, Morady. (2015). “Analysis of official letters based on applied general analytical model.” In the journal of language teaching and research. Vol. 6, No3. Iran.

M. Sandrick, Clinton. (2016). “How to write a letter Requesting a court hearing.

Nosnitsin, D. (2012). “Ethiopian manuscripts and Ethiopian manuscript studies”. Hamburg University.

Pankhurst, Richard. (1979). “The Amharic letters of Emperor Theodore of Ethiopian to Queen Victoria and her special envoy”.Oxford University press.

___________________. (2010). “Tewodros Bomba: Discovery of an Unpublished letter from Ase Tewodros to “Etege” yetamennu”. In the international journal of Ethiopian and Eritrean studies.

Panosa, Isabel. (2004). “The beginning of the written culture in Antiquity”. Revista Digital d’Humanitats.

Perham, Margery. (1969). “The government of Ethiopia”. London.

P.wood, Adrian. (1993). “Natural Resource conflicts in south-west Ethiopia: States, communities, and the role of the national conservation strategy in the search for sustainable Development”. University of Huddersfiedld. UK.

Rigg, p. (1991).“Whole language in TESOL”. TESOL Quarterly.

R., Adam. (2006). “cover letter.Almanac”. Second Edition.

R., Olson, David. (2009). “The History of the writing”.Beard.

Said, Edward.(1978). Oriantalism.Newyourk.

Schaffer and Chilton.(1997). “Handbook of Discourse Analysis”. Oxford: Blackwel publishers.

Sertse Abebe. (2011). “Bilingual script identification for optical character recognition of Amharic and English printed documents”. Addis Abeba University.

Sheyholislami J. (2018). “Critical Discourse Analysis”.Accessed on April 22, 2018. http://www.carleton. Ca/jisheyhol/ cda.htm.

Sutcliffe, p. (1992). “Peoples and Natural resources in North and South Omo and Kafa administrati regions of south-west Ethiopia: a case study of strategic natural resources planning. Addis Abeba.

Swales, J.M. (1990).“Genre analysis, English in academic and research setting.” Cambridge University press.

The first written Constition of Ethiopia in 1931.

Tola Gemechu Ango. (2018). “Midium scale” Forestland grabbing in Southwastern highlands of Ethiopia: Impacts on local livelihoods and forest Conservation”. Department of Human Geography Stockholm Uniersity.

Vllendroff, Edward. (1972). “some Early Amharic letters.” In bullet in of the school of oriental and African studies. Vol. 35, No. 2.CambridgeUniversity press.

_________________. (1986). "Two Amharic letters by the Falasha leader Tamrat Emanuel." In the journal of the royal Asiatic society of Great Britain and Ireland.No.2. Cambridge University press.


Widdowson, H. (1995). "Discourse Analysis: A critical view, language and literature".

Wood, A. (1983). "The decline of seasonal labour migration to the coffee forests of south-west Ethiopia. Department of Geography.


Xu, Bo. (2012). "An Analysis of English Business letters from the perspective of InterpersonalFunction." In jornal of English language Teaching. Vol.5, No.7.Candian center of science and Education.

Zoltan, Dorny. (2007). "Research methods in Applied linguistics Qualitative, Quantitative and mixed methodologyies." Oxford University press.


አባሪ አንድ



አባሪ ሁለት



አባሪ ሦስት



Appendix H

ኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት
የመሬት ይዞታና አስተዳደር ሚኒስቴር
የመሬት አስተዳደር ዋና መምሪያ

Imperial Ethiopian Government
Ministry of Land Reform & Administration
Dept. of Land Administration

P. O. Box

ለአቶ ገርማ ተሰማ
የሸዋ ጠቅላይ ግዛት
የመሬት ይዞታና አስተዳደር ሥራ አስኪያጅ
አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡— ለባለውለታዎች ስለሚሰጠው መሬት


በአርክስ ... ስለ ተጠቀሰው ጉዳይ የከምባታ አውራጃ ገዥ ወደፊት ኩታ ገጠም የሆኑ ... መሬቶች ለልማት ... በመንግሥት ስም ... ለማድረግ ... በልቅ ችርታ መሬት ለሚጠይቁ ሰዎች ... 28/61 ዓ.ም፡ በቁጥር 3/1259/36 ... ጥር 30/61 ዓ.ም፡ በቁጥር ለ/4530/6628/13 ... ከአውራጃው ገዥ የተላከውን ደብዳቤ ትክክል ገልበጡ ... ከዚህ ጋር አያይዣለሁ ።

... በአባሪው ጽሑፍ የተመለከተው ጉዳይ በበኩልዎ ተገቢ አስተያየት ... ደርሶን እናስታውቃለን ።

ከሰላምታ ጋር

...6.61

አባሪ አራት



Appendix - VII

አባሪ አራት የቀጠለ...

Appendix - IV continued 2

[illegible]

አባሪ አራት የቀጠለ...


3 APPENDIX VII continued 3

አባሪ አምስት

ማመልከቻ

ለክብር ሊቀ ሊቃውንት ተስፋዬ ገዛው

[illegible]

አባሪ አምስት የቀጠለ...

Appendix C-2

የቦረናን ገዥ ተኛዦዎች ሥራ የሕገ ጠበቃ አቶ አበበ ሰሺር ከነአጋሮቻችን ጋር በሕገ ፊት ቀረ እየመበሉ ነበረታችን ያለ በባላገር ስለሆነ ሰፋቹን እየበበ ሰቡ በመንግሥትና በሕገ በኩል ለጊዜውን እኛ አለንላችሁ እናንተ ገን በርቱበት በማለት የቃሬል ድጋፍ እየሰጡአችን ከቀዲዳ ጋሻ ጋሪዳ ጀርበና በደኖች ከተባሉት ሥፍራዎች ሐዲያ የተባለ ጉዳ በአነርቡ ወሬነተ ለጊደረገን ሰበበ ጋሕዳችን የአንራቻችን ሕዝብ በቋሚ አስቆጥተታለ የተደረጉትሥ ልዩ ልዩ ሰበበዎች የመንግሥት ጋሥራ ቤት ያለ ያችን ናችን የአደገ ሥራቸውም አነጓዩታጋ ቅባችን ለመንግሥት ባለሥልጣናት ለበገ ለናጥፋተ ነን የሥነበበበው በማለ በነበተ ቃል ያስ ተባበሉሉ።

ስለዚህ ከቡርነ ተያነ የሥነለሥነን የአንራቻችን ሕዝብ በሳሥና ጸፀታ ሉጠ በቃ ከአነዚአብሔርና ከነገሥ ነገሥቶ አደራ የተቀበሉ ስለሆነ ይህ የተጀመረው አደጋ ሥር ሰደ ከሕዝብ ጋር የሚያበቋሰቀ ከመሆኑ በፊት ልዩ ጊዶ ተመርጦ የነገረነ መንሻ አጥነተ አጥፊው ወደ ፍርድ ሸነን ፊት ቀርቦ አነዲቀጣና የኩሥባታ አንራቻ ሕዝብ የኢትዮጵያዊነት ስ ሜት ተከታተተ ለአገራችን ዕድገትና ብልጽገና አነሥራ ያ ደርጉ ዘንድ በግክበር እናመለከታለን ።

ገልባጭ /–

1ኛ ለሸዋ ፖሊስ ጽ/ቤት

2ኛ/ ለጸጥ ታ ጉዳኒስ ቴር

አዲስ አበባ ፤

## አባሪ ስድስት

Appendix - VI

ቁጥር፡ 3546/4774/56

1120/55
21/11/56

የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡
የከፋ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡፡

ቀን፡ ሐምሌ ፲፮ ፲፱፻፶፮ ዓ.ም.

ለፈታውራሪ መኮንን ጌንጌል፤
የቾንጆር ወረዳ ገዥ፤
ፍሩ

በወረዳው ገዛት የተጀመረውን የ1955ዓ.ም የመሬት ግምት ሥራ በማጠናቀቅ ተበርክቶባቸው ያለ ተሳቸውን መገመቻና የባላባት መተማኛ አቶ ከበደ ዱንቃ ይዘው ጠቅላይ ገዛቱ በጅሮንዱ ጽ/ቤት ቀረስ እንዲገኙ ታዘዘው ኖሮ በትእዛዙ መሠረት ለመፈጸም ያዓገታቸው በእርስያ በወረዳው ገ፫ ምክንያት መሆኑን በመዘርዘር ለመንግሥቱ ሥራ የተሳኩት አቶ ከበደ ዱንቃ አደረሾውን ለክፍል መሥሪያ ቤትያ በማዱረገ በቁጥር ቸ/31/56=በኔ 8 ቀን 1956ዓ.ም ቢጽፈልያ ገልባጩ ደርሶን ተመልክተነዋል፡፡

እንዲሁም ስለዚሁ ጉዳይ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት የከፋ ጠቅላይ ገዛት በጅሮንዱ ጽ/ቤትም በደረሰቸው ገልባጭ መነሻ በቁጥር ከ/7837/14/56=በኔ24 ቀን 1956ዓ.ም በተጻፈልያ ደብዳቤ የተባሉት የመገመቻ ከርኒያቸና የባላባት መተማኛዎች እን_ዳያ መጡ ተከልክለው እንደሆነና በነዚህም ሰነዶች ላይ እንዳች ብልሽትና ጉዳት ቢደርስባቸው ከፍ ያለ ኃላፊነትን የሚያስከትል መሆኑን በመገለጽ ቢጽፉልያ በደረሰን ገልባጭ ተረድተነዋል፡፡

አመልካቹ እንዳመለከቱት እውነት ተፈጽሞ እንደሆነ አፈጻጸሙ የሚያሳዝን ነውና ይህ ሊሆን የቻለበት ምክንያት በፍጥነት እንዲገልጹልን ሆኖ ለወደፊቱም አሰራር ደምቡን ተከትለው በጥንቃቄ ሥራው እንዲሠራ እንጂ እንደዚሁ ያለውን መጓጓፍን የሚያስከትል ነገር እንዳይ ፈጸም በጥብቅ እናስታውቃለን፡፡

ከሰላምታ ጋር፤

ግርማ ፡ እርገው ፡

ገልባጭ


..ለኢት.ን.ነ.መንግሥት= የከፋ ጠቅላይ ገዛት ጽ/ቤት፤ 21/11/56

.. .. .. .. .. ..በጅሮንዱ ጽ/ቤት፤ 12/12480

ለአቶ ከበደ ዱንቃ፤

አሰበ

አባሪ ሰባት



Appendex VI

የኢትዮጵያ፡ ንጉሠ፡ ነገሥት፡ መንግሥት፡
የጽሕፈት፡ ሚኒስቴር።

ቁጥር፡ 2057/7/78/93


አዲስ፡ አበባ፡

File No. 2075


የገንዘብ፡ ሚኒስቴር፡
አዲስ፡ አበባ፡

ክቡር፡ ሆይ፡

አባሪ ሰባት የቀጠለ...



አባሪ ስምንት



Confirmed

Model 35

የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡
የገንዘብ ፡ ሚኒስቴር ።
IMPERIAL ETHIOPIAN GOVERNMENT
MINISTRY OF FINANCE

No. 5

Addis Ababa 6/5/12

የኢትዮጵያ ፡ ን. ነ. መንግሥት
ያገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ።
128
55481

ለክቡር ያገር ግዛት ሚኒስቴር
አዲስ አበባ ።

ከጊሚራ አውራጃ ገዛት ሕዝብ ስለሚፈለገው የወዛፍ ገብር አሰባሰብ ከቡር ሻምበል ሰፍቹ ደፈሬ ሐምሌ ፳/ 1953 ዓ.ም በቁጥር 91/12542/2083/53 ለከፍተኛ ፤ ጄኔራል ዓቢይ አበበ ቢሮ ስላስተላለፉት ግልባጭ ነሐሴ 24 ቀን 1953 ዓ.ም በቁጥር 12117 የጻፉልን ደርሶናል ። —

ስለገብር አሰባሰብ በነጋሪት ጋዜጣ የተደነገገውን ዐዋጅ የገንዘብ ሚኒስቴር አሻሽሎ ምሕረት ለማድረግ ስለማይችል በቀረበው ሐሳብ መሥሪያ ቤታችን ሊስማማበት አልቻለም ። ነገር ግን ወዛፉን ገብር በሙሉ ከነአጠፊታው በአንድ ጊዜ ገባቸው በከፊል እንቀበልም ብሎ ገብር ከፋዩን መመለስ ጠቃሚ ሁኖ ባለመገኘቱ ፤ ክቡር የገንዘብ ሚኒስትር ነሐሴ 10 ቀን 1952 ዓ.ም በቁጥር 4673/7/52 ለየጠቅላይ ግዛቱ ባስተላለፉት ቴሌግራም መሠረት በየጊዜው የሚቀርበውን ገብር እየተቀበሉ ስለቀሪው ገንዘብ ማስታወሻ እየተያዘ ወደፊት በሕጉ መሠረት እንዲገባ ቢደረግ የተሻለ መሆኑን በማክበር እናመለክታለን ። —=========================

ከማክበር ሰላምታ ጋር

ክፍሌ ጓዴ
የጥ ዲሬክተር ።

ገልባጭ ፡— ለክቡር የከፋ ጠ/ግዛት እ/ቤት
ጊ ማ

3/4/54

4 ፡ 1 ፡ 54

አባሪ ዘጠኝ

APPendix - XI

የኢ.ፊ.ፊ.መ

የጀንጀሮ ቀበሌ ጽሕፈት ቤት 11/926

29-7-78

ቁጥር ፡ 7912

ኅዳር ፲፩ ቀን ፲፱፴፬ ዓ.ም

ለከፋ የክፍለ አውራጃ ጠቅላይ ግዛት ጽሕፈት ቤት

ጅማ

ክቡር ሆይ

ስለ አስተዳደር ገሕሬ የፃፉ በ11/10/84 ቁጥር ፕቅምት 14/38 ዓ.ም የተጻፈ ደብዳቤ ጎዳር 6/38 ዓ.ም ደርሶኛል/

የአገሩ ባህል ምንም ልዩ ልዩ ቢሆንም ሕዝቡን ለማስተዳደር ለአገሩ የአገር ገንዘብ ዘዴ አሁንም የሕዝቡን ግሕሪ በመምሰል ሲካሄድ ቢቆይ የአስተዳደር ዘዴ ሕግ እንደ ሆነ ከሁን ግዴታ ዘመን በ38 ዓ.ም በአዲሱ ኢትዮጵያ አስተዳደር ዘዴ መመሪያ በማድረግ እንዲሠራ መታሰቡ ስለተገለጸ/

የጀንጀሮ ቀበሌ ከነገር ካሁን በፊት በግብር በብዙህ ጉዳት ስለሚደርስበት የዚህን ግብር ቢቀለልለት በጣም የሚደሰት መሆኑን ስለአመለከተ፡

ምክንያቱ፡ አገሩ ኑሮው እንሰት እየተከለ በመኖሩ ሌላ ስራ ለማረስ ስለ ስላለበት ሕዝቡ የተቀነሰ እንዲሆን አገሩ በሚያፈራው ሕብት ሥራ መሥራት እንዲስፋፋ በያይነቱ የሕገር ፕቅም የሚሰጠው እንዲሠራ የመንግሥት ትእዛዝ ተሳልሮ በአዋጅ ሲነገር ሕዝቡ ሠራተኛ በመሆኑ በብዙህ ብልጽግና የሚያገኝ መሆኑን ለክቡርነትዎ በመግለጽ፡

በዚህ አኳሆን እንዲታሰብበት በማክበር አመለክታለሁ፡

[illegible]


ገብረ ተክሌ

ይህ፡ [illegible]

[illegible]

10/4/28 [illegible]

አባሪ አስር



አገር - 10

የኢትዮጵያ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት
በከፋ ክፍለ ሀገር
የጂማ አውራጃ አስተዳደር ጽ/ቤት
ስልክ ቁ. 110103

ቁጥር 5714/1458
ጅማ [illegible] ቀን 1967 ዓ.ም

= 2 =

[illegible] ንጽሕናቸውን ቢመለስ መሬታቸውን እስከ ዛሬ
ሁለት ዓመታት በእስር ቢንገላቱ ከቆዩ በኋላ [illegible] በቁጥር 1480/76/67 በተጻፈ
በገበርና ሥራ የሚተዳደሩ መሆኑን ነሐሴ 23 ቀን 67 ዓ/ም [illegible]
ደብዳቤ አረጋግጠውልናል ፡፡ [illegible] በ5ቱ የወሰነት ወረራ ዘመን

ሠ/ በሠኮሩ ወረዳ ፡- ነዋሪ/የሆኑት አቶ በላይ አንገዳ [illegible] የሚተዳደሩትም
በአርበኝነት ማገልገላቸውንና ያስመሰከሩበትንም ማስረጃ አቅርበው [illegible] ከወረዳው አስተዳደር ጽ/ቤት ነሐሴ 30/67 ዓ/ም
በሚያገኙት የሥራ አበል መሆኑን በመግለጽ ከወረዳው አስተዳደር [illegible] የተገለጸልን ሲሆን ፡-
በቁጥር 1268/180/5/67 በተጻፈ ደብዳቤ [illegible] ማዘጋጃ ቤቶች በየክፍላቸው በወላጅ
የቀረት ሁለት የወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤቶችና [illegible] የነበሩና አርበኝነታቸውን
[illegible] ዘመን ቤትና ንብረታቸውን [illegible] በመግለጽ ፡-
[illegible] የቤት አርበኞች [illegible]
[illegible] በቁጥር 1938/67

1ኛ/ የቄና ወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤት በቁጥር 2017/2045
2ኛ/ [illegible] ወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤት በቁጥር ሽ/1042/394/67
3ኛ/ የጅማ ከተማ ማዘጋጃ ቤት በቁጥር ሠ/1159/67 በተጻፈ ደብዳቤ [illegible]
4ኛ/ የበርበ ከተማ ማዘጋጃ ቤት በቁጥር [illegible]


ያረጋገጡልን መሆኑን እናገለጸን ፡-
[illegible] ወረዳ አስተዳደር
እስከ ዛሬ በተደረገው መጻጻፍ ሁሉ ለጉዳዩ መልስ ያልሰጠው [illegible] የበኩሉን መልስ
ጽ/ቤትም ተደጋግሞ ቢተላለፍለት ትእዛዝ መሠረት ከ2 ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ [illegible]
[illegible] በዚሁ ደብዳቤ [illegible] እንገልጻለን ፡፡

ኢትዮጵያ ትቅደም

ግልባጭ ፡-
ለ[illegible] ወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤት
በኩ[illegible] ፡-

6/13/67
11566

አባሪ አስራ አንድ



ቁጥር 5714/1958

ለከፋ ክፍለ ሀገር አስተዳደር ጽ/ቤት

1ኛ/ በቁጥር አ27/10067/9411/54 በ25/11/67 ዓ/ም
2ኛ/ " አ27/10566/9411/54 ነሐሴ 8/67 ዓ/ም
3ኛ/ " አ27/11011/9411/54 ነሐሴ 22/67 ዓ/ም

1ኛ/ በቁጥር 5056/67 ሐምሌ 29/67 ዓ/ም
2ኛ/ " 5322/1958 ነሐሴ 9/67 ዓ/ም
3ኛ/ " 5577/1958 ነሐሴ 28/67 ዓ/ም

ሀ/ በጂንጀሮ ወረዳ አስተዳደር

ለ/ በወየርዋ ወረዳ አስተዳደር
... በቁጥር 1580/67 በተጻፈ ደብዳቤ አረጋግጦልናል ፡፡

ሐ/ ከተርዋ ወረዳ አስተዳደር
... በቁጥር 1450/67 በተጻፈ ደብዳቤ ገልጾልናል ፡፡

አባሪ አስራ ሁለት

ን·ወ/ዓ/ዐዐ7
ግንቦት 2. 1970

ለብዙ ዓመታት በተገር ቢሮክራሲና በበከቷ ቢበቋቋ ተተዋወ ሠፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ አቢዮቱ ከመጣለትና የበዝባዦን ሥርዓት ግንበር ከጣለ ወዲህ በመለስተኛ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም መሠረት ለጭቁኑ ወገን በበለጠ ትምህርት ለማዳረስ ይቻል ዘንድ ትምህርት ሚኒስቴር የትምህርት ተሣትፎ ያለ አድልዎ የሚደርስበትን ዘዴ በመፈለግ ላይ ነው ።

ለአያሌ ዘመናት የተዛባውን የትምህርት ሥርዓት ችግር በትክክለኛ መረጃ ተመርኩዞ ከዚያም ሳይንሣዊ በሆነ ዘዴ ችግሩን ከአጠና በኋላ መፍትሔ ለመጠቆም በትምህርት የተሠማሩትን ሰዎችና በጠቅላላ የኅብረተሰቡን ፍጹም የሆነ ትብብርና መስዋትነት ይጠይቃል ።

በ1970 ዓ.ም እና እንዲሁም በ1971 ዓ.ም የትምህርት ሚኒስቴር የረጅም የመካከለኛ እንዲሁም ያጭር ጊዜ ጥናትን ለማከናወን እቅድ አውጥቷል ። ከመጣው ዐቅድ ውስጥ እንደመነሻ ሆኖ ለወደፊቱ ገን ጠለቅና ሰፊ ያለ ጥናትን የሚያስከትል ያሁኑ ያለ አድልዎ የትምህርት ተሣትፎ በኢትዮጵያ የሚል ጥናት በሆን ከእየክፍላተ ሀገሩ በትምህርት ሥርጭት ጉዳይ የሚጠኑ ናቸው የተባሉትን ወረዳዎች በከፊል ተመርጠው ለጥናት የሚያገለግለው እስታቲስቲካዊ መረጃዎችን መሰብሰብ ገድ ስለሆነ፣ በክፍለ ሀገሩ ውስጥ በ________ አውራጃ ________ የተባለውን ወረዳ ብቻ የሚመለከተውን ከትምህርት ሚኒስቴር በሚመጡት ሰዎችና እናንተ ለዚሁ ጉዳይ ከምትመድቧቸው ሰዎች ጋር በመመካከር በጥናቷ መረጃዎች ተሞልተው እንዲላኩልን በማድረግ ከትምህርት ሚኒስቴር የሚላኩት አጥኚዎችን በመነጋገር እንዲሁም እነሱን የሚረዳ ወይም የሚረዱ ሰዎችን መመደብና ሌላም አስፈላጊ የሆነውን ትብብር ሁሉ ታደርጉላቸው ዘንድ ከአደራ ጋር እናሳስባለን በማለት በ19/8/70 ዓ.ም በቁ.ረ 3/199/2796/4 በተጻፈ ደብዳቤ የኅብረተሰብአዊት ኢትዮጵያ ጊ.ወ. መንግሥት የትምህርት ሚኒስቴር ለክፍላተ ሀገራት ት/ቤቶች ጽ/ቤት በአድራሻ ሲጽፍ በተደረገልን ገልባጭ ላይ እንደተመለከተው አስፈላጊው ትብብር እንዲደረግላቸው እናሳስባለን ።

እሸቱ ካሳ
የማስተባበሪያ ክፍል ኃላፊ

**ግልባጭ፡**

ለኅብረተሰብአዊት ኢትዮጵያ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት
የትምህርት ሚኒስቴር
አዲስ አበባ ፡፡

../ጽስ

አባሪ አስራ ሦስት

ክ/219/መ7/2
ሐምሌ 15 1975

ከፍለ ሀገር አስተዳደር ጽ/ቤት

ለአስብ አውራጃ አስተዳደር ጽ/ቤት

አሰብ፡፡

ጉዳዩ፡ ስለመሠረተ ትምህርት ዘመቻ መዋጮ፡፡

1. በሀገር ውስጥ መወደዱን፣ በዓለም ኅብረተሰብ ዘንድ አድናቆትን ያተረፈው የብሔራዊ መሠረተ ትምህርት ዘመቻ ፕሮግራም አብዮታዊው መንግሥት ባወጣው ከፍተኛ ፖሊሲና መመሪያ የሚካሄድ መሆኑ ይታወቃል፡፡

2. ይኸን ከፍተኛ ዓላማ ለማስፈጸም ሰፊው ሕዝብ በገንዘብ መዋጮ ከፍተኛ ድጋፍ በመስጠት ላይ እንደሚገኝም የታወቀ ነው፡፡

3. ከሕዝብ የሚገኘውን መዋጮ በማስመልከት ጉዳዩ በሚመለከተው የትምህርት ሚኒስትርና የብሔራዊ መሠረተ ትምህርት ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴ ሲቀመንበር ሐምሌ 13/75 ዓ.ም. በቁጥር 10/3666/183 በጻፉልን ደብዳቤ፣ ለመዋጮው አሰባሰብ ብዛት ያላቸው ደረሰኞች ተዘጋጅተው የሚገኙና የዚህ መዋጮም ከሌላው መዋጮ ጋር በአንድ ዓይነት ደረጃ መታየት የማይገባው መሆኑን በመግለጽ አሠራሩ ለሕዝብ መዋጮ አሰባሰብ በቅርቡ ከወጣው መመሪያ ውጭ ይሆን ዘንድ አሳስበዋል፡፡

ዶር ፡ ጥላሁን
ሚኒስትር፡

ዘነበ ፡ ብርሃኑ ፡ ተገኝ ፡
ዘርፍ ፡ ኃላፊ ፡

አባሪ አስራ ሦስት የቀጠለ...

\- 2 -

4\. እንደ ተገለጸውም የዚህ የመሠረተ ትምህርት ዘመቻ ሥራ በመንግሥት አቅጣጫና ፖሊሲ ተደግፎ የተዘጋጀ፣ የራሱ የሆነ በፊ ዕቅድና መመሪያም ያለው ስለሆነ፣ ስለጠቀሳሰው ጉዳይ ወደፊት ከመንግሥት ተጨማሪ መመሪያ እስኪሰጥ ድረስ ይኸን በሚመለከት ከሕዝብ የሚሰበሰበው መዋጮ ካሁን ቀደም ሚያዝያ 19/75 ዓ.ም. በቁጥር ከ/265/መ2 ከተጻፈ ደብዳቤ ጋር የተላለፈውን መመሪያ ሣይከተሉ ለብቻው በተዘጋጀው መመሪያና ደረሰኝ እንዲሰበሰብ አስታውቃለሁ።

15/11/75

ዘነበ ብርሃኑ ትንሣኤ

ኢትዮጵያ ትቅደም

ታዬ ጥላሁን

ሚኒስትር

ግልባጭ፣ ለኅብረተሰብአዊት ኢትዮጵያ ጊ.ወ.መንግሥት

የብሔራዊ አብዮታዊ የምርት ዘመቻ ማዕከላዊ

ፕ/ጉ ጠቅላይ መምሪያ

" ለትምህርት ሚኒስቴር

አዲስ አበባ።

አባሪ አስራ አራት

ለ ከፋ ክፍለ ሀገር አስተዳደር ጽ/ቤት
ጅማ ::

ቀ1/233/መ7
ግንቦት 7 1976

ለአቦበ አውራጃ አስተዳደር ጽ/ቤት
አቦበ ::

ጉዳዩ:-- በሕዝብ ቁጥጥር ሥር ስለዋሉት የግል ት/ቤቶች አመራርና አስተዳደር፣

1. ርዕሱን በሚመለከት የትምህርት ሚኒስቴር ሚያዝያ 26/76 ዓ.ም በቁጥር 1/5-6H12/1527/66 የጻፈልንን ደብዳቤ ትክክል ገልባጭ 4 ገጽ ከዚህ ጋር ልከናል ::

2. በአባሪው ደብዳቤ ላይ እንደተመለከተው፣ የግል ት/ቤቶችን በሕዝብ ቁጥጥር ሥር ለማድረግ የወጣው አዋጅ ቁጥር 54/68 በሥራ ላይ ውሎ ሲታይ በአፈጻጸም ረገድ አንዳንድ ጉድለቶች በመከሰታቸው ይህ አዋጅ ተሽሮ በቅርቡ በወጣው አዋጅ ቁጥር 260/1976 መተካቱ የተገለጸና፣ አዋጁንም በየደረጃው ተግባራዊ ለማድረግ የትምህርት ሚኒስቴር ሴሚናር የሚሰጥ መሆኑ የተጠቆመ ስለሆነ፣

አዋጁን በሥራ ላይ በማዋልም ሆነ ሴሚናሩን በመከፈል ረገድ ባለው አፈጻጸም በየደረጃው የሚገኙት ኃላፊዎች የተለመደ ድጋፋቸውንና ትብብራቸውን ያደርጉ ዘንድ ከወዲሁ ለሚመለከታቸው መሪያ እንዲሰጥ እናስታውቃለን ::

6/9/76

ዘነበ ፡ ብርሃን ፡ ትንግሡ ፡
ዘርፍ ፡ ኃላፊ ፡

ኢትዮጵያ ፡ ትቅደም
6.9.76

ገልባጭ፣ ለኅብረተሰብአዊት ኢት/ጊ/ወ/መንግሥት
የትምህርት ሚኒስቴር
አዲስ አበባ ::

# አባሪ አስራ አምስት

የኅብረተሰብአዊት ኢትዮጵያ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት ፤
በአገር አስተዳደር ሚኒስቴር ፤
የከፋ ክፍለ ሀገር አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ።

ቁጥር ከ/አ/ማ/ክ/205/70
24/12 ቀን 1970 ዓ.ም

ለማጂ አውራጃ አብዮትና ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴ
ማ ጂ ፡ ፡

ቀደም የአሜሪካን ሚሲዮን ኃላም በቴል መካነኢየሱስ ይባል የነበረው ት/ቤት አዲስ ስያሜ እንዲሰጠው በታሰበው ሃሣብ መሠረት ከቀረቡት ስያሜዎች መካከል " የለውጥ ፍሬ " በመባል እንዲሠየም የከፍሉ ሀገሩ የአብዮትና ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴ የተስማማበት መሆኑን አየገለጽን ፣ ይህም አዲስ ስም ትምህርት ቤቱ በሚገኝበት የብሔረሰብ ቋንቋ ተተርጉሞ ስያሜው እንዲሆን ተወስኗል ፡ ፡—

የኅብረተሰብአዊት ኢትዮጵያ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት የአገር አስተዳደር ሚኒስቴርም ስያሜውን ተቀብሉ ለማጽደቅ እንዲያመች ከአውራጃው ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴ የተላከውን 1 ገጽ አባሪ አያይዘን መላካችንን እናስታውቃለን ፡ ፡

ኢትዮጵያ ትቅደም

ሻምበል ተሰማ በላይ
የጠቅላይ አስተዳዳሪ

ገልባጭ ፡—


ለአገር አስተዳደር ሚኒስቴር
አዲስ አበባ ፡ ፡

3. 1970

2

አባሪ አስራ ስድስት

Map of Southwestern Ethiopia




Source :https://www.ethnologue.com/map/DJER_z, accessed on 23 may 2010 E. C at 9:30 local time.

**ማረጋገጫ**

ይህ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ 1922 – 1983 ዓ.ም. ድረስ የተፃፉ የሥራ ደብዳቤዎች የቋንቋ አጠቃቀም ይዘት ትንተና በሚል ርዕስ የተዘጋጀ ጥናት ከዚህ በታች ስምና ፊርማዋ የሰፈረ አጥኚ ሥራ መሆኑን ለማረጋገጥ ትወዳለች፡፡

የአጥኝዋ ስም ቅድስት ጫንያለው

ፊርማ -------------------

ቀን---------------------

ጅማ

ተገቢው ማሻሻያ የተደረገበት ስለሆነ ገቢ ይሁን

የዋና አማካሪ ስም ---------------------------

ፊርማ ------------------